# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 044 ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






# ለኢትዮጵያ የብልጽግና ጉዞ ስኬት

## ሁሉም በየመስኩ እንዲተጋ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ አሳሰቡ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ለኢትዮጵያ የብልጽግና ጉዞ ስኬት የዜጎች ጥረትና የመልማት አቅም ወሳኝ በመሆኑ በሁሉም መስክ ራሷን የቻለች ነጻ ሀገር ለመገንባት መትጋት እንደሚገባ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አሳሰቡ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኦሮሚያ ክልል ጅማ ዞን እንዲሁም በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ የተከነወኑ የልማት ሥራዎችን ከመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ጋር በመሆን ጎብኝተዋል።

በአካባቢው በተለይም በሻይ ቅጠልና በሩዝ ልማት አስደናቂ ተግባራት እየተከናወኑ መሆኑን መመልከታቸውን ተናግረዋል።

በጅማ ዞን በኩታገጠም እየለማ ያለው የሩዝ ምርት አስደሳች መሆኑን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሻይ ቅጠል ልማትም ለሀገር ውስጥ በቂ ፍጆታ እየተመረተ

ለኢትዮጵያ የብልጽግና ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# "በኢትዮጵያ የተጀመሩትን ሁለንተናዊ ለውጦች ከዳር ለማድረስ 'ስለኢትዮጵያ'ን የመሳሰሉ የውይይት መድረኮች በስፋት ያስፈልጉናል"

-አቶ ተስፋዬ በልጅጌ
በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር



ሙሳ ሙሐመድ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ለውጦች ለማስቀጠል የተጀመረው የመነጋገር ሂደት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር አቶ ተስፋዬ በልጂጌ ተናገሩ፡፡

አቶ ተስፋዬ በልጅጌ በቅርቡ በጋምቤላ በተካሄደው ፲ኛው "ስለኢትዮጵያ" የውይይት መድረክ ላይ እንደተናገሩት፣ በሀገር ደረጃ ኢትዮጵያ እየመጡ ባሉት ለውጦች እና በሚያስፈልጓት ጉዳዮች ዙሪያ የተጀመሩት ስለኢትዮጵያ የመሳሰሉት የውይይት መድረኮች በሁሉም ዘርፎችና አካባቢዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡

አቶ ተስፋዬ እንደገለጹት፣ በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ዘርፎች ላይ ለውጥ ለማምጣትና የመጡትንም ለማስቀጠል የተጀመሩት የ"ስለኢትዮጵያ" ንግግሮች በሁሉም አካባቢዎች ተጠናክረው ሊቀጠሉ ይገባል፡፡

"በኢትዮጵያ ወደ ገጽ 4 ዞሯል

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

# ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ክብር ድምፃቸውን ላሰሙ ኢትዮጵያውያን መንግሥት ምስጋና አቀረበ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- መንግሥት ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ክብር ድምፃቸውን ላሰሙ መላ ኢትዮጵያውን ምስጋና አቀረበ፡፡

የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ትናንት ባወጣው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ

ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# የውጭ ተጽእኖን መቋቋም የሚያስችል የዲፕሎማሲ ስራ በተናበበና በተቀናጀ መንገድ መስራት ይጠበቅብናል

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያውያን የውጭ ተጽእኖን መቋቋም የሚያስችል የዲፕሎማሲ ስራ በተናበበና በተቀናጀ መንገድ መስራት እንደሚጠበቅባቸው የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ ተናገሩ፡፡

ርዕሰ መስተዳድሩ በአማራ ክልል በሰላማዊ ሰልፍ ድጋፍ ላደረጉ ዜጎች ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግና እና አርበኛ ነው፡፡ በተለያዩ ዘመናት ለተቃጣበት ጥቃት ሁሉ ያልተበገረ፤ ኢትዮጵያን በጽናት፣ በመስዕዋትነት ክብርና ነጻነቷን አስጠብቆ ያጸና ሕዝብ ነው። ኢትዮጵያም በረጅም ታሪኳ ህልውናዋን እና አድነቷን ያስከበረችው እና እያስከበረች ያለችው ደም በተከፈለበት መስዕዋትነት ነው።

የውጭ ወደ ገጽ 4 ዞሯል








ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

አቶ ሀሚድ አሕመድ

# አልማ የአባላቱን ቁጥር ስምንት ሚሊዮን ለማድረስ አቅዷል

**ፋንታነሽ ክንዴ**

አዲስ አበባ፡- የአማራ ልማት ማሕበር (አልማ) በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ሕዝባዊ መሠረቱን በማስፋት የአባላቱን ቁጥር ስምንት ሚሊዮን ለማድረስ ማቀዱን አስታወቀ:: በቀጣይነት ልማቱን በዘላቂነት ለመደገፍ የሚያስችሉ የኢንቨስትመንት ሥራዎችን ለመሥራት በሂደት ላይ እንደሚገኝም ተጠቁሟል::

የአማራ ልማት ማሕበር (አልማ) ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚና የአዲስ አበባ ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ሀሚድ አሕመድ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ማሕበሩ በአሁኑ ሰዓት 4 ነጥብ 5 ሚሊዮን አባላት አሉት:: ከ2015 እስከ 2017 በሚተገበረው አዲሱ የስትራቴጂክ እቅድ ትግበራ ጊዜ ሕዝባዊ መሠረቱን በማስፋት የአባላቱን ቁጥር ስምንት ሚሊዮን ለማድረስ አቅዷል::

ከአማራ ልማት ማሕበር አባላት 99 በመቶ የሚሆኑት በአማራ ክልል ይገኛሉ ያሉት ኃላፊው፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ለማሕበሩ ያለው የእኔነት ስሜት በመጨመሩ አባላት ቁጥር እያደገ መጥቷል:: በቀጣይነት ከአማራ ክልል በተጨማሪ በሌሎች አካባቢዎችም ጠንካራ የሕዝብ ንቅናቄ በማድረግ የማሕበሩን ሕዝባዊ መሠረት ማስፋትና የአባላት ቁጥር ለማሳደግ ሰፋፊ ሥራ መሥራት ይጠይቃል:: ማሕበሩ በቀጣይ አንዱ የትኩረት አቅጣጫው ይህ ነው ብለዋል::

አባላቱን በማስፋትና በአዋጁ መሠረት ሙሉ ትርፋቸው መቶ በመቶ ልማት ላይ የሚውል ኢንቨስትመንት ላይ በመሠማራት ከአስር ዓመት በኋላ የክልሉ ሕዝብ በማሕበራዊ ዘርፍ ያለበትን ችግር በራሱ አቅም የሚፈታበት ደረጃ ላይ ለማድረስ ያስቀመጠውን ራዕይ ለማሳካት እየሠራ መሆኑን አመልክተው፤ የሎጅ፣ የመጠጥ ውሃና በዋና ዋና ከተሞች ሁለገብ ሕንጻዎችን መገንባት ጥናታቸው ከተጠናቀቁ የኢንቨስትመንት ሥራዎች መካከል መሆናቸውን ገልጸዋል::

በቀጣይነትም ልማቱን በዘላቂነት ለመደገፍ የሚያስችሉ የቢዝነስ ኢንተርፕራይዞችን በጥናት ላይ ተመስርቶ እያስፋፋ እንደሚሄድም አስታውቀዋል::

አማራ ልማት ማሕበር የሕዝብ ማሕበር ነው ያሉት አቶ ሀሚድ፤ ሕዝብ በአንድነት ከቆመ የራሱን ችግር በራሱ መፍታት የማይችለው ችግር የለም:: የአልማ ፕሮጀክቶች ደግሞ በሕዝቡ ፍላጎት ላይ ተመስርተው ለሕዝብ የሚሠሩ ናቸው ሲሉም ተናግረዋል::

በመሆኑም አማራ ልማት ማሕበር የእኔ ማሕበር ነው በማለት መደገፍ፣ ከጎኑ መቆምና በገንዘብ፣ በሃሳብና በእውቀት ማሕበሩን ማገዝ እንደሚገባ ጠቁመው፤ ሁሉም አገር ወዳድ ዜጎች አማራ ልማት ማሕበርን እንዲደግፉ ጥሪ አቅርበዋል::

# ለ22 ዓመታት ከአንድ ለባዶ እስከ ባቢሎን በሳሎን

**ዳግማዊት ግርማ**

ቀኑ እሁድ ነበር ፤ ወንዱ፣ ሴቱ፣ ሙስሊም፣ ክርስቲያኑ፣ ወደ አንድ ቦታ ቀጠሮ ይዟል:: የተቃጠረበትን ሁሉ ሰርዞ ጉዞው ወደ አንድ ስፍራ ብቻ ያደረገ እስኪመስል መንገዱን የሰው ጎርፍ አጥለቅልቆት በኢትዮጵያ ብሄራዊ ቴአትር ቤት በር ላይ ከትሟል:: የመዲናዋ አዲስ አበባ ሰው ዘር ሁሉ ስብሰባው እዚህ ነው የተባለ ይመስል ሁሉም መዳረሻውን ወደ አንድ ስፍራ አድርጓል::

የዚህ ሁሉ ሰው በአንድ ስፍራ መገኘት ምክንያትም በቀድሞ ስሙ "አንድ ለባዶ" ያሁኑ ባቢሎን በሳሎን የተሰኘውን ቴአትር ሽኝት ለማድረግ ነበር:: በአንድ ክፍለ ዘመን ያህል ባስቆጠረው የኢትዮጵያ ቴአትር ታሪክ ውስጥ ሩብ ያህል የተጠጋውን ጉዞውን የከወነው ከባቢሎን በሳሎን ጋር ነው:: ቴአትርቤቱ የክፉና ደግ ጊዜውን ከባቢሎን በሳሎን ጋር አሳልፏል::

ልጅ ወልዶ ለማሳደግ፣ ዘርቶ ለመልቀም፣ ነግዶ ለማትረፍ፣ ከድህነት ዓለም ወጥቶ ሀብታም ለመባል፣ የጎረምሳ ልጅ አባት ለመሆን እንዲሁም አስተምሮ ለማስመረቅ በሚበቃ በዚህ ለሩብ ክፍለ ዘመን በጣት የሚቆጠር ጊዜ በቀረው እድሜ ላይ ብዙ ይሰራበታል:: አንድ ቴአትር ይሄን ያህል በሰው ልብ ውስጥ ለመኖር ባቢሎን በሳሎንን መሆን ይጠበቅበታል::

በኢትዮጵያ የቴአትር ታሪክ 22 ዓመታት ሳያቋርጥ የታየው ብቸኛ ቴአትር ነው:: አንዳንዶቹ ገፀ ባህሪያት በተለያየ ዘመን የተለያዩ ሰዎች ቢጫወቷቸውም በአለማየሁ ታደሰ እና በሉሌ አሻጋሪ የተወከሉት ባልና ሚስቱ ውብሸት እና ትዝታ ቴአትሩ በታየባቸው ዓመታት ሁሉ ታይተዋል:: ባልና ሚስቱ በገሀዱ አለማቸው ላይ ሰርግ አያውቁ ለቅሶ የለ የየግል ሕይወቶቻቸውን እርግፍ አድርገው ትተው ጉዳያቸው ሁሉ ነገራቸው ቴአትሩ ሆኖ ከርመዋል::

በውድነህ ክፍሌ ተደርሶ በተስፋዬ ገብረሃና እንዲሁም አሁን ላይ በስጋ የተለየን ሰለሞን ሙላት የተዘጋጀው ቴአትሩ



አለማየሁ ታደሰ፣ ስናፍቅሽ ተስፋዬ፣ ዳንኤል ተገኝ፣ ፍቃዱ ከበደ፣ ራሄሌ ተሾመ፣ ሰላማዊት በዛብህ፣ እመቤት ወ/ገብርኤል፣ ህንፀተ ታደሰ፣ እንድሪስ አህመድ፣ ሉሌ አሻጋሪ እና ሌሎችም ተሳትፈውበታል።

ባቢሎን በሳሎን ቴአትር ላይ ደለለኝ የተሰኘውን ገፀ ባህሪ ሰሞን ቦጋለ፣ ዳንኤል ተገኝ፣ ጌታሁን ሰለሞን፣ ያረጋል አጥናፉ፣ ሳምሶን ታደሰ፣ ሰለሞን ሙላትን ጨምሮ ዘጠኝ ተዋንያን ተቀያይረው ሰርተውታል። ዳንኤል ተገኝ ግን አስራ አራት ዓመት ያለማቋረጥ ተውኖታል::

የባቢሎን ታሪክ በቅዱሱ መፅሀፍ ታሪክ ላይ የሚገኝ ነው!! የባቢሎናውያን ታሪክ፤ ነገሩ እንዲህ ነው... በድሮ ጊዜ ነበር፤ ሰዎች ሰለጠንን አሉ፤ በትእቢትም ታበዩ፤ ፈጠረን ያሉትን አምላካቸውን ይኖርበታል ወዳሉት ሰማይ ድረስ የሚያደርስ ባቢሎን የተሰኘ ግንብ ይሰራሉ፤ እግዚአብሔርም እያንዳንዱ በተለየ ቋንቋ እንዲናገርበት ልሳናታቸውን አደባለቀ። መግባባት አልተቻላቸውምና ስራው ቆመ። ከዚያ በኋላ፣ ሕዝቦቹ ወደ ልዩ ልዩ መሬት ክፍሎች ሄዱ። ይህ ታሪክ ብዙ የተለያዩ ዘሮችና ቋንቋዎች መኖሩን ለመግለጽ እንደሚጠቅም ይታስባል። ርዕሱ በመካከላቸው ያለውን የጠብ ግድግዳ ለማፍረስ ያልቻሉት ባልና ሚስት ታሪክን ስለሰነደ ነው ባቢሎን በሳሎን የተሰኘ ርዕስ የተሰጠው::

ቴአትሩ የተመሰረተው አንድ ቤት ለሁለት ከፍለው በሚኖሩት ውብሸት እና ትዝታ በተባሉ ባልና ሚስት ላይ ነው:: ቅናት ፍቅር ንዴት ደስታ በተከፈለችው ቤታቸው ላይ ተስተውሏል:: አንዳቸው ሌላኛቸውን ለማስቀናት የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም። በዚህ ውስጥ ታዳሚ በማይመለስ የሳቅ ማዕበል ውስጥ ሲሰጥም ይስተዋላል::

የነ ትዝታ አንድ ቤት ናት በባቢሎናዊው መንፈስ ውስጥ ግን ሀገር ይወክላል፤ ቋንቋቸው ለተደበላለቀባቸው ስለ አንድ ነገር እያወሩ መግባባት ላቃታቸው ሁሉ የሚሆን በስላቅ እየተዋዛ ብዙ ይነገራል::

የቴአትሩ አባትና የሃሳብ ባለቤት ደራሲ ውድነህ ክፍሌ የባቢሎን በሳሎን ወላጅ ብቻ አይደለም፤ አስራ አራት ቴአትሮችንም ለመድረክ አብቅቷል:: አሁን በቅርቡም ከአራት ያላነሱ ቴአትሮች ለመድረክ ይበቃሉ። የሌሊት ሙሽሮች የተሰኘው ቴአትሩም ተከፍቷል።

# የከምባታ ሕዝብ አዲስ የቱሪዝም መስህብ ገጸበረከት

**ኃይሉ ሣህለድንግል**

ግርጌ ካለው ሜዳ ላይ ሆነን ተራራው ደረት ላይ ከተመለከትናቸው ደረጃዎች ጋር ገጥመናል፤ ቁና ቁና መተንፈስ፣ የደከመን ቆም ብለን የወጣናቸውን ደረጃዎችና የተነሳንበትን ሜዳና ዙሪያ ገባ ቁልቁል መመልከት፣ እንደገና መጓዝ ይዘናል:: ሜዳው ላይ ሆነን ተራራው ላይ የተመለከትነው ጉም እኛንም እየተመላለሰ ያለብሰናል:: ጉሙ የተራራውን ከፍታ በሚገባ ይጠቁማል::

የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎች ፣ የቱሪዝም ዘርፍ ተዋንያንና ጋዜጠኞች በቅርቡ ከከምባታና ጠምባሮ ዞን ዱራሜ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ በሚገኘው የአምበሪቾ ተራራ ላይ የተገነቡትን 777 ደረጃዎች እየወጡ ናቸው:: ከዱራሜ ከተማ ስምንት ኪሎ ሜትር ርቀት ያለው ይህ ተራራ፣ ከባህር ወለል በ2ሺ 600 ሜትር ከፍታ ላይ ይገኛል:: ተንቀሳቃሽ ምስሎችንና ፎቶዎችን ያነሳሉ፤ ቃለ ምልልሶችን ያደርጋሉ:: በወቅቱ ካፊያም ደመናም ነበሩ፤ ይሁንና ደመናውንም፣ ካፊያውንም፣ ጉሙንም እንዲሁም የደረጃዎቹን ብዛት ፈርቶ ጉዞውን ያቋረጠ ግን ያለ አይመስለኝም::

የዞኑ ምክር ቤት፣ የዞኑ አስተዳደርና ሕዝብ ከተለመደው የገቢ ምንጭ በመላቀቅ በራስ አቅም የመቆም እልህ የወለደው ይህን ተራራ ለቱሪስት መስህብነት የማዋልና የማልማት ቁርጠኝነት በተራራው ላይ 777 ደረጃዎችን በመገንባት የቱሪስት መስህብ ማድረግ አስችሏል::

የአምበርቾ ተራራ ኤኮቱሪዝም ስፍራና አረንጓዴ ልማት ፕሮጀክት ጽህፈት ቤት ስራ አስኪያጅ አቶ ዘመዴ ሄራሞ በስፍራው ለተገኙት ጎብኚዎች እንደተናገሩት፤ ተራራው በተፈጥሮ ሀብት የታደለ ነው:: 200 ሄክታር የሚጠጋ ጥብቅ የተፈጥሮ የቀርከሃ ደን፣ አቦ ሸማኔዎችና ሌሎች የዱር እንስሳት አሉት:: ከ350 የሚበልጡ ለመድሃኒትነት ሊውሉ የሚችሉ እጽዋትና ዋሻዎችም መገኛ ነው:: በእዚህ ላይ ባህላዊና ታሪካዊ ፋይዳዎችም አሉት::

አምበሪቾ እንዲለማ የተደረገው ወደ ቀደመው ማንነቱ መመለስ ያስፈልጋል የሚል አቋም ተይዞ፣ ቀደምት የከምባታ ሕዝቦች መጀመሪያ ያረፉበት ተራራ እንደመሆኑ ባህሉን፣ ታሪኩን፣ ቅርሱን በዚህ ላይ በመጨመር ጎብኚዎችን ይበልጥ በመሳብ ገቢ ማግኘት ይቻላል የሚል ሀሳብ ተጸንሶና ጥናት ተደርጎ ነው::

ለደረጃዎቹ ግንባታ አራት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ብር መውጣቱን አቶ ዘመዴ ጠቅሰው፣ በግንባታው አንድ ሺ ወጣቶች፣ የዞኑ ኢንጂነሮች በአጠቃላይ የዞኑ ምሁራን መሳተፋቸውን፣ ከዚህ ውጪ ሌላ የፋይናንስ ድጋፍ እንዳልተደረገበትም ተናግረዋል::

ፕሮጀክቱ ከመንግሥት ሀገራዊ እቅድ ጎን የሚሄድና አብዛኛዎቹ ስራዎችም ከጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ጋር እንደሚገናኙም ይጠቅሳሉ:: ዞኑ የባህልና ቱሪዝም መምሪያ እያለ ሌላ ቱሪዝምን የሚያለማ ተቋም አቋቁሞ እየሰራ መሆኑም ዞኑ ለቱሪዝም ዘርፉ የሰጠውን ትኩረት እንደሚያመልክት ይጠቅሳሉ::

የባህልና ቱሪዝም ጋዜጠኛውና የኢትዮ ቱሪዝም ሬዲዮ ፕሮግራም አዘጋጁ አቶ ዘርይሁን ግርማ በአምበርቾ ተራራ ላይ ደረጃዎች ከመገንባታቸው በፊትም፣ እየተካሄደ ባለበትና ከተጠናቀቀም በሁዋላ እየመጡ አይተውታል፤ ተራራውን በሚችሉት ሁሉ ለማስተዋወቅ መሞከራቸውንም ይገልጻሉ::

በቱሪዝም ጉዳዮች ላይም በማማከር ጭምር በግላቸው የሚሰሩት አቶ ዘርይሁን፣ ከቱሪዝም አኳያ በሀገራችን ብዙ ፕሮጀክቶች ይጀመራሉ፤ መሀል ላይ ግን ይቸገራሉ ሲሉ ይናገራሉ፣ እንደእነዚህ አይነት ፕሮጀክቶችን ደፍሮ መስራት ትልቅ ነገር መሆኑንም ይገልጻሉ:: በአሁኑ ወቅት ይህ ተራራ በሳምንት፣ በወር በብዙ ሰዎች እንደሚጎበኝም ጠቅሰው፣ የተራራው መልማት ለፕሮጀክቶች ጥሩ ምሳሌ እንደሚሆንም ይናገራሉ::

አቶ ዘርይሁን በአካባቢው ማህበረሰብ ተሳትፎ ላይ ብዙ መስራት እንዳለበትም ይጠቁማሉ:: እሳቸው እንዳሉት፤ ተራራው ላይ የሚታየው ተፈጥሮን ነው፤ ዓለም ላይ ባለው አሰራር /ትሬንድ/ በተፈጥሮ አካባቢ ቱሪዝም የሚለማው ማህበረሰብን መሰረት አድርጎ ነው፤ ለእዚህ አካባቢም ይህ ያስፈልገዋል::

የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ገበያ ባለሙያው አቶ ኢያሱ ሰለሞን፣ በቱሪዝም ዘርፍ ላይ ለ18 ዓመታት ሰርተዋል:: የአምበርቾ ተራራን ለማልማት ሲታሰብ ጀምሮ ያውቃሉ:: ቢሮው የቴክኒክ ድጋፍ ማድረጉን ይገልጻሉ:: ፕሮጀክቱን የዞኑ አስተዳደር የዞኑን ሕዝብ አስተባብሮ ሰራተኞች ከደሞዛቸው ቀንሰው፣ ማህበረሰቡ በጉልበቱ፣ በገንዘቡና ማቴሪያል በማቅረብ በደቦ ሥርዓቱ እየተቀባበለ እንደገነቡትም ነው የተናገሩት::

«ተራራውን እኛ መውጣት ከብዶናል፤ እነሱ ግን አሸዋና ሲሚንቶ ተሸክመው ወጥተዋል» በማለትም የሰራተኞቹን የዓላማ ጽናት ይናገራሉ:: ግንባታው በ2012 ግንቦት መጨረሻ ሲጀመር ዝናብ እንደነበር አስታወሰው፣ አሸዋው እየታጠበ ወደ ታች ይወርድ እንደነበርና እሱን ተሸክሞ በመውጣት መሰራቱን ይገልጻሉ:: በዚህም የከንባታ ሕዝብ ኢትዮጵያውያን የጥንካሬ ተምሳሌት መሆናቸውን ያረጋገጡበት ነው ሲሉ ይናገራሉ::

እስከ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ አልፎ አልፎ የእግር ጉዞዎች ከመኖራቸው በቀር በተራራ ሀይኪንግ እንደሌለም



ገልጸው፣ እዚህ ተራራ ላይ ግን ምንም አይነት አደጋ ሊከተል በማይችል መልኩ መሰራቱን ይጠቁማሉ:: በዚህም የከንባታ ሕዝብ ለሀገሪቱ ቱሪዝም ገጸበረከት ሰጥቷል ነው ያሉት::

እሳቸው እንዳሉት፤ አሁን ፕሮጀክቱ እየተጠናቀቀ ነው:: ተራራው ያለበት 18 ሺ ሄክታር መሬት ተከልሏል፤ ተራራውም እያገገመ ነው፤ በክልሉ ምክር ቤት ደንብ ተዘጋጅቶ ጸድቋል፤ እሱን ተከትሎ በክልሉ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ የክፍያ መመሪያ ተዘጋጅቶለታል:: አምበሪቾ ግብይት ውስጥ በሚገባበት ሁኔታ ላይም ቀደም ሲል በማስተዋወቅ በኩል ተሰርቷል፤ በቅርቡ በጋዜጠኞችና በቱሪዝም ተዋንያን የቱሪስት መስህቡን የሚያስተዋውቅ ጉዞ መካሄዱም የዚህ አንድ አካል ነው::

አሁን ባለው ሁኔታ ገንዘብ መሰብሰብ ነው ያልቻልነው እንጂ መስህቡ ገበያ ውስጥ ገብቷል ሲሉ ነው አቶ ኢያሱ ያስታወቁት:: ክፍያ መሰብሰቡም በቅርቡ እውን እንደሚሆን ጠቁመው፣ በእዚህ ሁሉ ላይ የሚዲያው ተሳትፎ ከታከለበት የአምበሪቾ ተራራ በእርግጠኝነት ትልቅ የቱሪስት መዳረሻ ይሆናል ብለን እናምናለን፤ አጠቃላይ የሀገር ውስጥ ቱሪዝም የጉብኝት ባህልም በአምበርቾ ይቀየራል ብዬ አስባለሁ ሲሉ ተናግረዋል::

# አሸባሪው ሕወሓት ሰብአዊ ድጋፍን እንደመያዣ በመጠቀም የትግራይን ሕዝብ ለጦርነት እየማገደ ነው

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ ፡- አሸባሪው ሕወሓት ለሕዝብ ሲባል የሚደረጉ ሰብአዊ ድጋፎችን በመያዣነት በመጠቀም የትግራይን ሕዝብ ለማያምንበት ጦርነት ለመማገድ እንደሚጠቀምበት የትግራይ ተወላጆች ገለጹ፡፡ ሕወሓት በፋላ ከተማ 600 ኩንታል ሰንዴ ለወታደራዊ አገልግሎት አከማችቶ መገኘቱም ጠቁመዋል፡፡

ትግራይ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር አቶ መስፍን ደሳለኝ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት ፤ አሸባሪው ሕወሓት ፍትሃዊ ተጠቃሚነትን ባልተከተለ የግለሰቦችን ፍላጎት መሰረት በአደረገ አስተሳሰቦቹ የትግራይ ሕዝብን የኢኮኖሚ ጥገኛ በማድረግ በከፋ ጦርነት ውስጥ ከቷል፡፡

አሸባሪው ሕወሓት ረሃብን እንደ ፖለቲካ መሳሪያ በመጠቀም ከመንግሥት እና ከዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶች የሚሰጠውን ሰብዓዊ እርዳታ በመዝረፍ የትግራይ ሕዝብን የኢኮኖሚ ጥገኛ በማድረግ ወጣቱ በረሃብ ከመሞት ወታደር እንዲሆንለት እያስገደደ እንደሚገኝ የገለጹት አቶ መስፍን፤ ሕልውናውን ለማስከበር ለጥፋት ድርጊቱ ለአደራጀው ልዩ ኃይል ቅድሚያ በመስጠት የትግራይን ሕዝብ ለረሃብና ለሥነልቦና ጉዳት ዳርጓል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ መስፍን ገለጻ ፤ አሸባሪው ሕወሓት ፍላጎቱ ሕዝብን አዳምጦ የመፍትሄ አካል መሆን ሳይሆን ሕዝቡ ከሱ ሽርፍራፊ አግኝቶ የኢኮኖሚ ጥገኛው ሆኖ እንዲቀጥል ማድረግ ነው፡፡ ጠላቱን የትግራይ ሕዝብ ጠላት በማድረግ ብቻውን እንዳይሆን ሕዝብን ምሽግ የሚያደርግ የጥፋት ስብስብ ነው ብለዋል ፡፡

ዛሬ አሸባሪው ሕወሓት በፈጠረው ችግር የትግራይ ሕዝብ ለሰብዓዊ እና ሥነልቦናዊ ጉዳት ላይ ተዳርጓል ያሉት አቶ መስፍን፤ መንግሥት መድረስ በሚችልባቸው አካባቢዎች አፋጣኝ ድጋፍ ማድረግ አለበት ብለዋል፡፡ ዓለም አቀፍ ለጋሽ ህብረተሰብም መንግሥት የጀመረውን ስራ በማገዝ የትግራይ ሕዝብን ከመከራው እንዲያላቅቁ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የትግራይ ተወላጅ የሆኑት አቶ ማስረሻ ፍሰሃ በበኩላቸው አሸባሪው ሕወሓት የግራይን ሕዝብ ለረሃብና ለሞት ያጋለጠ የጥፋት ቡድን ነው ብለዋል፡፡ በነጻ አወጣሃለሁ ስም ከበረሃ ትግል ጀምሮ የትግራይ ወጣቶችን እየማገደ ራሱን ነጻ ለማውጣት እየተፍጨረጨረ ይገኛል ሲሉም አክለዋል፡፡

ተከበብክ ፣ ወራሪ እየመጣብህ ነው በሚል የውሸት ፕሮፓጋንዳ መሰረት ልማቶችን በማፍረስ ትግራይ ሕዝብን ከሌሎች ኢትዮጵያዊ ወንድሞቹ እንዳይገናኙ በማድረግ መሰረተ ልማት ተጠቃሚ እንዳይሆን አድርገዋል፡፡

እንደ አቶ ማስረሻ ገለጻ ፤ መንግሥት በተናጥል ጦርነት በማቆም ፣ በሰላማዊ ስምምነት ለመፍጠር በሩን ክፍት ቢያደርግም በጦርነት አማራጭ የትግራይ ሕዝብን ለዘመናት ስቃይ ዳርጓል፡፡ ከለጋሽ ድርጅቶች የሚገኙ ሰብዓዊ እርዳታዎችን ከተራበው ሕዝብ ጉሮሮ ዘርፎ ራሱን ለማዳን ለአደራጀው ልዩ ኃይል ቀለብ በማድረግ በሕዝቡ ስም እየነገደ መሆኑን ማሳያ ነው ፡፡

ዓለምአቀፉ ሕብረተሰብም በመንግሥት በኩል ለተራበው ሕዝብ በፍጥነት ድጋፍ እንዲያደርጉ ጠይቀው በተቃራኒው ሀገራዊ ሉዓላዊነትን በመዳፈር አሸባሪውን ለማገዝ እጃቸውን በኢትዮጵያ ላይ መጫን የሚፈልጉ ኃይሎች እጃቸውን እንዲያነሱ አሳስበዋል፡፡

የፋላ ከተማ ነዋሪ የሆኑት ቄስ ስዩም ወልዱ በበኩላቸው እንደገለጹት ሕወሓት በትግራይ ሕዝብ እየለመነ የተገኘውን ሰብዓዊ እርዳታ ለወታደራዊ አገልግሎት በማዋል ሕዝቡ በረሃብ እንዲጎዳ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

የከተማዋ ነዋሪዎች ለከፋ ረሃብ ታጋልጠው ባሉበት ወቅት ሕወሓት ለወታደራዊ አገልግሎት ለማዋል 600 ኩንታል ሰንዴ በመጋዝን ውስጥ አከማችቶ ተገኝቷ የሚሉት ቄስ ስዩም፤ ቡድኑ በዓለምአቀፍ ህብረተሰብ እና በመንግሥት የሚደረጉ ድጋፎችን በመዝረፍ ለወታደራዊ አገልግሎት በማዋል ላይ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡ ቡድኑ ከኢሰብዓዊ ድርጊቱ እንዲቆጠብ ዓለም አቀፍ ሕብረተሰብ እና መንግሥት አስፈላጊውን ድጋፍ በፍጥነት እንዲያደርግም ጥሪ አቅርበዋል፡፡



ቄስ ስዩም ወልዱ



ፎቶ - በሃዲስ አብርሃ

# የገቢ ግብር ዕድገት ሀገሪቷ ራሷን ለመቻል ትክክለኛ መስመር ላይ መሆኗን የሚያረጋግጥ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የገቢ ግብር አፈፃፀም ዕድገት ሀገሪቷ ራሷን ለመቻል ትክክለኛ መስመር ላይ መሆኗን የሚያረጋግጥ መሆኑን የኢፌዴሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ገለጹ፡፡

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ባለፈው ሳምንት በታማኝነት ግብራቸውን ለከፈሉ ከፍተኛ ግብር ከፋዮች በተሰጠው የእውቅና ሥነሥርዓት ላይ እንደገለጹት፤ በታማኝነት ግብራቸውን የከፈሉ ተሸላሚዎች ብዛት ከዓመት ወደ ዓመት መጨመሩ የግብር ከፋዩ የሕግ ተገዢነት ማደጉን እና አስተማማኝ የልማት የገቢ ምንጭ የተገነባ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም በጥቅሉ ኢትዮጵያ ራሷን የመቻል ትክክለኛ መስመር ላይ መሆኗን የሚያረጋግጥ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በ2014 በጀት ዓመት የፌዴራል የገቢ ግብር አፈፃፀም 336 ቢሊዮን ብር የተሰበሰበ ሲሆን ይህም ከዕቅዱ 93 በመቶ መሳካቱን የሚሳይ ነው፡፡ ከ2013 በጀት ዓመት አፈፃፀም ጋር ሲነፃፀር ደግሞ የ20 በመቶ ዕድገት አሳይቷል፡፡

ፕሬዚዳንቷ፣ የገቢው ዕድገት እየጨመረ መምጣቱ የሚያበረታታ እና ሀገሪቷ በትክክለኛ መስመር ላይ እንዳለች የሚጠቁም መሆኑን የገለጹት ፕሬዚዳንቷ፤ ሆኖም ዕያደገ ለመጣው የሕዝብ የልማት ፍላጎት ተገቢውን መልስ ለመስጠት መንግሥትና ግብር ከፋዩ ተባብሮ ከኢኮኖሚው ተመጣጣኝ ገቢ መሰብሰብ ይገባል ብለዋል፡፡

የግብር ከፋዮች ቁጥር እና ከግብር የሚሰበሰበው ገቢ ከፍ እያለ መምጣቱን የጠቆሙት ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ፤ በግብር አሰባሰብ የታየው ዕድገት ጥሩ ቢሆንም ከኢትዮጵያ ብቻ በምናመነጨው ገቢ የሀገሪቱን ልማት ለማሳደግ አሁንም ገና ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ግብር ከፋዩ የሚጠበቅበትን የግብር ግዴታ መወጣት በማንኛውም ጊዜና ቦታ የመጀመሪያ ምርጫ መሆኑ መዘንጋት የለበትም ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ በመንግሥት በኩልም ነጋዴውን ግብር ለመክፈል የሚያበረታቱ ሥርዓቶች መዘርጋት እንዳለበት እና ግብር ከፋዩ ግብሩን ያለምንም ውጣ ውረድ መክፈል የሚያስችሉ ሁኔታዎች ሊኖሩ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

ፕሬዚዳንቷ እንደገለጹት፤ ግብር በወቅቱ እና በትክክለኛ መንገድ መክፈል ከማንኛውም የሚሠራ እና የሚያመርት ዜጋ የሚጠበቅ ግዴታ ነው፡፡ ይህንን ግዴታ የተወጣ ዜጋ ነው መብቱን ከመንግሥት ሊጠይቅ የሚችለው፡፡

ማንኛውም ሀገር እንዲመራ በሕዝብ የተመረጠ መንግሥት የሚመራትን ሀገር ኢኮኖሚ ለማሳደግ እና ለማልማት መሰረታዊ ለሆኑ ማህበራዊ ዕቅዶች፣ ለመንግሥት ኢንቨስትመንቶች አገሪቱን ለመጠበቅ አስፈላጊ እና አስተማማኝ የሆነ የገቢ ምንጭ ይሻል ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ ይህ ገቢ በዋናት ከግብር የሚገኝ እንደሆነና በቀላሉ ሊገመት የሚችል አለመሆኑን ጠቁመዋል፡፡

በተለይ አንድ ሀገር በጦርነት ውስጥ ስትሆን ከፍተኛ የራሷ ገቢ እንደሚያስፈልጋትና ይህም ሊገኝ የሚችለው ከግብር እንደሆነ ፕሬዚዳንቷ ተናግረዋል፡፡

በሌላ በኩል በጦርነት ወቅት የሚገባቸውን ግብር ሳይደብቁ እየከፈሉ ያሉ እንዳሉ ሁሉ በአንፃሩ ሁኔታውን ከለላ በማድረግ የተጎዱ ሰዎችን ሰቆቃ ሳይቀር በመጠቀም ለመክበር ሲሞከር እና ሙስና ሲስፋፋ እንደሚታይ ጠቅሰው ሀገር የምትገነባው ወገኔ ይማር፤ ጤናው ይጠበቅ፤ መንገድ ይሠራለት ውሃ ይግባለት ብሎ በሚያስብ አእምሮ ግብር ከፍሎ ግዴታውን በሚወጣው ማህበረሰብ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በአንፃሩ ደግሞ ሀገራችን በተፈተነችበት ጊዜ በአቋራጭ ለመክበር፤ በሕገ ወጥ መንገድ ሀብት የሚያሸሽ፣ ንብረቱን በአግባቡ የማያስመዘግብ የዕናት ቤት ሲጎዳ ለመዝረፍ የሚሮጥ መኖሩ የሚዘነጋ አለመሆኑን በመግለጽም ሕግን መሰረት በማድረግ አስፈላጊው እርምጃ መሰድ እንደሚጀመር ጠቁመዋል፡፡

# ድርጅቱ ያካሄዳቸው ማሻሻያዎች የአገልግሎት አሰጣጡ እንዲሻሻል አድርጓል

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ተግባራዊ ያደረጋቸው አዳዲስ ማሻሻያዎች አገልግሎት አሰጣጡን በማሳደግ ከነበረበት ደረጃ ከፍ እንዲል እንዳስቻሉት ተጠቆመ፡፡ በአፍሪካ ከሚገኙ ኦፕሬተሮችም ስምንተኛ ደረጃ ላይ ለመቀመጥ ችሏል፡፡

የኢትዮጵያ ፖስታ አገልግሎት ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚዋ ወይዘሮ ሃና አርአያስላሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ድርጅቱ ባካሄዳቸው ማሻሻያዎች የአገልግሎት አሰጣጡን ከነበረበት ደረጃ ከፍ ማድረግ ችሏል፡፡

ዋና መለኪያው በሆነው የመልእክት ደህንነትና ፈጣን አገልግሎት በ2020 ከ168 አገሮች 117ኛ ደረጃ ላይና በ2012 ዓ.ም 34 ሚሊዮን ብር ኪሳራ ገጥሞት ደመወዝ መክፈል ተቸግሮ እንደነበር አስታውሰዋል፡፡

ድርጅቱ ማሻሻያዎችን በማድረጉ በ2013 ዓ.ም መጨረሻ ከታክስ በፊት 72 ሚሊዮን ብር ትርፍ ማግኘት መቻሉንም አስታውሰዋል፡፡ በአፍሪካ ካሉ ኦፕሬተሮች ስምንተኛ ላይ እንደሚገኝም ነው የገለጹት፡፡

በአገልግሎት አሰጣጡ ከፍተኛ ክትትል መደረጉ፣ ከአገር ውስጥና የውጭ አጓጓዦች ጋር የተሻለ ተግባቦት መፈጠሩ፣ ለሰራተኞች አፈጻጸምን መሰረት ያደረገ የማበረታቻ ክፍያ መደረጉና ለተሻለ ፈጻሚ እውቅና መሰጠት መጀመሩ አፈጻጸሙን ለማሳደግ እንዳገዘም ነው የተናገሩት፡፡

አገልግሎት አሰጣጡን ማሻሻል የቻለባቸውን መንገዶች ተሞክሮ ለማጋራት መመረጡንም ነው የተናገሩት፡፡ ከ1900 ጀምሮ የዓለም ፖስታ ሕብረት አባል ሆኖ በመቆየቱ በተለይ የመልእክት ደህንነትና ፍጥነት ላይ ዋና መለኪያው የዓለም ፖስታ ሕብረቱ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

በተጠናቀቀው በጀት 130 ሚሊዮን ብር ለማትረፍ አቅደን 187 ሚሊዮን ብር አትርፈናል፡፡ አሁን የተገኘውን ውጤት መነሻ በማድረግም በቀጣይ ለተሻለ አፈጻጸም እንሰራለን ሲሉም ወይዘሮ ሃና ገልጸዋል፡፡

በተለይ መልእክት የማድረስና የመመለስ ስራ ሙሉ በሙሉ በቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ደንበኞች በየትኛውም ቅርንጫፎች የላኩት መልእክት የደረሰበትን ሁኔታ መከታተል የምንችልበትን የቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት መዘርጋት ችለናል፡፡ አዳዲስ ለመስራት ከምናስባቸው አገልግሎቶች ጋር ሲነጻጸር አሁንም የተሻለ ቴክኖሎጂ ተግባራዊ ማድረግ ይኖርብናል ብለዋል፡፡

የቴክኖሎጂ ለውጡ ይሄንን ስራችንን በአግባቡና በፈጣን መልኩ እንድንሰራ አስችሎናል፡፡ ስለዚህ የቴክኖሎጂ መቀያየሩ ለፖስታ ዘርፉ በአንድ በኩል ፈተና ይዞ ቢመጣም፤ በሌላ መልኩ ግን በተለይ የእቃዎች



ፎቶ - በሃዲስ አብርሃ

ወይዘሮ ሃና አርአያስላሴ

ዝውውር ላይ በጣም ትልቅ እድል ይዞ መጥቷል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

እንደ ወይዘሮ ሃና ገለጻ፤ በተለይ ከሶስትና አራት ዓመታት በፊት ቅሬታ ይነሳባቸው የነበሩ ብዙ ዘርፎች ነበሩ፡፡ ለምሳሌ ከመልእክት ደህንነት ጋር ተያይዞ ሰፊ ችግሮች ነበሩ፡፡

በተለይ ባለፈው ዓመት የመልእክት ዝውውራችንን ማሻሻል ላይ ብዙ አሰራሮችን በመተግበራችን አጠቃላይ አገልግሎት አሰጣጣችንን አሻሽሎልናል፡፡ ከመልእክት መጥፋት እና መዘግየት ጋር የነበሩ ችግሮችን በከፍተኛ ደረጃ መፍታት ችለናል፡፡ ቅሬታዎች በጊዜው መፈታት የሚችሉበትን አግባብ መዘርጋት ችለናል ብለዋል፡፡

በ2012 ዓ.ም ከመልእክት ደህንነት ጋር የተያያዙ የጠፉና በጣም የዘገዩ 90 ጉዳዮች በአቤቱታ ቀርበው ነበር፡፡ በ2014 ዓ.ም በእኛ ቁጥጥር ስር ያሉና ችግር ያለባቸው አራት ጉዳዮች ብቻ ነበሩ፡፡ ስለዚህ ከፍተኛ ማሻሻያ ማድረጋችንን መመልከት ይቻላል፡፡ የደንበኞች ቅሬታ ሲመጣም ፈጥነን ምላሽ መስጠት ችለናል ብለዋል ወይዘሮ ሃና፡፡

የመልእክት ደህንነት ችግር ዓለም አቀፍም የአገር ውስጥም ላይ ነበረ፡፡ አሁንም ዜሮ በመቶ ላይ አድርሰናል ማለት አይደለም ብለዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ዘንድሮ ከጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር በቅርበት ስራ በመጀመራቸው የሚገቡ መልእክቶች ጊዜን በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሶላቸዋል፡፡ ፈጣን መልእክት አገልግሎትን ዓለም አቀፍ ወጪ መልእክት ለኢትዮጵያ አየር መንገድ እስኪያስረክቡ አምስት ቀን ይፈጅ የነበረውን ጊዜም ከአንድ ቀን ባነሰ ማስተናገድ ተችሏል፡፡

ዜና

# ሁሉም የፌዴራል ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን ሊጠቀሙ ነው

**ሞገስ ጸጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በቀጣዮቹ ሁለት ዓመታት ሁሉም የፌዴራል ተቋማት የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሥርዓትን ይጠቀማሉ ሲል የመንግሥት ግዥና ንብረት ባለሥልጣን አስታወቀ፡፡

የባለሥልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሲስተም ፕሮጀክት ማናጀር አቶ ታደሰ ከበደ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ እስካሁን ባለው ጊዜ ውስጥ በሲስተሙ ከ25 በላይ የሚሆኑ ጫረታዎች ወጥተዋል፡፡ በቀጣይ ሁለት ዓመታት የፌዴራል መስሪያ ቤቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሰራል፡፡

በቀጣይ ሥርዓቱን ወደ ክልሎች በማውረድ ይሰራል ያሉት አቶ ታደሰ፤ በ2015ና 2016 በጀት ዓመት መጨረሻ ድረስ ሁሉም የፌዴራል ተቋማት ጨረታዎችን የሚያወጡትና ግዥዎችን የሚያከናውኑት ሲስተሙን በመጠቀም ይሆናል ብለዋል፡፡ በዚህም እንደ አገር ያለውን የተበላሸ የግዥ ሥርዓት ማስተካከል እና የአገርንም ሀብት ከስርቆትና ከብክነት ማዳን ይቻላል ብለዋል፡፡

እንደ ማናጀሩ ገለጻ፤ በ2014 በጀት ዓመት ብቻ የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሲስተምን በመጠቀም 66 መስሪያ ቤቶች ዓመታዊ የግዥ እቅዳቸውን ይፋ አድርገዋል፡፡ እንዲሁም በ2014 በጀት ዓመት ሰባት መስሪያ ቤቶች ሃያ ሁለት ጨረታዎችን በኦንላይን ሲስተም አውጥተው ለተጫራቾች ክፍት አድርገዋል፡፡ በ2015 በጀት ዓመትም ከ85 በላይ እቅዶች በሲስተሙ ታቅደዋል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሲስተሙን እንዲጠቀም በጋራ እየሰራን ነው ያሉት አቶ ታደሰ፤ በየክልሎች ያሉ ተቋማትና ቢሮዎች በሙሉ ጨረታዎቻቸውን በኦንላይን በማውጣት ግዢአቸውን እንዲፈጽሙ ይደረጋል ሲሉም ጠቁመዋል፡፡

እንደ አቶ ታደሰ ማብራሪያ፤ የባለሥልጣኑ የኤሌክትሮኒክስ የመንግሥት ግዥ ሲስተም ተግባራዊ እንዳይሆን የንግዱ ማሕበረሰብ የኢንተርኔት አጠቃቀም አለማደግ አንድ ችግር ነው፡፡ በኦንላይን ሰነድ ማዘጋት፣ ቅሬታ ሲኖር ማቅረብና ውላቸውን በኦንላይን ማስተዳደር አለመቻላቸው ትልቅ ስጋት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

አቶ ታደሰ እንደተናገሩት፤ ይህን ስጋት ለመቅረፍ ከሚዲያዎች ጋር በጋራ በመስራት የአመለካከት ለውጥ እንዲመጣ እየተሰጣ ነው፡፡ ሲስተሙ አዲስ እየለማ ያለ በመሆኑ መስሪያ ቤቶች ያለመቀበልና ትኩረት አለመስጠት ሌላው ችግር መሆኑን ገልጸዋል፡፡ አንዳንድ ተቋማት ላይ የሚሰሩ የግዥ ባለሙያዎች ሲስተሙን የስራቸው አካል አለማድረግ ከሚስተዋሉ ችግሮች ውስጥ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የንግዱ ማሕበረሰብ የኦንላይን አጠቃቀም ክህሎታቸው አናሳ በመሆኑ ሲስተሙን ተጠቅሞ የመስራት ችግር ይኖራል፡፡ ነገር ግን ይህን ችግር ለመፍታትና በአጠቃቀሙ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖር የግንዛቤ ፈጠራ ስራ እየተሰራ ነው፤ እንዲሁም በኦንላይን በመጠቀም መጫረት እንዲችሉ ዶክመንት የማዘጋጀት ስራ እየተሰራ መሆኑን የፕሮጀክቱ ማናጀሩ ገልጸዋል፡፡

## ለኢትዮጵያ ሉዓላዊነትና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በሀገሩ ጉዳይ እንደማይደራደር ዛሬም በይፋ አስታውቋል።

ትናንት እና ከትናንት በስቲያ "ለኢትዮጵያ እቆማለሁ፤ ድምፄንም አሰማለሁ" በሚል መሪ ቃል በመላው ኢትዮጵያ ባሉ ከተሞች በተደረጉ ሰላማዊ ሰልፎች ሕዝባችን በሀገሩ ሉዓላዊነት እና ክብር እንደማይደራደር ድምፁን ከፍ አድርጎ አሰምቷል ብሏል አገልግቱ በመግለጫው።

አገልግሎቱ እንዳስታወቀው፤ በመላው የአገራችን ትልልቅ ከተሞች የኢትዮጵያ ሕዝብ ባደረገው ሰላማዊ ሰልፍ ሀገሩን ለማንም አሳልፎ እንደማይሰጥና ማንኛውንም የውጭ ጣልቃ ገብነት እንደማይቀበል ገልጿል። ይህ የሕዝብ ድምፅ በሚገባ ሊሰማ ይገባል።

እንደ መንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫ፤ ሕዝባችን ያሰማው ድምፅ የኢትዮጵያ ድምፅ ነው። ኢትዮጵያ በምንም መልኩ በውስጣዊ ጉዳይዋ ላይ ማንም ጣልቃ እንዲገባባት የማትፈልግ ሉዓላዊ ሀገር ናት። ኢትዮጵያውያን ዛሬም እንደ ትናንቱ በማንኛውም ሁኔታ በየትኛውም የውጭ ኃይል የሀገራቸው ሉዓላዊነት እንዳይደፈር ዘብ እንደሚቆሙ ዳግም አረጋግጠዋል፡፡

ሉዓላዊነታችን ይከበር፣ በሰብዓዊ መብት ስም ጣልቃ ገብነት ይቁም፣ የተልዕኮ ጦርነት ይብቃ፣ ወዘተ የሚሉ መልእክቶች በሰላማዊ ሰልፎቹ መንጸባረቃቸውን ያስታወሰው መግለጫው፤ በማንኛውም ሁኔታ ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያ እንደሚቆሙም አረጋግጠዋል ብሏል፡፡

አሸባሪው ሕወሓት ሀገራችን ላይ የከፈተውን ጦርነት ተከትሎ አንዳንድ ምዕራባውያን ተቋማት፣ ግለሰቦች እና ሚዲያዎች የሚያራምዱትን የተሳሳተ አቋም ሕዝባችን በመላው ሀገሪቱ ተቃውሟል። የትግራይ ሕዝብ ጥቅም እና ፍላጎት ከወገኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ውጪ በሕወሓት ሊከበር እንደማይችልም ሕዝባችን በይፋ ተናግሯል። መከላከያ ሠራዊታችን ለግዛት አንድነት እና ለሉዓላዊነታችን የሚያደርገውን ተጋድሎም ደግፏል ሲል የገለጸው የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት መግለጫ ድምጻቸውን ላሰሙ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ምስጋና አቅርቧል፡፡

## “በኢትዮጵያ የተጀመሩትን

ከ2 ኛው ገጽ የዞረ

በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የተጀመሩት ንግግሮች ሲጠናከሩና ሲቀጥሉ የታዩት የለውጥ ፍንጮች ያድጋሉ ያሉት አቶ ተስፋዬ፣ ያልነበሩት ለውጦችም ይመጣሉ፣ ዴሞክራሲና የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ሂደትና ተግባሩም አብሮ ያድጋል ብለዋል፡፡

አሁን እንደ ሀገርና ዜጋ መወያየት በመጀመራችን የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው አካላት በአንድ መድረክ ቁጭ ብለው መወያየትና መነጋገር ጀምረዋል ያሉት አቶ ተስፋዬ፣ አጥተነው የነበረውን ይህን ባህልና ተግባር ለማሳደግ በስለኢትዮጵያ መድረክ የምናደርጋቸው ውይይቶች በሁሉም ዘርፎች ተጠናክረው መቀጠል መቻል አለባቸው ሲሉም ተናግረዋል፡፡

አቶ ተስፋዬ እንደተናገሩት፤ ባደረግናቸው የንግግር፣ የውይይት፣ የመሰባሰብ መድረኮች ስለኢትዮጵያ እድገት፣ ልማት፣ ሰላም፣ የወደፊት አገራዊ አቅጣጫዎችና ሌሎችም ጉዳዮች መነጋገር ጀምረናል፣ ይህን ጅምር ማጠናከርና ማሳደጉ ኢትዮጵያ በአፍሪካና በዓለም ደረጃ የሁሉም በጎ ነገሮች መፍለቂያ እንድትሆን ያስችላታል፤ ስለዚህ ሁሉም ዜጋ በሁለንተናዊ አገራዊ ጉዳዮቻችን በሰከነ መንፈስ የመወያየት ልምዱን ሊያዳብር ይገባል፡፡

ሀገራዊ ለውጥ ለማመጣትም የምናደርጋቸው ንግግሮችን ማጠናከርና በቀጣይነት ማካሄድ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

በስለኢትዮጵያ መድረኮችም በሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በጋራ በመወያየታችን ከወዲሁ ጠንካራ ሃሳቦች እየተነሱ ነው፣ ይሄ እየወሰደን ያለው በአፍሪካ ምድር አንዲት ትልቅና ግዙፍ ሀገር ኢትዮጵያን ለመገንባት የልጆቿ አንድነትና በጋራ ጉዳዮች ላይ በጋራ መምከርን ለመለማመድ ትልቅ መነሻ ነው፤ ይህ ዘላቂ እንዲሆን የሁሉንም ትብብር ያሻል፡፡ ለጋራ ጉዳዮቻችን በአንድነት መቆምና የኢትዮጵያን አንድነቷንና ጥንካሬዋን ለማምጣት በሀገራችን ጉዳይ ተሰባስበን መነጋገር አለብን ብለዋል፡፡

አቶ ተስፋዬ አክለውም፣ ባለፉት በዓድዋና በሌሎች ትልልቅ ጦርነቶችና ሀገራዊ ጉዳዮችን ያለፍነው እንደነዚህ ዓይነት አንድነት፣ መሰባሰብ፣ መተባበር ስለነበረን ነው ያሉት አቶ ተስፋዬ፤ በሀገር ጉዳይ በጋራ መቆም መቻልን አሁንም ከመቼውም ጊዜ በላይ አጠናክረን በማስቀጠል ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካም ለችግሮች መፍትሔ መሆን መቻል አለብን ብለዋል፡፡

እነዚህ የምናደርጋቸው የስለኢትዮጵያ የመሰባሰብ፣ የመተባበር፣ በሀገራዊ ጉዳዮች በጋራ የመቆምና አንድነትን የማጠናከር ነገሮች ሲዳብሩ የጋራ እሴቶቻችንን ያጎለብቱልናል ሲሉም ተናግረዋል፡፡

ኢትዮጵያ ትልቅና ብዙ ታሪክ ያላት ሀገር ናት፣ እኛ በእሷ ልክ ትልቅ ነን ወይ? ወደ ኢትዮጵያ ትልቅነትስ ሄደናል ወይ? ብለን እራሳችንን መጠየቅ አለብን ብለዋል፡፡

ሀገራችን ለአፍሪካውያን እና ለሌሎች ነጻነትና ማሸነፍ የታገለች ሀገር ናት፣ የኢኮኖሚ እድገትና ነጻነት ለአፍሪካ ሀገራት እንዲመጣ ፈር የቀደደች ሀገርም ናት ያሉት አቶ ተስፋዬ፣ ኢትዮጵያ ወደዛ የከፍታ ማማ እንድትመጣ የሰከኑና ሀገርን ያስቀደሙ ውይይቶች ያስፈልጋሉ ብለዋል፣ የተጀመሩትን አጠናክሮ በማስቀጠል ኢትዮጵያውያን ቀድመን የጀመርነውን የአፍሪካን ነጻነትና እድገት ከዳር ለማድረስ በሁሉም ዜጋ ዘንድ በሁሉም ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ በሰከነ ሁኔታ ምክክሮች እና ውይይቶች መቀጠል እንዳለባቸውም አመላክተዋል፡፡

## ለኢትዮጵያ የብልጽግና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መሆኑን በመመልከታቸው አድናቆታቸውን ገልጸዋል።

በቀጣይ ዓመት በሩዝና የሻይ ቅጠል ምርት ከሀገር ውስጥ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያ ማቅረብ ይገባል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለኢትዮጵያ ብልጽግና ስኬት የተጀመሩ የልማት ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ብልጽግና የሚሳካው በዜጎች ጥረት፣ ባለን ምቹ የመልማት አቅምና የተፈጥሮ ሀብት ነው ሲሉም አብራርተዋል።

በቦንጋ ዩኒቨርሲቲ በአትክልትና ፍራፍሬ፣ በእንስሳት፣ በቡናና ሌሎች የግብርና ልማት ሥራዎች የተመለከቱት አስደናቂ ሥራ ለሌሎች ዩኒቨርሲቲዎችም ምሳሌ ይሆናል ብለዋል።

ሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የአካባቢያቸውን እምቅ አቅም በመረዳት ማልማት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል። በቀጣይ ዓመት ምርቶችን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በሚያስችል መልኩ ለማምረት ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ እንደሚገባ መግለጻቸውን ኢዜአ ዘግቧል።

## የውጭ ተፅዕኖ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሉዓላዊነታችን የሚዳፈር፤ የአገራችን ክብር የሚያዋርድ የውስጥም ሆነ የውጭ ጠላት በመጣ ጊዜ ሁሉ እኛ ኢትዮጵያውያን ሆ! ብለን በአንድነት በመቆም ድል እየተቀዳጀን እና አሸናፊ እየሆነ መምጣታችን ታሪክ ብቻ ሳይሆን የአሁኑ ትውልድም በተግባር እየሰራው የሚገኝ እውነት ነው ብለዋል ርዕሰ መስተዳድሩ።

አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በአማራና አፋር ላይ መጠነ ሰፊ ወረራ በማካሄድ ወገኖቻችንን የገደለ፣ አካል ያጎደለ፣ ሀብትና ንብረት የዘረፈና ያወደመ ወንጀለኛ እና አረመኔ ቡድን ነው። ይሁን እንጂ ከመላ ኢትዮጵያውያን ጋር ሁነን ባደረግነው ርብርብ ወረራውን በመቀልበስ ችለናል። አሁንም በጀግናው መከላከያ ሠራዊታችን እና ጥምር ኃይላችን ወያኔ ለሉዓላዊነታችንና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አንድነት ስጋት በማይሆንበት ደረጃ ለማድረስ በጀግንነት ወኔ ተጋድሎ እያደረገ ይገኛል።

ጦርነቱ የውክልና ጦርነት እንጂ ከወያኔ ጋር ብቻ የሚደረግ አይደለም ያሉት ዶክተር ይልቃል፤ የውክልና ጦርነት ለመሆኑ የአማራና የአፋር ሕዝብ ሲጠቃ፣ ሲገደል፣ ሲፈናቀል፣ ሀብትና ንብረቱ ሲዘረፍና ሲወረር ምንም ያልተነፈሱት ምዕራባውያን ኃይሎች ተልካሻ ምክንያት እያቀረቡ በኢትዮጵያ ላይ የሚያደርጉት የኢኮኖሚ፣ የዲፕሎማሲና የሚዲያ ጫና ማረጋገጫ ነው ብለዋል።

አንዳንድ ምዕራባውያን እና ታሪካዊ ጠላቶቻችን ለወያኔ እየሰጡት የሚገኘው የገንዘብ፣ የዲፕሎማሲ እና የሚዲያ ድጋፍ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት እና አንድነት የሚዳፈር በመሆኑ በጽኑ እናወግዘዋለን ብለዋል።

በኢትዮጵያ ላይ እያደረጉት ያለው ጫና፣ ወከባና ዛቻም ዓለምአቀፉን ሕግ፣ መርህና አሰራር የሚቃረን ነው። ከዚህ የተዛባ እና ከዓለም አቀፍ ሕግ ተቃራኒ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ አጥብቀን እንጠይቃለን ሲሉም አሳስበዋል።

የወያኔን መደገፍ ኢትዮጵያን ማዳከምና ማፍረስ፣ በወረራ ጥቃት በደረሰባቸው ወገኖቻችን ላይ መሳለቅ፣ አሸባሪና በሕዝቦች ላይ ግፍ የፈጸመ ዘረኛ፣ ወንጀለኛ ቡድንን መደገፍ ነው። በመሆኑም የአገራችን ሉዓላዊነት በማስከበር የውስጥ ችግር በውስጥ እንዲፈታ አንዳንድ የምዕራባውያን ኃይሎች ከጣልቃ ገብነት አሰራራችሁ በመቆጠብ የበኩላችሁን አስተዋጽኦ እንድታደርጉ እንጠይቃለን ብለዋል።

ዶክተር ይልቃል እንደተናገሩት፤ እኛ ኢትዮጵያውያን እንደተለመደው በጽናት እና በአርበኝነት ስሜት በአንድነት በመቆም የአገራችንን ሉዓላዊነት የምናስከበር ሕዝቦች እንጂ በፍርሃት፣ በተጽዕኖ ነጻነታችንን አሳልፈን ለማንም የማንሰጥ ለመሆኑ የቅኝ ግዛት የአርበኝነት ተጋድሏችን ምስክር ነው። አሁን ለገጠመን የውጭ ተጽዕኖ የማንበገር ለመሆኑ ከጫፍ እስከ ጫፍ የምናሰማው የአንድነት ድምጻችን ማረጋገጫ ነው።

በሌላ በኩል በአንድ አገር ውስጥ የሚፈጠር ችግር በራሱ በአገር ውስጥ ጉዳይ ታይቶ የሚፈታ መሆኑን በውል በመገንዘብ የውጭ ጣልቃገብነት ትክክል አለመሆኑንና ጣልቃ ገብነትን በማውገዝ የአገራችን ሉዓላዊነት እንድናስከብር ከጎናችን በመቆም ያልተቋረጠ ድጋፍ ለሚያደርጉልን ወዳጅ አገሮች፣ ድርጅቶች እና ግለሰቦች ምስጋና እናቀርባለን ሲሉም ገልጸዋል።

በመሆኑም ሉዓላዊነታችንን ማስከበር የይሁንታ ጉዳይ ሳይሆን ተፈጥሯዊ መብታችን በመሆኑ ሁልጊዜም እንደምናሸንፍ አልጠራጠርም። ሉዓላዊነታችንና አንድነታችን በውጭ ተጽእኖ እንዳይደናቀፍ የውጭ ዲፕሎማሲ ስራችን በሚገባ አውቀንና ለይተን ለመስራት መረባረብ ይገባናል ሲሉም አሳስበዋል።

የሉዓላዊነታችን መገለጫ የሆነውንና ጸረ ሕዝብ በሆኑ ኃይሎች ላይ እርምጃ እየወሰደ፣ የአርበኝነት ስሜት እየጎመራ እንዲሔድ፣ ሉዓላዊነታችንና አንድነታችን እየጠነከረ እንዲሔድ ደሙን እያፈሰሰ፤ አጥንቱን እየከሰከሰ ከሚገኘው ጦር ኃይላችን ጎን በመቆም የተለመደውን ድጋፋችንን እና ደጀንነታችን አጠናክረን እንቀጥል ሲሉም መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

ከዚህም ጎን ለጎን የውጭ ጣልቃ ገብነት ተጽዕኖን መቋቋም የምንችለው የውስጥ አንድነታችን የበለጠ በማጠናከር በመሆኑ በውስጥ ያሉ ልዩነቶችን ለጊዜው ወደጎን በመተው እጅ ለእጅ ተያይዘን የውጭ ጣልቃ ገብነትና ተጽእኖን በአርበኝነት ስሜት፤ ተደራጅተንና ተቀናጅተን፣ አንድ ሁነን ተጽእኖውን ለመቋቋም በአንድነት እንድንነሳ ጥሪ አቅርበዋል፡፡

ከዚህም ጎን ለጎን ጦርነቱን የሚሸከም ኢኮኖሚ ለመገንባት ሁላችንም በተሰለፍንበት ዘርፍ ሁሉ ውጤታማ ሁነን ልማትን እናፋጥን ብለዋል፡፡

በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የምኖር ኢትዮጵያውያን በአርበኝነት ስሜት በአንድነት በመነሳት የውጭ ተጽእኖን መቋቋም የሚያስችል የዲፕሎማሲ ስራ በተናበበና በተቀናጀ መንገድ ያለምንም መታከትና መዘናጋት እንስራ በማለት ጥሪ ያቀረቡት ዶክተር ይልቃል፤ የአገራችን ሉዓላዊነትንና አንድነት ለማስከበር በጀግንነት እየተፋለመ ለሚገኘው ጀግናው መከላከያ ሠራዊትና ጥምር ኃይላችን በራሴና በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ስም ያለኝን ታላቅ አክብሮት እና

# ርዕሰ አንቀፅ

## የኢትዮጵያ የውጭ ግንኙነት መርህ ለመተባበርና መከባበር ሁሌም ቅድሚያ የሚሰጥና ጣልቃ ገብነትን ፈጽሞ የማይቀበል ነው!

በሀገራት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባትን ትልቅ የፖለቲካ መሳሪያ አድርገው የሚጠቀሙ አንዳንድ የውጭ ኃይሎች ዓለምን ብዙ ዋጋ አስከፍለዋል፤ እያስከፈሉም ነው። እውነታው የሀገራቱ የእለት ተእለት የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከሆነም ዓመታት ተቆጥሯል ።

በአንድ በኩል ራሳቸውን የሰብአዊ መብት ተቆርቋሪና ተሟጋች አድርጎ በማቅረብ ፤ ይህንን የሚያስፈጽሙ ዓለም አቀፍ ተቋማትን በመፍጠርና በመደገፍ ፤ በሌላ በኩል የዴሞክራሲ ሀዋሪያ በመሆን በአገራት ውስጥ ግጭቶችን በመፍጠርና በማራገብ ተጠቃሚ ለመሆን እየሰሩ ነው ።

ከዚህም በላይ በግልፅ ብሔራዊ ጥቅማችንን ለማስከበር በሚል የእነርሱን ዓላማ የሚሸከሙ ቡድኖችን በመፍጠር ፤ ሎጅስቲክን ጨምሮ በማንኛውም ሁኔታ አቅማቸውን የሚያጎለብቱ ድጋፎችን በመስጠት የአገራቱ ህዝቦች በቅጥረኞች /ባንዳዎች /ያልተገባ መከራና ስቃይ እንዲያዩ አድርገዋል እያደረጉም ነው።

በአንድ ወቅት የተሻለ ሰላም ፤ የኢኮኖሚ ዕድገትና ዓለም አቀፍ ተቀባይነት የነበራቸው ኢራቅ ፣ ሶሪያ እና ሊቢያን በፀደይ አብዮት ማግስት በዴሞክራሲና በነጻነት ስም ወደ አላሰቡት እና አልገመቱት አስከፊ ችግር እንዲገቡ አድርገዋቸው እስከዛሬም የዚሁ ችግር ገፈት ቀማሽ ሆነዋል።

"ስለ እናንተ ከኛ በላይ የሚያውቅላችሁ የለም" በሚል ዜማ የተጀመረው ይህ የጣልቃ ገቦች ሆይሆይታ በተጨባጭ እንደተባለው ለሀገራቱ ሕዝቦች የተሻሉ ቀናቶችን አላመጣም ከዛ ይልቅ ፤ የሀገራቱን ሕዝቦች ለሞት፣ ለስደትና ለከፋ ማህበራዊ ምስቅልቅል ከመዳረጉም በላይ የትልቅ ታሪክ እና ሕዝብ ባለቤት የነበሩትን አገራት አንገት ያስደፋ ክስተት ሆኖ አልፏል።

ይህ በ"እኛ እናውቅልሃለን "ስብከት ተጀምሮ፤ በዓለምአቀፍ ጫና የቀጠለው የአንዳንድ ምዕራባውያን የፖለቲካ አካሄድ ዛሬም ከትናንት የስህተት መንገዱ የሚመልሰው አጥቶ ለዓለም ሰላም ጠንቅ እንደሆነ ይገኛል። በተለይም ራሳቸውን በማወቅ እጣ ፈንታቸውን በራሳቸው ለመወሰን ለሚተጉ ሕዝቦች ዋነኛ ተግዳሮት ሆኗል።

በቀደመው የቅኝ ግዛት ዘመን አፍሪካውያንን ጨምሮ በመላው ዓለም የሚገኙ ጥቁር ሕዝቦችን ከፍያለ ዋጋ ያስከፈለው ይህ አስተሳሰብ፤ ሕዝቦች የራሳቸውን ዕድል በራሳቸው የመወሰን ፍጥረታዊ መብት ባለቤት እንደሆኑ በስፋት በሚደሰኮርበት ዓለም ከቋንቋ ያለፈ ስፍራ እንዳያገኝ አድርጎታል።

አገራቱ በፍላጎታቸው የፈጠራቸው ተቋማት፤ በራሳቸው የልቦና መዋቅር የቀረጿቸው ምሁራኖቻቸው ፤ የገንዘብና የቴክኖሎጂ አቅም ተዳምረው በራሳቸው መንገድ ለማደግና ካሉበት ጭለማ ለመውጣት የሚዳክሩ ተስፈኛ ሀገራት ስለተስፋቸው ያልተገባ ዋጋ እንዲከፍሉ እያደረጓቸው ይገኛሉ። ይህ በሰብአዊነትና በሰብአዊ እሴቶች ስም የሚደረግ የተስፋ ማጨናገፍ ዘመቻ አሁን ላይ ሊቆም ይገባል።

በተለይም በዚህ ወቅት ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን እጣ ፈንታ በራሳቸው ለመወሰን እየሄዱበት ያለውን አዲስ የታሪክ ገጽ ለመዝጋት በአንዳንድ የውጭ አገራት እየተካሄደ ያለው ዘመቻ ፤ በኢትዮጵያውያን ላይ ብቻ ሳይሆን በተመሳሳይ መንገድ ነገ ላይ እጣ ፈንታቸውን ለመወሰን የሚነሱ ሕዝቦችን የሚመለከት ነው።

ኢትዮጵያውያን በቀደሙት ዘመናት ያለፉባቸው የታሪክ ልሳኖቻቸው እንደሚመሰክሩትና እንደሚያስረዱት፤ ለተነሱለት ዓላማ ዋጋ የመክፈል ትልቅ አቅምና ቁርጠኝነት ያላቸው ሕዝቦች ናቸው። ዋጋ በመክፈል የታሪክ ገጾቻቸውን በደማቅ ቀለም ያቀለሙ ሕዝቦችም ናቸው።

በቀደመው ዘመን /በቅኝ ግዛት ዘመን / ቅኝ ገዥዎች "ስለ እናንተ ከእኛ በላይ የሚያውቅላችሁ የለም" በሚል የመጡበትን የሽፍጥ መንገድ በምን ያህል መስዋእትነት ማስቆም እንደቻለ ፤ ይህም የዛሬው ማንነቱ እሴት ሆኖ አንገቱን ቀና አድርጎ እንዲሄድ እንዳስቻለው የአደባባይ ሚስጥር ነው።

ዛሬም ቢሆን ራሱን ሆኖ ለመገኘት እያደረገ ባለው እልህ አስጨራሽ ትግል እየከፈለ ያለው ዋጋ የቱንም ያህል ከፍ ያለ ቢሆንም ፤ የመስዋእትነቱ ፍሬ ግን መጪው ትውልድ የተሻለ ነገዎች እንዲኖሩት ከማስቻል ባለፈ ራሱን ለተጨማሪ ታሪክ ሰሪነት የሚያበቃው አቅም ፈጣሪ እንደሚሆን ይታመናል።


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።**

## ከአገሬ እውነት ጎን እቆማለሁ!

**በእምነት**

ኢትዮጵያ በረጅም የታሪክ ሂደቷ ውስጥ በርካታ ኩነቶችን ያለፈች አገር ናት። እስከ ዛሬዋ እለት ድረስም ቢሆን ጥላቶቿ እንዲሁም ወዳጅ መሰል ምቀኞቿ የተኙላት አገር አይደለችም። አልተሳካም እንጂ ኢትዮጵያን በቅኝ ግዛት ለመያዝ ያልተሞከረ ነገር ያልተወጣበት ዳገት የለም ቢባል ማጋነን አይሆንም። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ተሞክሮ ከሽፏል። እነዚህ በኢትዮጵያ የሚጎመጁ አገራት ሙከራቸውን የሚደርጉት ደግሞ ሁሌም የውስጥ ባንዳዎችን በመጠቀም ነው።

"የእናት ሆድ ዥንጉርጉር" እንደሚባለው ይህች ታላቅ አገር እጅግ ጥቂት ማፈሪያ ባንዳ ልጆች ስላሏትም ያልተሳኩም ቢሆኑ ብዙ የእጅ አዙር ቅኝ ግዛቶች ሙከራ ተደርጎባታል። ነገር ግን ጥቂት ባንዳ ልጆች ቢኖሯትም መላው በሚባል ደረጃ ያለው ህዝብ ግን ይጠብቃታል፤ ይሞትላታልም። ሁሌም ህዝብ አሸናፊ በመሆኑ ኢትዮጵያ ከነ ክብሯ እዚህ ደርሳለች።

በተመሳሳይ በውስጥ ጉዳዮቿ ሳይቀር የውጭ ጣልቃ ገብነቱ አንዴ ሞቅ ሌላ ጊዜ ቀዝቀዝ ሲል ይታያል፤ ይኸው ድርጊት አሁን ድረስ ቀጥሏል። ጣልቃ ገብነቱ ሁለት መልክ ያለው ሲሆን፤ የመጀመሪያው በቀጥታ የሚከናወን ነው። ለአብነትም የጣልያንን ወረራ ተከትሎ ምዕራባውያን አገራት በግልጽ ኢትዮጵያ ላይ ያደረጉት ጣልቃ ገብነት ተጠቃሽ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚደረግ ጣልቃ ገብነት ሲሆን እንደ የዓለም ገንዘብ ድርጅት፣ የዓለም ባንክ እንዲሁም ዓለም አቀፍ ረድኤት ድርጅቶችንና ሚዲያዎችን የመሳሰሉ ተቋማትን በመጠቀም የሚደረገው ጣልቃ ገብነት ነው።

በኢትዮጵያ አሁን ያለው ጣልቃ ገብነት ደግሞ ሁለቱንም አካሄዶች የተከተለ ነው። የአሜሪካ መንግስት ከዚህ ቀደም ለግብጽ በይፋ በመወገን ሁኔታ የኢትዮጵያን በአባይ ወንዝ የመጠቀም ፍትሃዊና ተፈጥሯዊ መብት ለመንፈግ ሞክሯል። "የአፍሪካን ችግሮች በአፍሪካውያን" የሚል መርህ ያለውንና በአፍሪካ አገራት ሙሉ ተሳትፎ የተቋቋመውን የአፍሪካ ህብረት ስልጣን ወደ ጎን በመተው ፍርደ ገምድል ውሳኔዎችንም ሲያሳልፍ አይተናል።

ይህ አልሳካ ሲል ደግሞ አሸባሪነትን ለማጥፋት ቀዳሚ ነኝ የሚሉት ምዕራባውያን የራሱን አገር መከላከያ በክህደት ያጠቃውን አሸባሪውን የትህነግ ቡድን ወደ ስልጣን ለመመለስ የሚችሉትን ሁሉ እያደረጉ ይገኛሉ። ለጦርነቱ ተጎጂዎች መሰጠት ያለበት ምግብና መድኃኒት ለሽብር ቡድኑ አባላት ሲያከፋፍልና ሲጠቀምበት ከማየት በላይ የሚያሳዝን ነገር ባይኖርም ይህንን እውነት ግን በአደባባይ ከማውገዝ ይልቅ አሸባሪን በመደገፍ እውነትን ለመደፍጠጥ ሲሞክሩ ነው የተስተዋለው።

የዴሞክራሲና ሰብዓዊ መብቶች ጠበቃ ነን የሚሉት የውጭ ኃይሎች እነዚህን ምክንያቶቻቸውን ሰበብ አድርገው የገቡባቸው አገራት ሁሉ ወደ ፍርስራሽነት ሲቀየሩ ዓለም አይቷል። ኢራቅ፣ አፍጋኒስታን፣ ሶማሊያ፣ ሊቢያና የመሳሰሉት አገራት ዜጎች የሰላም አየር መተንፈስ ቅንጦት ሆኖባቸዋል።

የቀውስ ፖለቲካ ነጋዴዎቹ እሳት ጭረው የመሳሪያ ገበያቸውን ያደራሉ፣ አዳዲስ የጦር መሳሪያዎቻቸውን ይሞክራሉ፣ የሃብት ምዝበራቸውንም ያጧጡፋሉ። ይህ በኢትዮጵያ ምድር ሊሳካ የሚችል ጉዳይ እንዳልሆነ ልጆቿ እያረጋገጡ ነው። ወደፊትም ያረጋግጣሉ።

በእልቂት ደጋሾቹ ከጥንስሱ ጀምሮ የሚከናወነው ሴራ ከተቻለ ኢትዮጵያን ለማፍረስ ካልተቻለ እንደ ትህነግ ያለ ተላላኪ መንግስት ኢትዮጵያ ላይ መመስረት የሚል ዓላማ እንዳለው የኢትዮጵያ ህዝብ ጠንቅቆ አውቋል። ለዚህም ነው የሚመጣውን የውጭ ጫና በአንድነት ሲመክት የቆየው፤ አሁንም እየመከተ የሚገኘው።

ይህ አንድነቱ ዛሬም በሁሉም አቅጣጫ መጠናከሩ ለኛ እጅግ የሚያስደስት ለጠላት ደግሞ ሴራው እየከሸፈ መሆኑን የሚያሳይ መሆኑን ደግሞ በኢትዮጵያ ላይ ቀጥተኛና የእጅ አዙር ጫና እያሳደሩ ያሉ ምዕራባውያን ሁሉ ሊረዱት ወደቀልባቸው ተመልሰውም የአገሬን እውነት ሊያውቁና ሊቀበሉ ብሎም በዛው ልክ ቆመንለታል ለሚሉት ዴሞክራሲና ፍትህ ታማኝ ሊሆኑ ይገባል።

ኢትዮጵያ ረጅም የመንግስትነት ታሪክ ያላት አገር ከመሆኗም በላይ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ምስረታና በአፍሪካ ህብረት መመስረት ላይ ከተቀሩት የአፍሪካ አገራት በተሻለ መልኩ የላቀ ሚናዋን የተወጣች አገር መሆኗን የሚስተው አለ ብዬ አላምንም። ይህ መሆኑ ደግሞ በተለይም ሰላምና ፍትህ ለራቃቸው አገራት ቀድማ የምትደርስ አቅሟን ተጠቅማም ድምጽ የምትሆን አገር መሆኗም የሚካድ አይደለም፤ አሁንም በገሀድ የሚታይ ሀቅ በመሆኑ ።

ታዲያ እነዚህ ምዕራባውያን በራሳቸው ጥቅም ላይ ማንም እንዲመጣ እንደማይፈልጉት ሁሉ ለምን በሌሎች ጥቅም ላይ ይረማመዳሉ የሚለው የሁልጊዜም ጥያቄዬ ነው፤ ይህን ጥያቄ መመለስ ደግሞ እጅግ በጣም አስፈላጊም ይመስለኛል። በተለይም የዴሞክራሲ አባት እናት ነን፤ የሽብርተኞች መድኃኒት ነን ብለው በሚያወሩት ምዕራባውያን ዘንድ።

የኢትዮጵያ ህዝብም አገሩን ከጠላት ለመጠበቅ ዘብ ቆሟል። የህዝቡ ግልጽ መልዕክትም በምዕራባውያን ሴራ ኢትዮጵያ መቼም አትፈርስም! ሁሌም ሁላችንም ከአገራችን እውነት ጎን እንቆማለን የሚል ሊሆን ይገባል።

ሁሉም ወገን በውጭም በውስጥም ያለው ኢትዮጵያዊ አገሩ ከያዘችው እውነት ጎን መሰለፍ አሁን ላይ የውዴታ ግዴታው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በዓለም አደባባይ ብሎም በአገራችን ዜጎች ከያሉበት ተሰባስበው ድምጻቸውን ለዓለም ማህበረሰብ ለማሰማት እውነታችንን ለማስረዳት የጀመሩት መንገድ እጅግ ጥሩ ከመሆኑም በላይ ኢትዮጵያ ሁሌም በልጆቿ ታፍራና ተከብራ እንዲሁም ድል አድርጋ እንደምትኖር ማሳያ ይመስለኛል። ሁላችንም በአንድነት ከአገራችን እውነት ጎን የምንቆምበት ጊዜው ደግሞ አሁን ነው።

'ለኢትዮጵያ እቆማለሁ ድምጼን አሰማለሁ' በሚል መሪ ሃሳብ ሊካሄድ የታቀደው ሰላማዊ ሰልፍ ላይም በመሳተፍ ኢትዮጵያ ከያዘችው እውነት ጎን በመቆም ከአሸባሪው የትህነግ ቡድን ጋር በመወገን ኢትዮጵያ ላይ ተጽእኖ ለማሳደር የሚጥሩ አካላትን ማሳፈር በመሆኑ እንደ ዜጋ የሚጠበቅብንን ለማድረግ መዘጋጀት ይገባል።

መንግስት የኢትዮጵያን የግዛት አንድነት ለማስጠበቅና ሉአላዊነቷን ለማረጋገጥ የሄደበትን ርቀት ማድነቅ እንዲሁም መደገፍ ኢትዮጵያን መደገፍ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልገናል።

የትህነግ የሽብር ቡድን ህልውናውን ለማቆየት ሲል የትግራይ ሕዝብን ለከፋ ችግር እየዳረገ በመሆኑም ይህ ግፍና መከራ በግልጽ እንዲታወቅ፤ ግፍና መከራውን ወደ ጎን በመተው ኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ጫና የሚፈጥሩ አካላት በቃችሁ ለማለትም ከዚህ የተሻለ ጊዜ ይኖራል ብዬ አላስብም። ከዚህ ባለፈ የውጭ ኃይሎችን ጣልቃ ገብነት ማውገዝ እና ከኢትዮጵያ ጎን የቆሙ አገራትን ማመስገን ኢትዮጵያዊ ባህላችን ያስተማረን ጨዋው የእኛ ስነ ምግባር ነው።

ኢትዮጵያውያን ይህንን በሉዓላዊነት ላይ የተጋረጠ መልከ ብዙ ጫና በጋራ ቆመን መመከት ካልቻልን በተመሳሳይ የኢትዮጵያን የግዛት አንድነትን ለማስጠበቅ መንግስት እያደረገ ያለውን ጥረት መደገፍ ከተሳነን እውነት የአባቶቻችንን አደራ በሊታ ሆነን በታሪክ መዝገብ የምንሰፍር ትውልዶች እንሆናለን። አበቃሁ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## “ሙያውን ማወቅ ለሚፈልግ ሰው ደራሽ መሆን እፈልጋለሁ”

### -ሜካፕ አርቲስት ሰዓዳ አበበ

**ተገኝ ብሩ**

ልጅ ሆና ጥልቅ የሆነ የኪነጥበብ ፍቅር ነበራት:: ትምህርት ቤት ሳለች በኪነጥበብ ክበቦች ንቁ ተሳታፊ ነበረች:: የኪነጥበብ ፍቅር ሙያዊ ጉዳዮችን ለመመልከትና ወደወደደችው አንድ ሙያ ለመሳብ ምክንያት ሆኗታል:: ይህም በሆሊውድ የሚቀርቡ የተለያየ ዘውግ ያላቸው ፊልሞችን መከታተል ልማዷ እንዲሆን አድርጓል። ይህ ደግሞ አንድ ነገር ላይ ልቧን አሳረፈው። በፊልሞቹ ውስጥ የሚታዩ የሜካፕ ስራዎች:: በምታያቸው ፊልሞች ላይ በሜካፕ ስራዎች መማረክና እሷም ያንን የሜካፕ ሙያ የማወቅ ጥረት አሳደረባት። የሜካፕ ባለሙያዋ ሰዓዳ አበበ::

በፊልሞች ላይ ገጸ ባህሪያት የሌላ ሰው መልክ አልያም የሚፈለገውን ገጸ ባህሪ የማስመሰል የሜካፕ ጥበብ (prosthetic makeup) በተለየ ይማርካትና ስራው ምን እንደሆነ መመርመር ጀመረች:: እዚያ ውስጥ የምታያቸው የሜካፕ ጥበቦችን በተለያየ መንገድ መማርም ስራዋ ሆነ::

ይህ ሙያው ላይ ከፍተኛ ፍላጎት አሳደረባትና በራሷ እንድትሞክር መንገድ ሆናት:: ቤት ውስጥ የተለያዩ የመዋቢያ ቁሳቁሶችን በመጠቀም በራሷና አቅራቢያዋ ባሉ ቤተሰቦቿ ላይ መስራት ጀመረች:: ቤተሰቦቿም የምትሰራውን አይተው ሲያደንቁላት ደግሞ የበለጠ መነሳሳት ተፈጠረባት:: ገንዘብ ስታገኝ ወደ መዋቢያ እቃዎች መሸጫ ሱቆች መሄድ አዘወተረች:: እዚያ የገዛችውን እቤት ካለው ጋር እያቀላቀለች አዳዲስ የሜካፕ ስራዎችን በመሞከር ራሷን ማስተማር ላይ ትኩረት አደረገች::

ይህ ቤት ውስጥ የምታደርገው ጥረት ከፍ ወዳለ ደረጃ የሚያደርስ አንድ አጋጣሚ ፈጠረላት:: የሜካፕ ሙያ ትምህርት ቤት ገብታ የመማር ፍላጎት ቢኖራትም አጋጣሚውን ማግኘት ሳትችል ቀረች:: በሌላ በኩል ግን ከልጅነቷ ጀምሮ ትወደው የነበረው የፊልም ሙያ ጥበብ ለመማር አንድ ትምህርት ቤት ገባች:: በዚያም ከፊልም ሙያተኞች ጋር የመገናኘትና ያላትን የሜካፕ ስራ ክህሎት



እንዲሁም የመስራት ፍላጎት ለመናገር እድል ሲገጥማትም ስራዎቿን ማሳየት ጀመረች:: የፊልም ባለሙያዎችም የምትሰራቸውን የሜካፕ ስራዎች ይወዱላትና ያበረታቷት ጀመር:: ይህም መስራት እንደምትችል አረጋገጠላት።

በሂደትም እየተማረች ባለችበት የፊልም ሙያ ማሰልጠኛ ተቋም ውስጥ የሚሰሩ የተለያዩ አጫጭር ፊልሞች ላይ በሜካፕ ስራ መሳተፍ ጀመረች:: ይህም ብዙዎች ስራዋን አጠንክራ እንድትይዝ ገንቢ አስተያየት እንዲሰጧትና ከፊልም ሰሪዎች ጋር በመገናኘት ወደ ስራ መግባት አስቻላት። ሁሌም እራሷን በሙያው የተሻለ ቦታ ማድረስ የምትፈልገው ሰዓዳ አዳዲስ ነገሮችን መሞከርና በሜካፕ ስራው የተለየ ነገር ለመስራት ጥረቷን ቀጠለችና ተወዳጅ ባለሙያ ለመሆን በቃች::

አሁን ላይ አገራችን ላይ ከተመረጡ የሜካፕ ባለሙያዎች መካከል የምትመደበውና በርካታ ስራዎችን በመስራት ላይ የምትገኘው የሜካፕ አርቲስቷ ሰዓዳ፣ የተለያዩ የሜካፕ አይነቶችን በመስራት በሙያው ላይ ያላት ክህሎት ጥልቅ መሆኑን አሳይታለች:: በስራዋ ውስጥ የተለያዩ ጉዳዮችን በሜካፕ ለማሳየትም ትሞክራለች:: የሴት ልጅ ጥቃት፣ የዓለም የአየር ፀባይ ለውጥ፣ ስለ ሰላም፣ ስለ አገር፣ ስለ ዘረኝነትና ወቅታዊ ጉዳዮችን በተሰጣት ሙያ ማንፀባረቅ ያስደስታታል::

ከምትሰራቸው ዘርፍ ብዙ የሜካፕ ስራዎች በተጨማሪ በፊልም ደረጃ ወደ 32 ፊልሞች ላይ ተሳትፎ አድርጋለች:: ከሜካፕ ሙያ በተጨማሪ አንዳንዶቹ ፊልሞች ላይ በትወናም ተሳትፎ አድረጋለች:: ከተሳተፈችባቸው ፊልሞች መካከል ኪያ፣ ክሱት፣ መላ፣ የተረት ሎሚ፣ ዶቃ (ዶቃ በቅርቡ የሚወጣ)፣ የሴት ልጅ ዝምታ፣ ሞት እምቢ፣ ልዋጭ፣ ጥቁር እና ነጭ 2፣ ሲሳይ ነው፣ ሚስት ጨርሰናል እና በ4 ተከታታይ የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይ ተሳትፋ ችሎታዋን አስመስክራለች::

በሙዚቃ ክሊፕ ከነ ወንድሙ ጂራ፣ ሀሊማ አብዱራህማን፣ አብነት ግርማ፣ ኮሜዲያን ቶማስ፣ ሚኪያስ ወልዴ እና ሌሎችም ጋር ሰርታለች:: በአጫጭር ፊልሞች ደግሞ “Love and the Brain” እና “The Trip” በተባሉ በዓለም አቀፍ ደረጃ ለውድድር በቀረቡ ፊልሞች ላይ በመሳተፍ ከቡድን አጋሮቿ ጋር ሽልማትን አግኝታለች::

ሙያው አሁን ላይ ያለበት ደረጃ ሙሉ ለሙሉ መልካም ነው ማለት እንደማይቻል የምትናገረው ሰአዳ፣ አንዳንድ የሙያውን ኃያልነት የሚያውቁ እና ሙያውን ከልባቸው የሚያከብሩት ደራሲያን፣ ዳይሬክተሮች እና ፕሮውዲሰሮች በደንብ እየተጠቀሙበት መሆኑን በስራ አጋጣሚ የተመለከተችውን ታስረዳለች:: ነገር ግን ይህን ያልተረዱ ሰዎች ስራውንም አጣጥለው ሙያተኛው የሚፈልገውን ሳይሰራ የሚገባውን ገንዘብ ብቻ ሳይሆን ክብርና ልምድ ሳያገኝ የሚያልፍበት ጊዜ እንዳለ ታስረዳለች። የሙያው ክብር የሚገባቸውና ጥቅሙን የሚረዱ ሰዎች ሲበረክቱ አንድ ቀን የኢትዮጵያን የፊልም ኢንዱስትሪ በሜካፕ ሙያ ከፍ ወዳለ ደረጃ ማድረስ እንደሚቻል ግን ያላትን ተስፋ ትናገራለች።

በውጭው ዓለም የሜካፕ ሙያ እጅጉን ከፍተኛ ደረጃ መድረሱን የምታስረዳው ሰዓዳ፤ ከሀሳብ ጀምሮ በቁሳቁስ አቅርቦት፣ የባለሙያው ነፃነት፣ የባለሙያው ክፍያ ለሙያው የሚሰጠው ክብርና በጋራ የመስራት ፍላጎት ከእኛ አገር አሰራር ጋር ትልቅ ልዩነት እንዳለው ትገልፃለች::

“በፊት ላይ በአንዳንድ ማህበረሰብ ዘንድ በሙያው ላይ ያለው አመለካከት ከባድ ነበር” የምትለው ሰዓዳ፣ የምትሰራቸውን አንዳንድ ስራዎች በማህበራዊ ሚዲያ በምትለቅበት ጊዜ በአስተያየት መልክ “የሴይጣን ስራ ነው የምትሰሪው” ትባል እንደነበር ትናገራለች:: ነገር ግን አሁን ላይ ሜካፕ ትልቅ ሙያ መሆኑን ሰው እየተረዳው መሆኑን ትናገራለች:: ሙሉ ለሙሉ ነቀፌታው ባይጠፋም ሰው ማበረታታ እየለመደ መሆኑንም ታብራራለች::

“ለሙያው እድገት እኛ ባለሙያዎች በራሳችን ማድረግ ያለብን አስተዋጽኦ እንዳለ ሆኖ የፊልም ደራሲያን፣ ዳይሬክተሮች፣ ፕሮውዲሰሮች የሚሰሩት ስራ ላይ የሜካፕ ባለሙያዎችን በደንብ ሊያሰሩ የሚችሉትን ታሪኮች መፃፍ ከለመዱ፣ የፊልም ዘውግ ደግሞ ወጣ ብሎ (science fiction .. thriller .. horror.. action) ፊልሞችን መስራት ይገባቸዋል:: ማህበረሰቡም የሙያውን ትልቅነት ተረድቶ ቢያከብረው እንዲሁም የሚሰሩ ሰዎችን ማበረታታት ቢቻል መልካም ውጤት ላይ መድረስ” ይቻላል ትላለች።

“ሙያውን ለሚፈልግ ሰው ደራሽ መሆን እፈልጋለሁ” የምትለው ሰአዳ፣ ሙያተኞች የትም ሳይለፉ አጠገባቸው የመሆን ሃሳብ እንዳላት ታብራራለች። “አላህ ከረዳኝ ማሰልጠኛ ተቋም ከፍቼ ሙያውን ማወቅ የሚፈልጉ ሰዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ ማለት እፈልጋለሁ:: ኢንሻአላህ ሌሎችም ብዙ እቅዶች አሉኝ ሁሉም እንደሚሳኩ ተስፋ አረጋለሁ” በማለትም ምኞትና የወደፊት እቅዷን ትገልፃለች።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ከብሔራዊ ፈተናው ባለፈ.....

**አቤል ገ/ኪዳን**

የ12ኛ ክፍል ፈተና ተጠናቅቋል:: በብዙ ድራማ ታጅቦ የተካሄደው ፈተና መጠናቀቁ ትልቅ እፎይታ ነው:: በእኔ ግምት የዘንድሮው ፈተና አንድ ትልቅ ሙከራ ነበር:: በዚህ የፈተና ሂደት ብዙ ጭንብሎች ተገፍፈዋል:: ፈተናን እንደ ፖለቲካ መሳሪያ የሚጠቀሙ ኃይሎች ክንዳቸው ተሰብሯል:: ኩረጃን ተማምነው ሳያጠኑ የሚከርሙ ተማሪዎች ከአሁን ወዲያ ይህ አይነት እድል እንደሌላቸው አውቀውታል:: በሙስና ተማሪዎቻቸው ተኮራርጀው ውጤት ሰቅለው እንዲያልፉ ያደርጉ የነበሩ ትምህርት ቤቶች አሁን ከእውነታው ጋር ሊጋፈጡ ጊዜያቸው ደርሷል:: ብቻ ግሩም ሙከራ ነበር:: በቀጣይ አመትም እንደሚደገም ተስፋ አለኝ::

የዛሬው ትዝብቴ የሚያተኩረው ግን በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ነው:: እሱም በግል ትምህርት ቤቶች የተስፋፋው የውጤት ግሽበት ላይ ነው:: መቼም የግል ትምህርት ቤት ጉዳይ ብዙ ነው:: የዋጋቸው ሰማይ መንካት፤ የተማሪዎች የስነ ምግባር ጉዳይ፤ የትምህርት ቤቶቹ የግብዓት ጉዳይ ወዘተ ብዙ ነገር ያነጋግራል:: የሆነ ሆኖ ሐምሌ በመጣ ቁጥር ዋጋቸውን የሚሰቅሉት እነዚህ የግል ትምህርት ቤቶች ለወላጅ የከፍያውን ዋጋ የሚመልሱለት በከፈለው ልክ በልጁ ላይ እውቀት በመጫን ሳይሆን ማርክ በመቆለል ነው::

እኔ በማውቀው ድሮ ድሮ ሁሉም ተማሪ ብዙውን ጊዜ ከፍተኛ ውጤት የሚያስመዘግበው እንደ ስእል እና ስፖርት ባሉ ብዙም ከባድ ባልሆኑ እና ለልጅ በሚስማሙ የትምህርት አይነቶች ነበር:: እኔ ራሴ ሁሌም ከዘጠና በላይ የማገኘው በነዚህ የትምህርት ዘርፎች ላይ ነበር:: በሌሎቹ ላይ ግን ትክክለኛ አቅሜ ፍንትው ብሎ ይታያል:: ለምሳሌ ያህል ሂሳብ የሚባል ትምህርት ብዙም የማይገባኝ የነበረ ሲሆን እስከማስታውሰው በሂሳብ ትምህርት ያስመዘገብኩት በጣም ከፍተኛ ውጤት 70 አካባቢ ነበር::

የግል ትምህርት ቤቶች ላይ ነገሩ በተቃራኒው ነው:: ሂሳብ የማይወደው ተማሪ በሂሳብ 97 አግኝቶ ታገኘዋለህ፤ ሳይንስ ጭራሽ የማይሰርጸው ልጅ በሳይንስ 99 ነው ያገኘው ይባላል፤ ቋንቋ የሚቸገረው ልጅ በቋንቋ ዋነኛ ተፎካካሪ ሆኖ ይታያል:: ብቻ ማርኩ እንደ ዘንድሮ ገበያ ላይ የተንጠለጠለ ነው:: ልጆቹ እንግዲህ እንዲህ የጋሸበ ማርክ ሲሰበስቡ ኖረው ነው ብሔራዊ ፈተና ላይ የሚቀመጡት እና ባልለመዱት ስርአት የሚመዘኑት::

የትምህርት ዋነኛው ተልእኮ ለተማሪው የመሞከር እና የመሳሳት እድልን መስጠቱ ነው:: አሁን አሁን እኮ ልጆቹ ጭራሽ እንዳይሳሳቱ እየተደረጉ ነው የሚማሩት:: መምህሩ የሚያወጣላቸው ጥያቄ ለመልሱ የተቃረበ ነው:: ፈታኙ አጠገባቸው ቆሞ እንዳይሳሳቱ የሞራልም የእውቀትም ድጋፍ ያደርግላቸዋል:: ራሳቸውን ችለው እንዲሰሩ እና ውጤት እንዲያመጡ እድል አይሰጣቸውም:: ትምህርት ቤቶች ይህን ከመጠን ያለፈ ድጋፍ የሚያደርጉት ተማሪው ውጤቱ ዝቅ ካለ እነሱን ስለሚወቅስ እና ገበያ ስለሚቀዘቅዝባቸው ነው:: ወላጅ ይህን የጋሸበ ውጤት የሚቀበለው የከፈለው ገንዘብ እና የደከመው ድካም ውጤት ያመጣ መስሎ ስለሚሰማው ነው:: በዚህ ሂደት ተጎጂዎቹ ልጆቹ ናቸው:: ራሳቸውን፤ ተሰጥኦቸውን፤ ዝንባሌያቸውን መለየት አይችሉም:: ሁሉም ነገር ላይ ጎበዝ ናችሁ ስለተባሉ የእውነትም ሁሉም ነገር ላይ ጎበዝ የሆኑ ይመስላቸዋል:: እንዲህ ሆነው ሄደው ነው እንግዲህ ብሔራዊ ፈተና ላይ የሚቀመጡት:: ያኔ ልጆቹ ከምቾት ቀጠናቸው ይወጣሉ:: ከምቾት ቀጠናቸው ሲወጡ እና እውነታውን ሲጋፈጡ ደግሞ ብስጭት ይመጣል:: ፈተናው ከበደኝ፤ ፈታኞቹ አጉላሉኝ፤ የተፈተንበት ቦታ አልተመቸኝም፤ ወዘተ የሚመጣው ከምቾት ቀጠና ከመውጣት ነው::

አሳዛኙ ነገር ልጆችን በዚህ መልኩ በምቾት ቀጠናቸው ውስጥ ብቻ ሆነው እንዲማሩ እና እንዲያድጉ መደረጋቸው ከትምህርት እና ፈተናውም ባለፈ በመቀጠል ለሚመጣው ሕይወት ዝግጁ እንዳይሆኑ ማድረጉ ነው:: ሕይወት ላይ የሚያግዝ ፈታኝ የለም:: ለመልስ ዝግጁ ሆኖ የሚዘጋጅ የሕይወት ጥያቄም የለም:: የሕይወት ጥያቄ ከባድ ነው:: ፈታኙም ራሱ ሕይወት ነውና ጨካኝ ነው:: ከጎን ሆኖ አይዞህ የሚልም የለም:: ዛሬ ማርክን ማጋሸብ ይቻላል:: እውቀትን ግን እንደ ማርኩ መቆለል አይቻልም::

ስለዚህም ስራው መጀመር ያለበት ወደኋላ ተሂዶ ነው:: ተማሪዎች ፈተናን መለማመድ ያለባቸው ከታች ጀምሮ ነው:: ደብተራቸው ላይ አንዳንዴ ኤክስ ምልክት ሊኖር ይገባል:: የተሳሳቱትን እና ያልገባቸውን ከታች ጀምሮ እያወቁ፤ እየጠየቁ፤ የእውቀት ክፍተታቸውን እየደፈኑ ሊመጡ ይገባል:: ወላጅ ልጁ በምን ትምህርት ላይ ጎበዝ እንደሆነ በምን ላይ ደግሞ ድጋፍ እንደሚፈልገው እያወቀ መሄድ አለበት:: ወላጅ የልጁን ደብተር ገልጦ ሲያይ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ራይት ሲያይ መጠራጠር አለበት:: ምክንያቱም ይህ እውነት እና ጤናማ ስለማይሆን ነው::

ይህ በእንዲህ እንዳለ በግል ትምህርት ቤቶች የሚታየው የውጤት መጋሸብ እንዳለ ሆኖ በመንግስት ትምህርት ቤቶች የሚታየው የውጤት መላሸቅ፤ ኩረጃ እና ሌሎችም ብዙ የሚያሳስቡ ናቸው:: ተማሪዎች ከሚገባቸው በላይ ውጤት ሊሰጣቸው አይገባም የተባለውን ያህል በዚያው ልክ የተማሪዎችን ሙከራ እና ጥረት እውቅና የማይሰጥ እንዲሁም ተማሪዎች ያሉባቸውን ተግዳሮቶች ግንዛቤ የማይሰጥ የትምህርት አሰጣጥም ሆነ ትምህርት ቤት ብሎም መምህር መስተካከል አለበት::

ሲጠቃለል የትምህርት ሚኒስቴርም ጥረት ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች እኩል የሆነ የመወዳደሪያ መፍጠር ነው:: የዘንድሮው ብሔራዊ ፈተናም የዚያ ጥረት መገለጫ ነው:: ትምህርት ሚኒስቴር ይህን ግሩም ሙከራ ሙሉ ለሙሉ ውጤታማ ለማድረግ እና በዘለቄታው ኩረጃን ከኢትዮጵያ የትምህርት ስርአት በማስወጣት ጥራት ያለው ተማሪ ለማፍራት እያደረገ ያለው ጥረት የሚደነቅ ነው:: ነገር ግን ከብሔራዊ ፈተናው ባለፈ በሁሉም ደረጃ ላይ መሰራት አለበት:: የውጤት ግሽበትም ሆነ የውጤት ልሽቀት እንዳይኖር ሁሉም ተማሪ በፍትሃዊነት የሚመዘንበት ምዘና ስርአት በሁሉም የክፍል ደረጃ ላይ ሊዘረጋ ይገባል::

# ነፃ ሃሳብ

# እየጠለቀች ያለችው የአሸባሪው ትህነግ ጀንበር

**እስማኤል አረቦ**

የካቲት 1967 ጥቂት የትግራይ ተወላጆች የነበረውን ስርዓት በመቃወም ነፍጥ አንግበው ደደቢት በርሃ ከተቱ፡፡ የትግራይ ነጻ አውጪ ግንባር /አሸባሪው ትህነግ/ መመስረቱም ተበሰረ፡፡ ከአንድ አመት በኋላም በ1968 የመጀመሪያውን ማኒፌስቶ (ድርጅቱ የሚመራበት ሰነድ) በሚስጢር ተሰራጨ፡፡ የነበረውን ስርዓት ለመቃወምና በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማንበር በርሃ ገብተናል ያሉት ግለሰቦች በወራት ውስጥ ሃሳባቸውን ለውጠው ትግራይን ከእናት ሃገሯ የመገንጠል አላማ እንዳላቸው አስታወቁ፡፡ አማራም ዋነኛ ጠላታቸው እንደሆነ አወጁ፡፡

በድንገት የተቀየረውና ትግራይን ከእናት ሀገሯ ኢትዮጵያ ለመገንጠል የተሸረበውን ሴራ የሚቃወሙ ንጹሃን የትግራይ ልጆች በድብቁ ማኒፌስቶ አልተስማሙም፡፡ በአገኙት አጋጣሚ ወደ በርሃ የገቡበት አላማ ትግራይ መገንጠል እንዳልሆነና ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር ያለውን ኋላቀር ስርዓት በጋራ ማስወገድ ዋነኛ የትግል ስልት መሆን እንደሚገባው በየአገኙት አጋጣሚ ተሟገቱ፡፡

ሆኖም እነዚህ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን በሴራ በየአሉበት መታረድ ጀመሩ፡፡ ኢትዮጵያዊነትን ስለመረጡ በያሉበት ተረሸኑ፤ እድለኛ የሆኑትም ባዶ ስድስት የሚባል ከምድር በታች እስር ቤት ለአመታት ታሰሩ፡፡ ተንገላቱ፡፡ ግማሾቹም እራሳቸውን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አጠፉ፡፡ በአጠቃላይ በ17 አመታቱ ጦርነት ውስጥ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ያሉ ከ20 ሺ በላይ ንጹሃን የትግራይ ልጆች በአሸባሪው ትህነግ አመራሮች የጭካኔ በትር መገደላቸውን በትግሉ ወቅት የነበሩ ነባር የቡድኑ አመራሮች ይናገራሉ፡፡

እስከ 1977 ዓ.ም ድረስ ትህነግ በሚያራምደው ጸረ-ኢትዮጵያዊ አካሄድ በርካታ ተቃውሞዎች ሲገጥሙት ቆይቷል፡፡ ንጹህ ኢትዮጵያዊ የሆነው የትግራይ ህዝብም ትግራይን ከኢትዮጵያ የመገንጠል አስተሳሰብን ስለማይቀበለው በትህነግ የተረቀቀው ማኒፌስቶ ለህዝቡ ይፋ ሳይሆን ቆይቷል፡፡ አልፎ አልፎ ሾልከው የሚወጡ ወሬዎችም የትግራይን ህዝብ ተቃውሞ እንዳይቀሰቅሱ በማለት በፍጥነት የማዳፈን ስራዎች ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ የህዝብ ተቀባይነት ያላቸውን እንደ ሙሴና አግአዚ የመሳሰሉ ጠንካራና ንጹሃን ኢትዮጵያዊ የትግራይ ልጆችን ከጀርባቸው በመተኮስ እንዲገደሉ ተደርጓል፡፡

በ1977 የተከሰተው ድርቅ ግን የትህነግን ታሪክ ቀየረ፡፡ ትግራይን ጨምሮ በሰሜኑ ክፍል የተከሰተው ድርቅ ለትህነግ አመራሮች ሰርግና ምላሽ ሆነ፡፡ በሰዎች ርሃብ እና ዕልቂት የፖለቲካ መሰረቱን አጠነከረ፡፡ በጣዕረ ሞት ውስጥ ካሉና ከሚያቃትቱ ነፍሶች በተነጠቀ የእርዳታ እህል የአሸባሪው ትህነግ ክንድ ፈረጠመ፡፡ ከዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ለድርቁ ተጎጂዎች ከተሰበሰበው 100ሚሊዮን ዶላር ውስጥ 95 ሚሊዮን ዶላሩን በመስረቅ እራሱን በመሳሪያ አጠናከረ፡፡ በምትኩ የትግራይ ህዝብ በርሃብ ረገፈ፡፡

በቂ ምግብ ያላገኘው የትግራይ ህዝብ ሕይወቱን ለማትረፍ ወደየትኛውም ቦታ እንዳይንቀሳቀስ ታገተ፡፡ የትግራይ ህዝብ መላወሻ አጥቶ አይኑ እያየ በርሃብ ረገፈ፡፡ ለህዝብ ዕልቂት ምንም አይነት ርህራሄ የማይሰማው የቡድኑ አመራር በሰረቀው ገንዘብ መሳሪያ በገፍ አስገባ፡፡ ቀደም ሲል አንዲት ስንዝር መሬት ተቆጣጥሮ የማያውቀው ትህነግ በየቦታው በለስ ቀናው፡፡

**አሁን የትግራይ ህዝብም የትህነግን ሴራና የማደናገሪያ ስልት የተረዳ ይመስላል፡፡ ለዘመናት በዚህ ቡድን አደንቋሪ እና አደንዛዥ ፕሮፓጋንዳ ልጆቹን ከመገበር ባለፈ ያገኘው አንዳች ጠቀሜታ እንደሌለ ከተጨባጭ የሕይወት ተሞክሮው ለመረዳት እድል አግኝቷል**

ሰኔ 15 ቀን 1980 ዓ.ም በትግራይ ህዝብ ላይ ሌላ ክህደት ተፈጸመ፡፡ ለደርግ ወታደራዊ ኃይል የተሳሳተ መረጃ በመስጠት ለገበያ የወጣውን የሃውዜንን ህዝብ በማስጨረስ ሌላ ክህደት ፈጸመ፡፡ ጸረ- ኢትዮጵያ አቋም በነበራቸው ሀገራት ድጋፍም ጉዳዩን ዓለም አቀፍ ለማድረግ ተሞከረ፡፡ በሁኔታው ግራ የተጋባው ዓለም አቀፉ ማህበረሰብም በወቅቱ የነበረውን መንግስት አውሬ አድርጎ ሳለው፡፡

በርካታ ወከባ የደረሰበትም የመንግስቱ ኃይለማርያም አመራር በሂደት መፍረስ ጀመረ፡፡ 1983 ዓ.ም የስርዓቱ ማብቂያ ሆነ፡፡ በንጹሃን ደም ላይ እየተረማመደ የመጣው የትህነግ አመራርም በለስ ቀንቶት ታላቋን ኢትዮጵያን የመምራት ዕድል አገኘ፡፡

ሳያስበው ኢትዮጵያ የመምራት ዕድል ያገኘው የትህነግ አመራር በወረደ አስተሳሰቡ ኢትዮጵያን ከታላቅነት ወደ ቁልቁለት ማውረድ ጀመረ፡፡ የ3ሺ አመት ታሪክ ባለቤት የሆነችውን ኢትዮጵያ በአንድ ሽማግሌ ዕድሜ በ100 ዓመት ቀንብቦ አስቀመጣት፡፡ ከኢትዮጵያዊነት ይልቅ ዘርና ጎሳ ገነነ፤ በመላ ሀገሪቱ ብሔርተኝነት ተቀነቀነ፡፡ ኢትዮጵያዊነትም ጭጋግ ለበሰ፡፡ ጸረ ኢትዮጵያዊ የሆኑ አካላትም ጮቤ ረገጡ፡፡ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት እንዳበቃላቸው ታመነ፡፡

ሆኖም በጽኑ መሰረት ላይ የቆመው ኢትዮጵያዊነት አቧራ ቢወርሰውም፤ ጉም ቢሸፍነውም፤ አቀበትና ቁልቁለት ቢበዛበትም እንዳደፈጠ አንበሳ ክንዱ ብርቱ ነበር፡፡ በአገዛዝ ዘመኑ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ይጠላ የነበረውን የትህነግ አመራርን ለማስወገድ ሁሉም የልቡን በልቡ አድርጎ ሲጠብቅ ቆይቷል፡፡ የትህነግ አመራር ውዳቂ እንዳገኘ ጥንብ አንሳ ሙስናና ዘረፋ ላይ ሲርመሰመስ ኢትዮጵያዊነትን የሚያቀነቅኑ አመራሮች ብቅ አሉ፡፡

በኦሮሚያ፤ በአማራ በአዲስ አበባና በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ጸረ ትህነግ እንቅስቃሴዎች በረከቱ፡፡ በሁኔታው የተደናገረው የትህነግ አመራር የሚይዘው የሚጨብጠው አጣ፡፡ መሳሪያ ቢተኩስም፤ አስቸኳይ ጊዜ አዋጆችን ቢያዥጎደጉድም የኢትዮጵያን ህዝብ ማቆም አልቻለም፡፡

በሁኔታው ተስፋ የቆረጠው ሴረኛው የትህነግ አመራር 27 አመታት በፈላጭ ቆራጭነት ከኖረበት አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ፈርጥጦ መቀሌ ገባ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብም በመጠኑ እፎይታ አገኘ፡፡ ሆኖም በሴራ ተወልዶ በሴራ ያደገው የትህነግ አመራር መቀሌ መሽጎ ኢትዮጵያን ማተራመስ ቀጠለ፡፡

ቀድሞ የዘራቸውን መርዞችና የቀበራቸው የጥፋት ፈንጂች አንድ በአንድ ማፈንዳት ጀመረ፡፡ ብሔርን ከብሔር መፋጀት፤ ሃይማኖትን ከሃይማኖት ማናቆር ጀመረ፡፡ በዚህም በበርካታ አካባቢዎች ሞት፤ ስደትና መፈናቀል ነገሰ፡፡ ዩኒቨርስቲዎችም የዕውቀት ማዕከል መሆናቸው ቀርቶ የሞት ማእከላት እንዲሆኑ አበክሮ ሰራ፡፡

አሸባሪው ትህነግ ከሃዲ ቡድን ነው፡፡ ውለታን የማያስታውስ፤ በቀለኛና አረመኔ ነው፡፡ ለዚህ ትልቁ ማሳያ በሰሜን ዕዝ ላይ የወሰደው ትውልድ ይቅር የማይለው አጸያፊ ተግባር ነው፡፡ የሰሜን ዕዝ አባላት ከ20 አመታት በላይ በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ የትግራይ ህዝብን ሲጠብቁ ኖረዋል፡፡ ሆኖም ከሃዲው ትህነግ የሰሜን ዕዝ ወታደሮችን በውድቅት ጨለማ ከጀርባቸው አርዷቸው ተገኝቷል፡፡ ይህም አልበቃ ብሎት በጠራራ ጸሃይ ከበድን ላይ ልብስ ገፎ በጸሃይ አንቃቅቷል፡፡ በተጋደሙ ሬሳዎች ፊት ከበሮ አንስቶ ደልቋል፡፡

ሆኖም ጀግናው የመከላከያ ሰራዊት ይህን አረመኔ ቡድን የገባበት ገብቶ ቀጥቶታል፡፡ የመከላከያ ሰራዊትን ምት መቋቋም ያልቻለው ቆላ ተንቤን ገብቶ ለመሸሽግ ተገዷል፡፡ ሆኖም ለትግራይ ህዝብ በሚል መንግስት ከተቆጣጠረው የትግራይ መሬት መውጣቱን ተከትሎ በውጭ ደጋፊዎቹ አማካኝነት እንደገና ነፍስ ዘርቶ ወደ አማራና አፋር ክልል በመምጣት እንደገና የበቀል እርምጃውን ፈጽሟል፡፡ መነኩሴዎችን ደፍሯል፤ በልጆቿ ፊት እናትን ደፍሯል፤ የሰዎችን ሆድ በሳንጃ ቀዷል፤ ገሏል፤ አፈናቅሏል፤ ቤተ እምነቶችን ደፍሯል፡፡

አሸባሪ ቡድኑ ይህን አስጸያፊ ተግባር እየፈጸመ ደብረሲና ድረስ ቢመጣም የኢትዮጵያ የጸጥታ ኃይሎች አስራ አምስት ቀን ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ቀጥቅጥጠው ከአማራና ከአፋር ክልል በማስወጣት አንገቱን ሰብሮ መቀሌ እንዲገባ አድርገውታል፡፡ የተሰበረ አከርካሪውን ለስድስት ወራት ሲጠግን ቆይቶ ነሐሴ 18 ቀን 2014 ለሶስተኛ ጊዜ ትንኮሳ በማድረግ ጦርነት ቀስቅሷል፡፡ እራሱ በጫረውም እሳት የመጨረሻ ግብዓተ መሬቱን ቆፍሯል፡፡

አሸባሪው ሕወሓት ሶስተኛውን ጦርነት የጀመረው የውጭ ደጋፊዎቹን በመተማመን ነው፡፡ የውጭ ኃይላት የሸብር ቡድኑ እስትንፋስ እንዳትቆረጥ የሳተላይት እና የመሳሪያ ድጋፍ፤ የሚዲያና የኮሙኒኬሽን እገዛ፤ ዲፕሎማሲያዊ ጫናና የኢኮኖሚ ዕቀባ ቢያደርጉም አሸባሪ ቡድኑን ሊያድኑት አልቻሉም፡፡ አሁን የትግራይ ህዝብም የትህነግን ሴራና የማደናገሪያ ስልት የተረዳ ይመስላል፡፡ ለዘመናት በዚህ ቡድን አደንቋሪ እና አደንዛዥ ፕሮፓጋንዳ ልጆቹን ከመገበር ባለፈ ያገኘው አንዳች ጠቀሜታ እንደሌለ ከተጨባጭ የህይወት ተሞክሮው ለመረዳት እድል አግኝቷል ።በተለይም ቡድኑ በህዝባዊ እንቢተኝነት ከስልጣን ተወግዶ ትግራይ በመመሸግ የሄደበት የጥፋትና የእብሪት/ የእብደት / መንገድ ለትግራይ ህዝብ የቱን ያህል ደንታ ቢስ እንደሆነ ከመቼውም ጊዜ በላይ እንዲያገናዝብ እድል ሰጥቶታል።

ለትግራይ ህዝብ ቅርብ በነበረው ፤ በቀበሮ ጉድጓድ ሆኖ ለአመታት ሲጠብቀው የነበረውን የመከላከያ ሰራዊት ከኋላው ከመውጋት ጀምሮ ለሰላም የተዘረጉ እጆችን በመርገጥ ለስልጣን ጥማቱ ሲል ተጨማሪ ሁለት ጦርነቶችን በሀገር ላይ በማወጅ የትግራይ ወጣቶችን ለእልቂት ዳርጓል ።ሕዝቡን ከፍ ወዳለ ማህበራዊ ምስቅልቅል ውስጥ ከቶ ፤ በዚህም በአለም አቀፍ ደረጃ ለመቆመር ረጅም ርቀት ተጉዟል ።

ከሁሉም በላይ መቼም ቢሆን ሊለያቸው ከማይችላቸው የአማራና የአፋር ወንድም ህዝቦች ጋር ደም በማቃባት የህዝቦቹ ቀጣይ ግንኙነት ችግር ውስጥ እንዲወድቅ ስራዬ ብሎ በተጠናና ጭካን በተሞላበት መንገድ ተጉዟል ።ይህ ሁሉ የቡድኑ ጥፋት የትግራይ ህዝብ የቡድኑን የጥፋት መንገዱ አይኑን ከፍቶ ማየት እንዲችል ረድቶታል። ለዚህም ነው ነጻ በወጡ የትግራይ መሬቶች ህዝቡ ለሰራዊቱ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልካም ምኞቱን እየገለጸ ያለው ። ለዚህ ነው እዚህ እዚያም የቡድኑን አገዛዝ የሚቃወሙ ድምጾች በትግራይ ምድር መሰማት የጀመሩት።

በአሁኑ ወቅት አሸባሪ ቡድኑን ለማዳን የሚችል ምንም አይነት ምድራዊ ኃይል የለም፡፡ ስለሆነም አሁን የቀረው አሸባሪው ትህነግ በ1967 ተወልዶ በ2015 ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ የሚል የሙት መታሰቢያ ሃውልት ማቆም ብቻ ነው፡፡

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የአርሶ አደሮቹ ስንዴን ለውጭ ገበያ የማምረት ተነሳሽነት ማሳያ

**አስቴር ኤልያስ**



ከአርሲ ዞን ብቻ ወደ አስራ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የሚጠጋ የስንዴ ምርት ይጠበቃል

በጥቅምት ወር ነፋስ ከወዲህ ወዲያ በሚገማሸረው የስንዴ ማሳ ጠርዝ ላይ ቆም ብለው ከአጋሮቻቸው ጋር ሲያወጉ ያገኘናቸው አርሶ አደር ፈይሳ ቡታ፣ ሁሌም ሲቆጩኝና ጥያቄ ሲያጭርብኝ የነበረው የዳቦ ቅርጫት እየተባለ የሚነገርላት ኢትዮጵያ  ዳቦ ሊሆን የሚችለውን ስንዴ ከውጭ ስታስገባ ማየቴ ነው ይላሉ።

አርሶ አደር ፈይሳ ነዋሪነታቸው በአርሲ ዞን ሔጦሳ ወረዳ ሲሆን፣ የቡቺ ሐቤ ባዶሳ ቀበሌ የሕብረት ስራ ማህበር አባል ናቸው። እኛ ኢትዮጵያውያን ስንዴን በስፋት አምርተን በቅርባችን ላሉ ለጎረቤት አገራት መላክ የሚያስችለን አቅሙ እያለን ከውጭ አገር ማስገባታችን ሳያንስ ለልመና እጃችንን መዘርጋታችን ሊያስቆጨን ይገባል ሲሉ ይገልጻሉ። እስካሁን የመጡበት ይህ ሁኔታም  ከእንግዲህ ወዲያ ሁሉም በቁጭት ተነሳስተው እንዲሰሩ ሊያደርጋቸው እንደሚገባም ያስገነዝባሉ።

በእነ አርሶ አደር ፈይሳ ክላስተር ያሉት አርሶ አደሮች ስንዴ አምርተው ለውጭ ገበያ ማቅረብ እንደሚችሉ ራሳቸውን አሳምነዋል ወደ ስራ ገብተዋል፤ በዚህ ስራ ላይ ማተኮርን ትልቁ ተግባራቸው አድርገው ተነስተዋል።

ሰሞኑን ከተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ዞኖች ከግብርናው ዘርፍ የተውጣጡ ታዳሚዎች በአርሲ ዞን በስንዴ አምራችነቷ ከምትታወቀው ሔጦሳ ወረዳ በሻቂ ሻራራ ቀበሌ ተገኝተው የልምድ ልውውጥ ባደረጉበት ወቅት እርሳቸውም ልምድ ካካፈሉ አርሶ አደር አንዱ ናቸው። እኚህ አርሶ አደር፣ የቡቺ ሐቤ ባዶሳ ቀበሌ ህብረት ስራ ማህበር አባል ከመሆናቸው በተጨማሪ እርሻቸውን የሚያካሂዱት በክላስተር (ኩታ ገጠም) ነው፤ አርሶ አደሩ የክላስተሩ ተጠሪም ናቸው። በቁርጠኝነት የሚሰሩ አርሶ አደር ከመሆናቸው የተነሳም በርካታ አርሶ አደሮችን ያቀፈው ክላስተር መጠሪያ ስሙ «ፈይሳ ክላስተር» በመባል ለመታወቅ በቅቷል።

ክላስተሩ በብዙ እንግዶችም የተጎበኘ ነው። በ‹ፈይሳ ክላስተር› የታቀፉ አርሶ አደሮች ስንዴ የሚያመርቱት በ506 ሔክታር መሬት ላይ ነው። ከዚህ ውስጥ ደግሞ 100 ሔክታሩን ለዘር ማብዣ አውለውታል።

አርሶ አደር ፈይሳ፣ ሁልጊዜ መለመን አስነዋሪ ከመሆኑም በተጨማሪ አሳፋሪም ነው ይላሉ። አሳፋሪና አስነዋሪ ነው ያሉበትንም ምክንያት ሲያብራሩ፤ ኢትዮጵያ የጎደላት ነገር ስለሌላት ነው ብለው ኮራ ብለው ይናገራሉ። የሰጡትን የሚያበቅል ሰፊ መሬትና በውሃም ቢሆን የታደለች አገር መሆኗን ጠቅሰው፣ ካለፈው የአመራረት ዘዴ ዋጋ ከፍላም ቢሆን ልትወጣ እንደሚገባ ነው የሚገልጹት።

«ራሳችንን የግድ በምግብ መቻል ብቻ ሳይሆን  አሁን በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ የተጀመረውን ስንዴ ለውጭ ገበያም የማቅረብ እቅድ  ለማሳካት በትኩረት መስራት አለብን ይላሉ። ይህን ደግሞ ተግባራዊ ለማድረግ አቅማችንን ሁሉ አሟጠን በመረባረብ ላይ እንገኛለን ብለዋል። ያለምንም ማጋነን በእኛ አካባቢ ያሉ አርሶ አደሮች የ‹ይቻላል›ን መንፈስ ተላብሰናል ማለት እደፍራለሁ ሲሉም ገልጸዋል።

በክላስተሩ 130 አርሶ አደሮች ታቅፈዋል፤ እነርሱም ስንዴ ወደውጭ አገር በመላኩ ረገድ የመጀመሪያዎቹ እንዲሆኑ እድል የተሰጣቸው መሆናቸውን ነው አርሶ አደር ፈይሳ የተናገሩት። ይህን የመጀመሪያ የሆነ እድላቸውንም በአግባቡ ሰርተው ተግባራዊ ለማድረግ ቁርጠኞች ስለመሆናቸው ያመለክታሉ።

አርሶ አደሩ፣ ስንዴ ለውጭ ገበያ የማቅረቡን ጉዳይ እንደምናሳካው በእርግጠኝነት መናገር እንችላለን፤ ይህ ብቻ አይደለም፤ ወደፊት ደግሞ ስንዴ ከውጭ ከመግዛት፣ ከድህነት ለመውጣት ቁርጠኝነቱ አለን። በመሆኑም እያንዳንዱ ከእኛ ጋር የሚሰራ ባለድርሻ አካል ታች ድረስ ወርዶ መስራት ይጠበቅበታል። እንደእሱ ከሆነ ደግሞ ታሪክ መቀየር የሚያስችለን ሀብት በእጃችን አለና እናሳካዋለን ብዬ አምናለሁ ሲሉ ገልጸው፣ እኛ ጠንክረን ከሰራን ድህነትን የማናጠፋበት፣ ራሳችንን በምግብ ከመቻል ባለፈ ቀሪውን ዓለም የማንመግብበት ምንም ምክንያት አይኖርም ብለዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ ገና ያልተነካ ሀብት ባለቤት ናት፤ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ወጣቶችም አሏት። ምንም እንኳ የግብርናው ስራ አብዛኛውን ጊዜ ለአርሶ አደሩ ተትቶ የቆየ ዘርፍ ቢሆንም፤ አሁን ግን የተማረውም ሆነ ያልተማረውም ወደስራ መግባት አለበት።

አንዳንዶች ለግብርና የሚሰጡት ትርጉም ዝቅተኛ እንደሆነም አርሶ አደሩ ጠቅሰው፣ ለግብርናው ሙሉ አቅማችንን አውለን በትጋት ከሰራን ከየትኛውም ዘርፍ ባልተናነሰ ውጤታማ መሆን እንችላለን ነው የሚሉት። እሳቸው ኮምባይነር እና ትራክተር ለመግዛት ጠይቀዋል። ይህን የሚያደርጉት ደግሞ ሌላ ገቢ ኖሯቸው አይደለም፤ በግብርናው ዘርፍ ተግተው መስራት በመቻላቸው ነው። አርሶ አደር ፈይሳ በእርግጠኝነት በግብርና መለወጥ እንደሚቻል ያመለክታሉ። በትጋት ሰርተን ማምረት ከቻልን ወደውጭ ገበያ የማንልክበት ምክንያት አይኖርም፤ እንዲያውም ለውጭ ገበያ ማቅረቡ በጣም ቀላሉ ነገር ነው ይላሉ።

የሔጦሳ ዩኒየን ዘር ከማቅረብ ጀምሮ የግብርና ምርቶችን እስከመረከብ ድረስ አብሯቸው የሚሰራ መሆኑን የተናገሩት አርሶ አደር ፈይሳ፣ ሔጦሳ ዩኒየን ማለት የእኛ ድምር ውጤት ነው ሲሉ ይገልጻሉ። ኬምቴክስ የተባለ የእርሻ ግብዓቶች አስመጭ የግል ድርጅት አብሯቸው የሚሰራ ድርጅት መሆኑንም ጠቅሰው፤ ልክ እንደዚህ ድርጅት ሁሉም ለሚሰራው ስራ የተሻለ ነገር ማቅረብ ቢችል አገራችንን በአጭር ጊዜ ውስጥ ራሷን ከድህነት ማውጣት ይቻላል ብለዋል። የዘንድሮው እንደ ጅማሬ ቢሳካ በቀጣይ ዓመት የሚላከውን ምርት ከማሳደጋችንም በተጨማሪ ተፎካካሪ እስከመሆን እንደርሳለን፤ ከዚህ ደግሞ የሚያግደን አይኖርም ሲሉ አስረድተዋል።

የሔጦሳ ወረዳ የግብርና ጽህፈት ቤት ምክትል ኃላፊ አቶ ዘሪሁን መኮንን በበኩላቸው የሔጦሳ ወረዳ በስንዴ አምራችነቷ ቀደም ሲልም እንደምትታወቅ ተናግረው፣ ኩታ ገጠም በስፋት የሚሰራበት ወረዳ  መሆኗ የዘንድሮውን ለየት እንደሚያደርገው ይጠቁማሉ። አጠቃላይ ወረዳዋ ካላት መሬት ውስጥ ከ95 በመቶ በላይ የተሰራው በኩታ ገጠም መሆኑና ወረዳው ከ95 በመቶ በላይ በሜካናይዜሽን መጠቀሙ መሆኑን ያብራራሉ።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ወረዳው ካለው ኩታ ገጠም እርሻ 1 ሺ 390 ኩታ ገጠሞችን አንድ ላይ ሰብስቦ እየሰራ ነው። ከ26 ሺ ሔክታር መሬት ውስጥ ወደ 24 ሺ ሔክታር የሚሆነው የተዘራው በኩታ ገጠም ነው። ከዛ ውስጥ 15 ሺ 952 ሔክታሩ በስንዴ ዘር ተሸፍኗል። በዚህ መልኩ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ስንዴ ነው። በተለይም በወይና ደጋና ቆላማው አካባቢ ስንዴ በከፍተኛ ሁኔታ እየተመረተ ይገኛል።

ከዚህም የተነሳ ዘንድሮ ወደ 50 ሺ ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ ዝግጅት ተደርጓል። እንደ ኦሮሚያ ክልል ወደ ሶስት ሚሊዮን እንደ ፌዴራል ደግሞ አስር ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለውጭ ገበያ ለመላክ ዝግጅት መደረጉን መረጃዎችን ጠቅሰው ተናግረዋል። ከፍተኛ መስኖም ባይኖረን በክረምቱ ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርገን እየሰራን ስለሆነ ይህን እናሳካዋለን ሲሉም ገልጸዋል።

በጠቅላይ ሚኒስትራችን ሲገለጽ የቆየው ጉዳይ በስራ እየተገለጠ ነው ወይስ አይደለም የሚለው በተግባር መሬት ላይ እየታየ ያለ ጉዳይ ነውና ተነሳሽነቱን ወስደን በመስራት ላይ እንገኛለን የሚሉት ደግሞ የሔጦሳ ወረዳ ዋና አስተዳዳሪ አቶ መሐመድ ሁሴን ናቸው። ይህን እውነት የመገናኛ ብዙኃኑ መጥተው ማየት ይችላሉ ሲሉም አረጋግጠዋል።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ በውጭ አገር መገናኛ ብዙኃኑ በኩል እንደሚወራው ኢትዮጵያ በጦርነት እየታመሰች ያለች አገር አይደለችም፤ ያጋጠማትና ተገዳ የገባችበትን ጦርነት ሕግን በማስከበር ረገድ ወደፍጻሜው ማምጣት ብቻ ሳይሆን በልማቱም በኩል በአግባቡ እየሰራች ስለመሆኗም ሊነገርላት ይገባል። ይህንንም በማምረት እያሳየች ትገኛለች። እየበለጸገች ያለች አገር እንጂ ድህነቷ ላይ የቆመች አለመሆኗን ትልልቅ ነን የሚሉ መገናኛ ብዙኃን ሊያጤኑት ይገባል።

በአሁኑ ወቅት ስንዴን ከራሳችን አልፈን ለውጭ ገበያ እናቀርባለን ስንል እየሰራን ያለውን ስራ ተማምነን ነው ሲሉ ይገልጻሉ። በኩታ ገጠም (በክላስተር) መስራት በመጀመራችን ትልቅ ለውጥ እያመጣን እንድንሄድ አስችሎናል ሲሉ አቶ መሀመድ ይጠቁማሉ። ኩታ ገጠም ደካማውን አርሶ አደር ወደ ብርቱው አርሶ አደር የሚስብ ስራ መሆኑንም ጠቅሰው፣  ውጤት እንድናስመዘግብ እያደረገን ያለ ነው ሲሉ ዋና አስተዳዳሪው አመልክተዋል።

በኩታ ገጠም የዘራነውን 3ሺ ሔክታር ስንዴ ለውጭ ገበያ ለማዋል አቅደናል የሚሉት አቶ መሐመድ፣ ይህ ደግሞ እንደሚሳካ መቶ በመቶ እርግጠኛ ነኝ። እንዲያውም ከዚህም በላይ እናሳካዋለን ብዬ አምናለሁ ብለዋል።

እኛ በወረዳችን ያሉ አርሶ አደሮቻችንን ግብርና ወደ ሜካናይዜሽን ለውጠናል ብለን እናምናለን። በወረዳው በአሁኑ ወቅት በበሬ የሚያርስ አርሶ አደር እምብዛም አታዩም። ሁሉም የሚያርሰው በትራክተር፣ ሁሉም የሚያጭደው በኮምባይነር ነው ማለት ያስደፍራል ብለዋል።

በእርግጥ ሁሉም ነገር አልጋ በአልጋ ነው ማለት አይቻልም  ያሉት አቶ መሀመድ፣ ለምሳሌ ሙጃን የሚያጠፋልንን የአረም መድኃኒት ዛሬም ቢሆን እንሻለን ይላሉ። ስንዴን መሬት ስላለን ብቻ ዘርተን መቀመጥ ማለት አይደለም፤ ልክ እንደ አንድ ህጻን ልጅ መንከባከብን የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። እንክብካቤው እንደተጠበቀ ሆኖ ቴክኖሎጂውን በአግባቡ ተጠቅመን የምንሰራ ከሆነ ደግሞ ኦሮሚያን ሁሉ ይዘን መውጣት እንችላለን ሲሉ በእርግጠኝነት ተናግረዋል። እጅ ለእጅ ተያይዞ በመስራት ኦሮሚያን ብሎም ኢትዮጵያን የበለጠ ማሳደግ እንደሚቻልም ነው ያመለከቱት።

የአርሲ ዞን የሰብል ልማት ባለሙያ አቶ ሙዘይን አማን የዞኑን ሰፊውን እርሻ የሚሸፍነው ስንዴ መሆኑን ጠቅሰው፣ ዘንድሮ በመኸር ሰብል ከተሸፈነው 656 ሺ ሔክታር መሬት ውስጥ 281 ሺ ሔክታሩ የተሸፈነው በስንዴ ነው ይላሉ። ከአንድ ወር በኋላ ለአጨዳ ብቁ የሚሆነው ስንዴ ደረጃውን ጠብቆ እንዲታይ ካደረገው ምክንያት አንዱ የአረም መድኃኒቶችን በአግባቡ መጠቀም በመቻሉ ነው ሲሉ ይናገራሉ። በተለይ ኬምቴክስ በመባል የሚታወቀው ድርጅት ከአርሲ ዞን አርሶ አደርና ግብርና ባለሙያዎች ጋር በቅርበት ሆኖ ሰፋፊ ስራዎችን እየሰራ መሆኑን ይገልጻሉ። አርሶ አደሩ ኬምቴክስ የሚያቀርባቸውን የአረም መድሃኒቶች እንደ ፓላስ፣ ሱፐር ፓላስና ሌሎች ኬሚካሎችን በስፋት መጠቀሙ ለምርታማነቱ ትልቁን ድርሻ ማበርከቱን አስረድተዋል።

ባለሙያው እንደሚሉት፤ መንግስት ለግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ነው። ዘንድሮ ደግሞ ስንዴ ላይ በትኩረት እየሰራ ነው። እንደዞንም በስንዴ ላይ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል።  ዘንድሮ ብቻ 281 ሺ ሔክታር በዘር ተሸፍኗል፤ ከአንድ ወር በኋላ ወደ ሰብል ስብሰባው የሚገባ ይሆናል።

በአጠቃላይ ወደ አስራ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የሚጠጋ ምርት ከስንዴ ብቻ እንጠብቃለን ያሉት ባለሙያው፤ ከዚህ ውስጥ 60 በመቶው ለቤት ፍጆታ፣ 40 በመቶው ደግሞ ለአገር ውስጥም ሆነ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ነው ብለዋል። ከዚህ ውስጥ አንድ ሚሊዮን ኩንታል የሚሆን ስንዴ እንደ አርሲ ዞን ብቻ በአገር ደረጃ ለውጭ ገበያ ከታቀደው ትልቁን ድርሻ ለመሸፈን ዞናችን ሰፊ አቅም አለው ሲሉ አስረድተዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ አርሶ አደሩ ቴክኖሎጂ የመቀበል ዝግጁነቱ ጥሩ ነው፤ አስፈላጊ የሆነውን ግብዓት በሰዓቱ በማቅረቡ ረገድ ግን ክፍተት አለ። በጥቅሉ የግብዓት ችግር አለ፤ በዚህ ጉዳይ ሁሉም ባለድርሻ ቢተባበር መልካም ነው፤ ከዚህ በላይ ምርታማነትን ለመጨመር ግብዓት መሟላት ብሎም ሁሉም እንደየደረጃው መትጋት ይጠበቅበታል።

መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፤ በኦሮሚያ ክልል በዘር ለመሸፈን ከተዘጋጀው 6 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ እስከ አሁን በኩታ ገጠም የለማውን ጨምሮ 5 ነጥብ 2 ሚሊዮን ሄክታር መሬት የሚሆነው በዘር ተሸፍኗል። በስንዴ ብቻ 1 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም ለማልማት ርብርብ እየተደረገ ሲሆን፣ በእስካሁኑ ሂደት 1 ነጥብ 3 ሚሊዮን ሄክታር መሬት በኩታ ገጠም ልማት በስንዴ ብቻ መሸፈን ችሏል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

## የትምህርት ቤት ምገባና ትሩፋቶቹ

**ጽጌረዳ ጫንያለው**

ተማሪ ዳዊት ፍጹም የዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት የሰባተኛ ክፍል ተማሪ ነው። ተማሪ ዳዊት ከድሃ ቤተሰብ የተገኘ በመሆኑ በርካታ ችግሮችን አሳልፏል። እናቱን ላለማስቸገር ምሳ ሳይቋጠርለት ወደ ትምህርት ቤት የሚሄድባቸው ጊዜያት በርካታ ናቸው። እናቱም ቢሆኑ በሰው ቤት ልብስ አጥበውና ለውዝ ሸጠው ስለሚያስተዳድሩት ሁልጊዜ ምልቶላቸው ምሳውን ላይቋጥሩለት ይችላሉ። ምግብ ሲኖር ጎርሶ ሲያጣም ረሀቡን ችሎ እንዲማር ተገዷል። ክፍል ውስጥ ቢገባም ትምህርቱን ለመከታተል ግን ይቸገር ነበር። ስለዚህ አብዛኛውን ጊዜ የትምህርቱን ሰዓት በእንቅልፍ እንደሚያሳልፍ ያስታውሳል። ይሄ ውጤቱ ዝቅ እንዲል አድርጎታል።

‹‹እስከ ስድስተኛ ክፍል ግንፍሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው የተማርኩት። በደረጃ ከ20 በላይ እንጂ ከዚያ በታች ወጥቼ አላውቅም›› የሚለው ተማሪ ዳዊት፤ በእናቱ ብርታትና ከእርሱ የባሱ ሰዎችን ሲያይ እንደሚጽናና ይናገራል። ምክንያቱም በረሃብ ምክንያት ራሳቸውን ስተው የሚወድቁ፣ የተማሪዎችን ፊት ላለማየት ከክፍል የሚቀሩ ጥቂቶች እንዳልነበሩ ያስታውሳል።

‹‹የድሃ ልጅ መሆን በትምህርት ቤት ውስጥ በብዙ መልኩ ያሸማቅቃል። ይዞ ከሚመጣው ምግብና መጠን አንጻርም ብዙ ፈተና ነው።›› ያለን ተማሪ ዳዊት፤ አንድ ቀን የገጠመውንና ዘላለም የማይረሳውን ነገር ያነሳል። ጊዜው እናቱ ምሳ ያልቋጠሩለት ነበር። ነገር ግን አብሮ መብላት የተለመደ ስለነበር ጉጉት አድሮበታል። ስለዚህም ከእነርሱ ጋር እመገባለሁ ብሎ አስቦ ትምህርቱን በአግባቡ ተከታትሎ ወጣ። ሆኖም ያሰበው አልሆነም። ጓደኞቹ ችግሬን ይሸከሙልኛል የሚላቸው ተማሪዎች ምሳ ስላልያዝክ አብረኸን መብላት አትችልም አሉት። በዚህም እጅግ አዘነ።

ከእረፍት በኋላ የሆነውን እያሰበ የባሰ ረሃቡ ጠናበት። በዚህም እንቅልፍ ብቻ ሳይሆን እንባም ተናነቀው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከጓደኞቹ ጋር መብላቱን አቋረጠ። ከተቋጠረለት ይበላል ካልተቋጠረ ደግሞ ጦሙን ውሎ ወደቤቱ ይመለሳል። ያን ጊዜ የሆነውን መቼም ማሰብ እንደማይፈልግ አጫውቶናል።

አሁን ነገሮች በመቀየራቸው ደስተኛ ብቻ ሳይሆን በውጤትም የተሻለና የደረጃ ተማሪ እንደሆነ የሚናገረው ዳዊት፤ ይህንን ሥር የሰደደ ችግር በመጠኑም ቢሆን እንደሚቀርፍ ተስፋ የተጣለበት የትምህርት ቤት ምገባ ፕሮግራም እነርሱን ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻቸውንና መምህራንን እፎይ እንዳስባላቸው ያምናል። በተለይም መንግሥት ወጥ በሆነ መንገድ መተግበሩ ዝቅ ያለ ስሜት ሳይሰማቸው ከእኩዮቻቸው እኩል እንዲማሩና ውጤታማ እንዲሆኑ እንዳስቻላቸውም ያነሳል።

እኛ ዛሬ የተገኘንበት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያለው የካራ አሎ ቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ይህንን ከሚያረጋግጡ መካከልም ይጠቀሳል።

የተማሪዎች ፈገግታ ሲበሉና ሳይበሉ እንኳን የሚለይበት ነው። ተሰልፈው ሲታዩም እውነትም ይህ ምገባ ብዙ ነገሮችን ከቤተሰብ ተጋርቷል እንድንልም እንሆናለን። ምክንያቱም ዛሬ ባለው ኑሮ ውድነት ስንቶች ልጆቻቸውን በሚገባ መመገብ ይችላሉ ብንል ምንም ሊሆን ይችላል ምላሻችን። በመንግስት በተቀረጸ መርሃ ግብር ግን ከቅድመ መጀመሪያ እስከ ስምንተኛ ክፍል ባሉ በሁሉም የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ይህ ተግባር ይከናወናል። በዚህ ደግሞ ባለፈው ዓመት በነበረው መረጃ እንደተመላከተው ከ300 ሺህ በላይ ተማሪዎች ተጠቃሚ ሆነዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እንደገለጸው ደግሞ በባለፈው በጀት ዓመት ለትምህርት ምገባ ከ1ነጥብ2 ቢሊዮን ብር በላይ በመመደብ በከተማዋ እና በዙሪያዋ የሚገኙ ከ600 ሺህ በላይ ተማሪዎችን የምገባ መርሃ ግብሩ ውስጥ ተካተው ምግብ አግኝተዋል። ይህ የሆነው ደግሞ ቀደም ሲል ከነበረው በጀት ዓመት ተጠቃሚዎቹን በእጥፍ በማሳደግ ነው። በተጨማሪም የከተማ አስተዳደሩ የዜጎችን ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በተለያዩ አምስት ክፍለ ከተሞች በቀን አንድ ጊዜ መመገብ የማይችሉ ዜጎችን በመለየት የምግብ አገልግሎት እንዲያገኙ በአንድ ጊዜ 1000 ዜጎችን ማስተናገድ የሚችሉ የመመገቢያ ማዕከላትን በማቋቋም በሺዎች የሚቆጠሩ የጎዳና ተዳዳሪዎች እና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያሉ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ችሏል።

የተማሪዎች ምገባ መርሐ ግብርን ጨምሮ የከተማ አስተዳደሩ በምገባ ዘርፍ የጀመራቸው ሥራዎች ለሌሎች አገራት ምርጥ ተሞክሮ ሆኗልም። በጣሊያን ሮም ከተማ በተባበሩት መንግስታት ድርጅት አዘጋጅነት በተካሄደው



ፎቶ፡- በአሸናፊ ጉደታ

የካራ አሉ ቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርትቤት ተማሪዎች በምገባ ላይ

የዓለም ስነ ምግብ ኮንፈረንስ ላይ በተሞክሮነት ቀርቧል። ሽልማትም ተሰጥቶታል። ምክንያቱ ደግሞ ሥራው ተማሪዎች የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ከማድረጉ እና የተማሪዎችን ውጤት በማሳደግ የመድገምና የማቋረጥ ምጣኔን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ከመቻሉ ባለፈ፣ በምገባ መርሃ ግብሩ ምግብ በማብሰል ሥራ ከ10 ሺህ በላይ ለሚሆኑ እናቶች የሥራ ዕድል በመፍጠር ቋሚ ገቢ እንዲያገኙ ማስቻሉ ነው።

ከተማ አስተዳደሩ በምገባ ሥራው በዓለም አቀፍ ደረጃ ሽልማትን በአገኘበት ወቅት ሽልማቱን የተቀበሉት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አበቤ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ይህን ሽልማት ያሸነፈች ብቸኛ የአፍሪካ አገር ሆና ነው። ይህ መሆኑ ደግሞ ሽልማቱ ኢትዮጵያን ብቻ ሳይሆን አፍሪካንም እንዲወክል አድርጎታል። ከሁሉም በላይ ኢትዮጵያ በብዙ መንገድ ሁልጊዜ ምግብ የምትለምን አገር ተደርጋ የምትታወቅበትን ገፅታ ቀይሮታልና እውቅናው ለአገራችን ታሪካዊ ለውጥ ነው።

ጉዳዩ ሀብታም ወይንም ድሃ የመሆን ጉዳይ ሳይሆን፣ የመንግስትን የፖሊሲም፣ የተግባርም ቆራጥነትና ካለችው ውስን ሃብት ለዜጎች ቅድሚያ በመስጠት በተሰራው ስራ የተገኘ ሽልማት ነው። በቀጣይም ይህ ተግባር ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ብለዋል። ለመሆኑ እንዴት ቢሰራ ተሸለመ ካልን ከላይ እንዳልነው የካራ አሎ ትምህርት ቤት ምላሹን ይሰጠናል።

የትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር አቶ አሰፋ መላኩ እንደሚሉት፤ ምገባ የተማሪዎች ብቻ ሳይሆን የወላጆችም ተስፋ ነው። የመምህራንም እፎይታ መሰረት ነው። ምክንያቱም መርሃ ግብሩ ከመጀመሩ በፊት መምህራን የተማሪዎቻቸው በልቶ አለመምጣት ስለሚያሳስባቸው ካላቸው ደመወዝ ላይ ቀንሰው ሲመግቡ ነበር። ያም ሆኖ ብዙዎችን መደገፍ አላስቻላቸውም። ብዙዎችን ከማቋራጥ ማስቆም አልሆነላቸውም። ማርፈድና መቅረትንም በምንም ተአምር ሊታገሉት አልቻሉም። በዚህም ምንም እንኳን የአቅማቸውን ቢያስተምሩም የሚጠብቁትን ውጤት አያገኙም። አሁን ግን ነገሮች በምገባው ተቀይሮላቸዋል። ብዙ ነገሮች ቆመዋል በሚባል ደረጃ ላይ ደርሰዋል።

ምገባው ተግባራዊ መሆን ሲጀምር ተማሪዎች በየትምህርት ዘመኑ ወደ ትምህርት ገበታ የሚመጡበትን እድል ሰጥቷል። በትምህርታቸው ከፍተኛ ውጤት አምጥተው የሚያልፉ ተማሪዎችን ቁጥር ጨምሯል። በተማሪ ቤተሰብ ውስጥ የሚፈጠረው የኢኮኖሚ ችግር ጭምር ተቃሏል። ይህ ደግሞ በተማሪው ስነልቦና ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አወንታዊ ተጽዕኖ አሳድሯል ይላሉ።

የመርሃ ግብሩ ተግባራዊ መሆን ወላጆች በመንግስት ትምህርት ቤቶች ላይ መተማመን እንዲኖራቸው ከማድረጉም ባሻገር መጠነ መቋረጥ እንዲቀንስ እድል ሰጥቷል። የትምህርት ምገባ መርሃ-ግብሩ የወላጆችን ጫና ከማቃለሉ ባሻገር ተማሪዎች ትምህርታቸውን ተረጋግተው እንዲከታተሉም እንዳደረገ ያነሳሉ።

እየተተገበረ ያለው የተማሪዎች ምገባ መርሐ-ግብር ለተማሪ ወላጆች የሥራ ዕድል በመፍጠር ረገድም የማይተካ ሚና እንዳለው የሚናገሩት ደግሞ የትምህርት ቤቱ የትምህርት መሻሻል ምክትል ርዕሰ መምህርና የምገባ መርሃ ግብሩ አስተባባሪ አቶ አይሸሽም ልየው ናቸው። እርሳቸው እንደሚሉት፤ በተፈጠረው የሥራ ዕድል ተደራጅተው እንዲሰሩ በማድረግ የተማሪ ወላጆች በኢኮኖሚ አቅማቸው ከፍ ብሏል። ለአብነትም በትምህርት ቤቱ ከ110 በላይ እናቶች የሥራው ተጠቃሚ ሆነዋል።

በትምህርት ቤቱ ምገባው መጀመሩ ብዙ ለውጦችን እንዳመጣ ምስክርነታቸውን የሚሰጡት ምክትል ርዕሰ መምህሩ፤ የመጀመሪያው ነው የሚሉት በትምህርታቸው የተሻሉ ተማሪዎችን ማፍራት መጀመሩን ነው። ለዚህ ደግሞ መነሻው መጠነ ማቋረጡ፣ መውደቁን፤ ማርፈዱና ትምህርትን በአግባቡ መከታተል እንዲችሉ ማድረጉ እንደሆነ ያነሳሉ። ምገባው ከመጀመሩ በፊት በርካታ ተማሪዎች የመማር ማስተማር ስራውን ያስተጓጉሉት እንደነበርም ያስታውሳሉ።

ለአብነት የሚጠቅሱትም በክፍል ውስጥ እንቅልፍ ሲወስዳቸው ማየቱ፤ በርሃብ ምክንያት መውደቃቸውና የጤና እክል እንዲያጋጥማቸው መሆኑን ነው። መምህሩ እነርሱን በመርዳት የሚያጠፋው ጊዜ እንዲበዛና በአግባቡ ለተማሪዎቹ ትምህርቱን እንዳያቀብል ያደርገዋል። አሁን ግን ነገሮች ተቀይረዋል። ተማሪዎች ከራሳቸው አልፈው ቤተሰቦቻቸውን መመገብ ችለዋል። እንዴት ከተባለ ተማሪዎች በራሳቸው ምሳ እቃ ምግቡ ስለሚሰጣቸው ግማሹን በልተው ለተራቡት ቤተሰባቸው ግማሹን ይወስዳሉ። ይህ ደግሞ ምገባው ተማሪዎች ቤት ድረስ ሄዶ የስነልቦና ህክምና እንደሚያደርግላቸው ያሳየናል ይላሉ። ወላጆች ሲቀምሱት አስተያየትን ይቸራሉና ምግቡ ማስተካከያ እንዲደረግለትም ያግዛል። እናም ምገባው የትየለሌ ጥቅም አለው ባይ ናቸው።

ምገባው ከመማር ማስተማሩ ባሻገር የብዙ ወላጆችን እንባ የጠረገና እፎይታን የሰጠ ነው። ምን ልቋጥር፣ ከተማሪዎች ያንስብኛል እያሉ እንዳይሳቀቁም አግዟቸዋል። ውሎ ሲመጣም በቀን አንዴ ብቻ የሚመግቡትን ነገር ነው የሚያዘጋጁት። ይህ ደግሞ በዛሬ የኑሮ ውድነት ያለውን ሸክም መንግስት ምን ያህሉን እንደሸፈነ መረዳት ይቻላል ይላሉ።

ትምህርት ቤታቸው መንግስት በፈጠረው የምገባ እድል ከ3715 ተማሪዎች ውስጥ ወላጆቻቸው ትምህርት ቤቱን እስኪላመዱ በሚል ምሳ የሚቋጥሩላቸው 60 ተማሪዎችን ቀንሶ ሌሎቹን በምገባው ተጠቃሚ ያደርጋል። የቅድመ መደበኛ ክፍሎችን ለብቻ በተለየ ሜኑና ክፍልም ይመገባል። አንደኛ እስከ አራተኛ ያሉትን ከአምስት እስከ ስምንት ካሉት ነጥሎም እንደየባህሪያቸው የሚመገቡበትን ስርዓት ፈጥሯል።

ለቅድመ መደበኛ የተለየ እንክብካቤ የሚደረግበት ምክንያት ሕጻናት የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት አለባቸው ስለሚባል ያንን ተግባራዊ ለማድረግ ነው የሚሉት አቶ አይሸሹም፤ ምገባ ተከፋፍለውና በጥራት የሚያቀርቡ 110 እናቶችን በመያዝ የሚሰራ ነው። ጥራቱ እንዳይጓደልም ቀደም ሲል የቁጥጥር ቡድን ተመድቦ እየቀመሰ መጠኑንና ጥራቱን በማየት ያያል። አሁን ደግሞ መንግስት ያወረደው አቅጣጫ ስላለ በእርሱ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሆነ ያነሳሉ።

አቶ አይሸሽም የምገባው ጥቅም መተኪያ የሌለው ተግባር እንደሆነ አንስተው፤ በአሰራር ዙሪያ በርካታ ችግሮች እየገጠሟቸው እንደሆነ ይናገራሉ። የመጀመሪያው ያደረጉትም በተደጋጋሚ ጥያቄ የሚቀርብበት የእናቶች ልፋትና ክፍያቸው ያለመመጣጠን ነው። ተማሪዎችን ልክ እንደልጆቻቸው አድርገው ለመመገብ ቢጥሩም ክፍያቸው ግን በቀን 20 ብር ነው። ይህ ደግሞ የዛሬውን ኑሮ ውድነት ለመደጎም ቀርቶ አንድ እቃ ለመግዛት አያስችላቸውም። እናም መንግስት ምላሹን በአፋጣኝ ቢሰጣቸው መልካም ነው ይላሉ።

በሁለተኛ ደረጃ እንደችግር የሚያነሱት የውሃ ጉዳይ ሲሆን፤ በሳምንት አንድ ቀን ለያውም ለትንሽ ሰዓት መጥቶ የሚጠፋ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ ብዙ ሮቶዎች ቢኖራቸውም ጠብታ እንጂ ብዛት ያለው ውሃን አያስገኛቸውም። ምክንያቱም አካባቢው ላይ ያለው ውሃ ወዲያው ከማጠራቀሚያው ያልቃል። የዚህን ጊዜ ለምግብ መስሪያ ብቻ ሳይሆን ለመታጠቢያ ጭምር ያጣሉ። የምግብ ስራው በእናቶች ጉልበት ከቤታቸው በጀሪካን በመጣ ውሃ ቢሰራም እጃቸውን ሳይታጠቡ የሚበሉ ልጆችን አበራክቷል። ይህ በመሆኑ ደግሞ ተማሪዎች ጤናቸው ላይ ችግር መፍጠሩ አይቀሬ ነው። እናም መንግስት ሊያያቸው እንደሚገባ አጥብቀው ይናገራሉ።

እንደ አቶ አይሸሹም ገለጻ፤ የውሃ ችግሩን ለመፍታት በራሳቸው በኩል ብዙ ጥረት አድርገው አንድ ግብረሰናይ ድርጅት አግኝተው ነበር። የከርሰ ምድር ውሃ እንደሚያወጣላቸውና ቦታውን ጭምር አይቶ ሄዶ ነበር። ሆኖም የተለያዩ ቦታዎች ሄደው ለማስፈቀድና ጉዳዩን ለማስረዳት ቢሞክሩም በመንግስት ቢሮክራሲ የተነሳ ሊሳካላቸው አልቻለም። ይህ ብቻ ሳይሆን አካባቢው በውሃ ችግር ይታወቃልና የከተማ አስተዳደሩ ከንቲባ ወይዘሮ አዳነች አቤቤ በቅርቡ ምላሽ እንደሚሰጡት ቃል ቢገባም ችግሩ ግን አሁን ድረስ አልተፈታም። ስለሆነም እንደመንግስት ከሁለት አንዱ መፍትሄ እንዲሆን ቢያግዝ መልካም ነው።

ውሃ እናገኛለን በሚል ተስፋ በግቢው ውስጥ የጀመሯቸው በየመደቡ ተከፍለው መምህራንና ተማሪዎች እንዲሁም መጋቢ እናቶችና የአስተዳደር ሰራተኞች የሚንከባከቧቸው አትክልቶች ነበሩ። በውሃ እጥረት ምክንያት ግን የተፈለገውን ያህል እያመረቱላቸው እንዳልሆነ የሚገልጹት አስተባባሪው፤ የውሃ ጉዳይ አፋጣኝ ምላሽ የሚፈልግ በመሆኑ ሊታይ እንደሚገባ አበክረው ያስረዳሉ።

በመጨረሻ ፈተና ሆኖብናል ብለው ያነሱት ጉዳይ የኤሌክትሪክ ነገር ሲሆን፤ የምግብ አገልግሎቱን ለማቅረብ ዛሬም እናቶች ልክ እንደገጠሩ በእንጨት እየሰሩ መሆናቸውን ነው። በኤሌክትሪክ የመስራት እድሉ ቢኖራቸው ሰዓታቸውን ቆጥበው ለሌሎች ሥራዎች የሚነሱበትን እድል ሰጣቸው ነበር። በተጨማሪም አንድ አይነት ጣዕም ያለው ምግብ መስራት እንዲችሉ ያግዛቸዋል። የጤና ጉዳያቸውም የተስተካከለ ይሆናል። ከሁሉም በላይ ለማገዶ የሚወጣው ከፍተኛ ገንዘብ ብዙ ችግሮችን ቀርፎ ለሌላ ማዋል የሚቻልበትን እድል ይፈጥራል። ስለሆነም ይህም ሊታሰብበት ይገባል ይላሉ።

ለምገባ ተብሎ የሚመደበው ገንዘብ አይደለም እነዚህን ጥቂት ችግሮች ብዙ ነገር የሚፈታ እንደሆነ የሚጠቅሱት አቶ አይሸሽም፤ ባለፈው ዓመት ብቻ ቢታይ ለእነርሱ ትምህርት ቤት ወደ 25 ሚሊዬን ብር ተመድቧል። ይሁንና ጥቅም ላይ የዋሉት በዛ ከተባለ 12 ሚሊዬን ብር ነው። ቀሪው ተመልሷል። ስለዚህም፣ ተመላሽ ከማድረግ ይልቅ መንግስት አሰራሩን ቃኝቶ ችግሮችን መፍቻ ቢያደርጋቸው ብዙ የተሻለ እድሎችን ለተማሪዎች ብቻ ሳይሆን ለማህበረሰቡ ማቅረብ ይችል እንደነበር ያነሳሉ። አሁንም እንዳረፈደ በመጥቀስ ለተግባራዊነቱ ቅን የሆኑ ልቦች ይምጡ ይላሉ።

ትምህርት ቤታቸው በምገባው ዙሪያ የቀጣይ እቅዶችን ጭምር ይዞ እንደሚንቀሳቀስ የሚናገሩት አቶ አይሸሽም፤ አንደኛው ምገባውን ለመደጎም የሚያስችሉ ሥራዎችን እየከወኑ መሆኑን ያነሳሉ። ይህም የጓሮ አትክልቶችን በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ በመስራት ነው። ነገር ግን የውሃ ጉዳይ መፍትሄ ካላገኘ የሚቻል እንዳልሆነ ይናገራሉ።

ሌላው ያነሱት ነገር ለምገባው መሻሻል ከአንዳንድ ተቋማት ጋር ማስተሳሰርና በዝቅተኛ ዋጋ ግብዓቶች እንዲቀርቡ ማድረግ ነው። ይሁንና መንግስት ቢታከልበት የበለጠ እንደሚሆን ያምናሉ። ምክንያቱም የግብርና ምርቶች አቅርቦትን በብዛት ማሳካት የሚቻለው በእርሱ በኩል ሲመጣ ነው። እንደ ሸገር አይነቶችም የዳቦ አቅርቦቱን የተሳለጠ የሚያደርጉት መንግስት ጣልቃ ሲገባ ነው። ስለሆነም ይህ ቢታይና ምገባ ማዕከላቱ ቢደገፉ ባይ ናቸው።

በመደጋገፍ ውስጥ ብዙ ለውጥ አምጪ ሥራዎችን እናያለን። ለዚህም በአብነት የምናነሳው በቅርቡ የተደረገው አለማቀፋዊ ሽልማቱ ነው። ምገባው የተማሪዎችን ብቻ ሳይሆን የሁሉንም ማህበረሰብ ችግር የሚፈታ መሆኑን በቅርብ እያየነው ነውና ይገባናልም ሳልል አላልፍም። ከዚያ ባሻገርም እንደሚያስኬደን አምናለሁ የሚሉት አቶ አይሸሽም፤ በምገባው ብዙዎች እስትንፋሳቸው ተመልሷል፤ ተስፋ አግኝተዋል፤ ጠንካራ ተማሪዎች ተፈጥረዋል፤ ህልመኛና የሚደርሱበትን የሚያውቁ ተማሪዎችን መምህራን እንዲያዩ ሆነዋል። ቤተሰብም ተስፋው እየለመለመለት ነው። ምክንያቱም በምገባው እፎይታን አግኝቷል፤ ኑሮ ውድነቱን መቋቋም ችሏል። ስለዚህ ምገባው ፖለቲካ ሳይሆን ለውጥ ነውና ሽልማቱ የውጤቱ ነው። ወደፊትም አጠናክረን እንድንሰራ የሚያበረታን ነው። እናም ሁላችንም ስኬቱን እያየን በምንችለው መልኩ እንደግፈው ሲሉ መልዕክታቸውን ያስተላልፋሉ። እኛም ምክራቸውን እንቀበለውና እንተግብረው በማለት ጽሑፋችንን ቋጨን። ሰላም!!

# ወቅታዊ

## ‹‹ዓለም አቀፉ ጫና ኢትዮጵያ ላይ መበርታቱ መንግስት እጁን አላስጠመዝዝም በማለቱ የመጣ ነው››

**- አቶ ነጋሲ በየነ**
**በአሜሪካ ዋሽግተን ዲሲ ነዋሪ**

አስቴር ኤልያስ

**በአገረ አሜሪካ ለ30 ዓመታት ያህል ቆይተዋል:: በዋሽግተን የበሽታዎች መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከል (ሲዲሲ) ውስጥ ነው የሚሰሩት። በተለያዩ አስገዳጅ ምክንያቶች ከአገር ይውጡ እንጂ የሚወዷት አገራቸው ግን ከልባቸው ለአፍታም ወጥታ አታውቅም:: ምንም እንኳ ከአገራቸው ኢትዮጵያ ርቀው ለሶስት አስርት ዓመት ያህል በውጭ አገር ቢቆዩም አገራቸውን በእጅጉ ይወዳሉ:: ኢትዮጵያን የተመለከቱ ጉዳዮች ላይ በክፉ የሚያነሳትን በመቃወም፤ መልካም ተግባሯን ደግሞ በመደገፉ ረገድ ግንባር ቀደም ተሰላፊ ናቸው:: ኢትዮጵያ በውጭ አገር የሚያስፈልጋት የድጋፍ ሰልፍ ሲኖር የሚቀድማቸው የለም:: የተቻላቸውን ያህል ለአገራቸው ለማበርከት ደፋ ቀና ይላሉ:: በሞትና በሕይወት መካከል እያጣጣረ ለላለው አሸባሪው ትህነግ ስለነበረው ባሕሪና ስለትግራይ ሕዝብ እጣ ፈንታ እንዲሁም የቡድኑ ማጣጣር ያስደነገጣቸው ምዕራባውያን የአሸባሪው እስትንፋሱ እንዳያከትም በኢትዮጵያ ላይ እያሳደሩ ለላለው ተጽዕኖ እና መፍትሔን አስመልክቶ አቶ ነጋሲ በየነ ጋር ከአሜሪካን ዋሽግተን ዲሲ በስልክ ያደረገውን ቃለ ምልልስ አጠናቅረን እንደሚከተለው አቅርበነዋል::**

**አዲስ ዘመን፡- ትህነግ በቆየባቸው የስልጣን ዘመንም ሆነ ከስልጣን በፊት ያለውን ባህሪ እንዴት ይገልጹታል? በተለይ ደግሞ የትግራይን ሕዝብ በደበልጥ ዋጋ አስከፍሎታልና እዚህስ ላይ ምን ይላሉ?**

**አቶ ነጋሲ፡-** ትህነግን ከድሮ ጀምሮ በደንብ ስከታተለው ቆይቻለሁ:: ምክንያቱም እኔም አንዱ የትግራይ ተወላጅ እንደመሆኔ በትግራይ ክልል ተማሪ እያለሁም ቡድኑ በዚህ ገባ፤ በዚህ ወጣ ሲባል በወቅቱ አስታውሳለሁ:: የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ ስደርስ በወቅቱ ቀይ ሽብር የሚባለው ነበር:: ከዚህ በተጨማሪ ትህነግ ስለነበር ሁሉንም እከታተል ነበርና ስለቡድኑ ሁኔታ ግንዛቤው ነበረኝ:: ከድሮ ጀምሮ በተለይ አርሶ አደሩን በጣም ያሰቃየው ስለነበር ይህንን አውጥቶ አይናገረው እንጂ ጥሩ ስም ያልነበረው ነው:: አርሶ አደሩ የቡድኑ አባላት የጠየቁትን ማቅረብ ካልቻለ ገላውን በጋለ ብረት ያለርህራሄ ይተለትሉታል:: በጋለ ማጭድም ያሰቃዩታል:: ሌላው ቀርቶ በቁም ሁሉ እስከመቅበር የከፋ ጭካኔ ያሳዩታል:: እስከአንገቱ ድረስ ይቀብሩትና በላዩ ላይ ከብቶች ይነዱበትም ነበር::

ከዚህ በተጨማሪ ትህነግ በዋሻ ውስጥ የጨለማ እስር ቤትም የነበራቸው ናቸው:: ከዚያ ከጨለማው እስር ቤት ምናልባት የታደለ ጥቂት ሰው ሊወጣ ይችል እንደሆን እንጂ አብዛኛዎቹ ጸሐይ እንደናፈቃቸው እስከወዲያኛው የሚያሸልቡበት ጊዜ ብዙ ነው:: እንደ እድል ሆኖ የወጣ ሰው ራሱ የሚወጣው በጣም ታምሞ በመሆኑ ጸሐይ የማየት እድሉ ምናልባት ከአንድ ሳምንት የሚዘል አይሆንም፤ ወዲያው ላይመለስ ይህቺን ምድር ይሰናበታታል:: ምክንያቱም በጨለማው እስር ቤት ቆይታቸው ምግብ በደንብ አይሰጣቸውም፤ እንዳይሞቱም እንዳይድኑም አድርገው ስለሚያቆዩአቸው ከወጡ በኋላ የመኖር እድል አይኖራቸውም::

ከዚህ በተጨማሪ የታሰረው ሰው ቤተሰቡ የሚታወቅ ከሆነ እነርሱ (ትህነግ) ገደሉ እንዳይባሉ ከአንድ ሳምንት በኋላ የሚሞት መሆኑን ከተረዱ እና በምድር የመኖሩ እድል መመንመኑን ካረጋገጡ በኋላ ሊኖር ስለማይችል በሚል ከጨለማው እስር ቤት ከእነሕይወቱ አውጥተው ለቤተሰቡ ያስረክባሉ:: ያ የተለቀቀውም እስረኛ ከቀናት በኋላ እንደግምታቸው ይሞታል:: የትህነግ ሁኔታ በጥቅሉ በርካታ ሸር የተሞላበት እንዲሁም ተንኮል የታከለበት



አካሄድ ነው:: በቡድኑ ዘንድ ዴሞክራሲ የሚባል ነገር ለጣዕም ያህል እንኳን የሌለው ድርጅት ነበር ማለት ይቻላል::

ይህ ድርጅት የትግራይን ሕዝብ ለ47 ዓመታት ያህል አሰቃይቶታል:: እኔ በተለይ በቀይ ሽብር ከመታሰሬ በፊት አንዳንድ የቅርብ የምላቸው ጓደኞቼ ‹ወደበረሃ ብትወርድ ይሻልሃል ከምትታሰር› ይሉኝ ነበር:: በመሆኑም እነርሱ ባሉኝ መሰረት ለመሄድ አስብም ነበር:: ይሁንና በትምህርቴ ላይ ትኩረት አደርግ ስለነበር ቸል ብዬም ነበር:: ጉዳዩ ግን እየጠና ስለመጣ አንዳንድ ነገሮችን ማስተዋል ጀመርኩ:: በወቅቱ እማር በነበረበት አጼ ዮሐንስ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ግራ እና ቀኝ እመለከት የነበረው ሬሳ ስለነበር የምማረው ለዚህ ነው እንዴ በሚል አንድ ውሳኔ ለመወሰን ተገደድኩ:: ወይ ኢህአፓ ወይ ደግሞ ወደበረሃ ከመውረድ አንዱን መምረጥ ግድ አለኝ:: በዚያን ጊዜ ግን የትህነግን ማኒፌስቶ በትኩረት ማንበብ ጀመርኩ:: ይሁንና እነርሱ ዘንድ እንዳልሄድ ያስወሰነኝ ነገር ሁለት የሚጋጩ ጉዳዮችን በማስተዋሌ ነው::

በወቅቱ ማኒፌስቶው ይል የነበረው አንደኛው ሕወሓቶች ኮሚኒስት ስለነበሩ ትግራይ ብሔር ሞልታለች ለማለት በኢኮኖሚ እንዳደገች አድርገው ነበር የሚስሏት፤ መንገድ አለን፤ ይህ አለን፤ ያኛውም አለን በማለት ትግራይ በኢኮኖሚ እንዳደገች አድርገው በመቅረጻቸው ባዘጋጁት ምዕራፍ አንድ ይታያል::

ምዕራፍ ሁለት በሚል ደግሞ የተዘጋጀው የአማራ ጭቆናን የሚያሳይ ሲሆን፣ በዚህኛው ምዕራፍ ላይ በዝርዝር የሚስተዋለው ትግራይ ምንም ነገር እንደሌላት ከአማራ ጭቆና የተነሳ እንደደቀቀች የሚያትት ሐሳብ ነው:: በዚህ መልኩ አንደኛውና ሁለተኛው ምዕራፍ የሚጋጭ ሆኖ ስላገኘሁት እነዚህ አካላት ውሸታም ናቸው በሚል ለእነዚህ ውሸታሞች ደግሞ ሕይወቴን አልሰጥም አልኩ፤ ወደበረሃ መውረድ በዚህ መልኩ የቀረብኝ ቢሆንም ለእስር መዳረጉ ግን አልቀረልኝም ነበርና በቀይ ሽብር ለመታሰር ተገደድኩ:: ይሁንና ስለተፈታሁ ከቆይታ በኋላ የደርግም ፍራቻ ስለነበረብኝ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ብገባም ችግሩ አይቀርልኝም በሚል ስኮላርሽፕ ፈልጌ በመጀመሪያ ወደ ራሽያ ወጣሁ:: ከራሽያ በኋላ ወደ አሜሪካ አቀናሁ:: በአሁኑ ወቅት በዋሽግተን የበሽታዎች መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማእከል (ሲዲሲ) ውስጥ የምስራ ሲሆን፣ በቀረው ጊዜዬ ግን አገሬን በማገልገል ላይ እገኛለሁ::

ሕወሓት ከመጀመሪያው ጀምሮ ፀረ ሕዝብ ነው:: ዴሞክራሲ የሚባለው ነገር በፍጹም አይነካካውም:: እርሱ የሚለው ነገር ካልተደመጠ ተጽዕኖው ከባድ ነው:: በአሁኑ ወቅት መጨረሻቸው ደርሶ የጅምላ መቃበሮች ተቆፍረው ሐቁ ምን ያህል እንደሆነ ሕዝቡ ቢያወጣ ብዬ አስባለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- ምዕራፍ አንድ እና ምዕራፍ ሁለት ብለው ያነሷቸው ሐሳቦች ለአንዱ ወገን ትግራይ ምንም የላትም የሚል ሲሆን፣ ለሌላኛው ወገን ደግሞ ያላት ናት ያሉበት ምክንያት ምን ይሆን ብለው ያስባሉ?**

**አቶ ነጋሲ፡-** በወቅቱ ትህነጎች ኮሚኒስቶች ስለነበሩ ትግራይ ብሔር ለመባል አምስት ነገሮችን ማሟላት መቻል ነበረበት:: እነዚህም ባህል፣ ቋንቋ፣ መልካምድራዊ አቀማመጥ፣ ስነ ልቦናዊ አንድነት እና የኢኮኖሚ ማደግ ናቸው:: እንደዛ የሚለው የጆሴፍ ስታንሊን መጽሐፍ ነው:: አንድ ኅብረተሰብ ብሔር ለመባል አምስት ነገሮችን ማሟላት አለበት የሚለው ከጆሴፍ የተቀዳ ነው:: የትህነግ አባላት ደግሞ የብሔር ትግል ነው የምናደርገው ስለሚሉ ብሔር ሞልተናል ለማለት ያንን ያደርጉ ነበር::

ሁልጊዜም ቢሆን ብሔር ብሎ የሚነሳ የትኛውም ድርጅት ጠላት ሊኖረው ይገባል:: ጠላት የማይኖረው ከሆነ ደግሞ ሕዝቡ አይንቀሳቀስለትም:: ስለዚህ ጠላት ብሎ የፈረጀው ደግሞ አማራውን ነው:: ምክንያት አድርጎ ያቀረበው ደግሞ አማራ ስለጨቆነን ትግራይ እንዳያድግ አድርጓል የሚል ነው:: በዚህ አባባል ሰውን ለመቀስቀስ እንዲጠቅመው ነው::

**አዲስ ዘመን፡- ይህ ቡድን የትግራይን ብሎም የኢትዮጵያን ሕዝብ ጎድቶታልና ከዚህስ በኋላ ለትግራይ ሕዝብ ዘላቂ ተስፋው ምንድን ነው ብለው ያስባሉ?**


**አቶ ነጋሲ፡-** ጦርነት አስፈላጊ ነገር አለመሆኑ የሚታወቅ ነው፤ እነርሱ ደግሞ ጦርነትን ሙጥኝ ብለውበታል:: በባህሪያቸው ውስጥ ሰጥቶ መቀበል የሚባል ነገር በፍጹም የለም:: ተፈጥሯቸው ሁሉንም መውሰድ፤ ሁሉንም መጠቅለል ነው:: ያለፈውን ታሪካቸውን ልብ ብለን ከሆነ ሁሉንም ነገር የፈቱት በጦርነት ነው:: ደርግን ለማሸነፍ የተጠቀሙት ጦርነትን ነው:: ኢህአፓን እንዲሁ በጦርነት ነው:: ኢድዩንም በጦርነት ነው:: አንድ በትግራይ ውስጥ እንደእነርሱ አይነት ሆኖ የተቋቋመ ሌላ ድርጅትም በጦርነት ነው የጨረሷቸው:: እንደ መከላከያ ሰራዊት የወጓቸው በተኙበት ነው:: በተለይ እነዚህን ትግራይ ሁለት ድርጅቶችን መሸከም አትችልም በሚል ተዋህደን አንድ ድርጅት እንሁን ብለው በመነጋገር ለእነርሱም አንድ ሆነናል በሚል ተስማምተው እና ለስምምነታቸው የሚሆን ድግስ ከደገሱ በኋላ እኩለ ሌሊት ላይ ስለተጣመርን አብረን ማደር እንችላለን ብለው ለሕወሓት ልዩ መልዕክት ተሰጥቷቸው ነበርና በትዕዛዙ መሰረት ሌሊት ላይ እጃቸውን እንዲሰጡ እምቢ ብለው ካንገራገሩ እንዲገድሏቸው በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ገደሏቸው:: ከእነርሱ ውስጥ አንድ እድለኛ ሰው ማምለጥ ችሏል:: ስለዚህ ትህነግ አደብቶ ከጀርባ የመውጋት ልማዱ የዛሬ ሳይሆን ሲፈጥረውም ጀምሮ የኖረበት ባህሪ ነው:: ባህሪያው ተንኮል የተሞላበት ነው::

በእርግጥ አሁን ባለው ጦርነት በጣም እየተዳከሙ ነው:: የትግራይ ሕዝብ ከመሪዎቹና ከመሪዎቹ ቤተ ዘመዶች በስተቀር የሚተነፍስበት ስለሌለው ለ47 ዓመት በስቃይ ውስጥ ነበር ማለት ይቻላል:: በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ሕዝብ የእነርሱ ተንኮል በደንብ ገብቶታል:: በስልጣን ላይ በነበረበት ጊዜ በኢትዮጵያውያኑ ላይ ያደረሱት ስቃይ ስላለ ተንኮሉን አሳምሮ ስለሚያውቅ ከዚህ በኋላ ሕብረቱና አንድነቱ እንደሚመጣ ባለሙሉ ተስፋ አለኝ:: የአሁኑ ጦርነት በፌዴራል መንግስት አሸናፊነት ይጠናቀቃል ብዬ ነው የማምነው::

ትህነግ ከመሳሪያና ከሰራዊት ውጪ ተደርጎ መሪዎቹ በሕግ አግባብ መጠየቅ ይኖርባቸዋል:: ይህ መንግስት ራሱ የሚወስነው ነገር ነው:: ነገር ግን መልሶ ማቋቋም የሚያስፈልገው አካል አለ:: ባለፈው በተቋቋመው ጊዜያዊ አስተዳደር አካባቢ አንዳንድ ስሕተት ተፈጽሟል:: ይህም ስህተት ምንድን ነው የሚባል ከሆነ በወቅቱ የተሾሙ ሰዎች የሕወሓት አፍቃሪዎች ናቸው:: ሕወሓትን ከልባቸው ውስጥ ያላወጡ አካላት ናቸው:: በዛ ስህተት ምክንያት ነው የአማራ፣ የአፋርም ሆነ የትግራይ ወጣት በገፍ ገብተው ያለቁት:: ስለሆነም የእነርሱ ሴል የሆኑ ሁሉ ተበጣጥሰው እንዲቀሩ በሌላ ተተክተው በአግባቡ ቢሰራ መልካም ይመስለኛል::

በአሁኑ ወቅት አሸባሪው ትህነግ ትክክለኛ ያልሆነ ድርጅት ነው ብለው የሚያምኑ አሉ:: ባለፈው ስምንት ወር ያህል በትግራይ ጊዜያዊ አስተዳደር በቆየበት ጊዜ ለለውጥና ለእውነት የቆሙትን 53ቱን ገድለዋቸዋል:: አብዛኛው አመራሩ ግን የእነርሱ ወዳጅ የሆኑ ነበሩ::

# ወቅታዊ



**ውጭ አገር ያሉት ግን አብዛኞቹ የመሪዎቹ ልጆች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ እነዚህ ልጆች ደግሞ የመጡት በስኮላርሽፕ ሰበብ ሲሆን፣ የአንድ ሚሊዮን ዶላር ቤት ውስጥ የሚኖሩ እና የመቶ ሺ ዶላር መኪና የሚያሽከረክሩ ናቸው፡፡ ይህ የቡድኑ መሽነፍ ከጥቅማቸው ጋር ክፉኛ የተሳሰረ ስለሆነ በየአደባባዩ በመንከባለሉም ሆነ በሌላ ሌላውም በጣም ንቁ ሆነው የሚሳተፉ ናቸው**

ከእዚህ በኋላ በጣም ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነውና መንግስት ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ባይ ነኝ:: ይህ ካልሆነ ግን እኛ ኢትዮጵያውያን የምንኖረው እዳ እየከፈልን ነው::

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት ከትግራይ ሕዝብ የሚጠበቀው ምንድን ነው? ከአገር ውጭ የሚገኙ የትግራይ ተወላጆችስ ኢትዮጵያ ማገዝ ያለባቸው እንዴት ነው?**

**አቶ ነጋሲ፡-** ባለፈው ጊዜ መንግስት በአንዳንድ ምክንያት የተነሳ የትግራይን ክልል ለቅቆ ሲወጣ ቡድኑ ከተደበቀበት ዋሻ መጥቶ እንደገና ቆፍሩ የደበቀውን መሳሪያ በማውጣት መልሶ ኢትዮጵያን ሊወር ችሏል:: ስለዚህም በአግባቡ መንበርከካቸው በደንብ ግልጽ መሆን አለበት:: መልሰው አፈር ልሰው እንዳይነሱ መደረግ አለበት ባይ ነኝ::

እኔ አንድ ነገር እረዳለሁ፤ ከውጭ የእነርሱ አምላኪዎች እንዳሉ ስለማውቅ ተጽዕኖ መኖሩን እገነዘባለሁ:: እነዚህ አካላት ኢትዮጵያ እንድትረጋጋ የማይፈለጉ አካላት ናቸው:: ስለዚህ አሁን የትግራይ ሕዝብ ሕወሓት ኃይል እንደሌለው እርግጠኛ መሆን ከቻለ የእነርሱ ፍላጎት የለውም:: የትግራይ ሕዝብ ስጋቱ እነርሱ ስለሚያጠቁት ነው:: ዝምታን የሚመርጠው ተሸንፉ ተብለው እንኳ ተመልሰው ይመጡ ይሆናል የሚል ስጋት ስላለው ጭምር ነው::

እንዲያውም የትግራይ ሕዝብ ከትህነግ መላቀቁን እንደሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ደስታውን አደባባይ ወጥቶ እልል እያለ መግለጽ የሚፈልግ ሕዝብ ነው፤ ነገር ግን ስጋቱ የተንኮለኛው ቡድን እንቅስቃሴ ነው:: ከዚህ ውጭ ቡድኑ በመወገዱ እንደሌላው ክልል ደስታውን እየጨፈረ መግለጽ የሚፈልግ መሆኑን እርግጠኛ ነኝ:: ነገር ግን ይህን እንዳያደርጉ የሚያስፈራቸው የትህነግ ሴል የሆኑ አካላት በውስጣቸው ስላሉ ነው:: እነዚህ ሴሎች ‹ወየውልህ› ይሏቸዋል:: በጊዜያዊ አስተዳደሩ ጊዜ የታየውም ይኸው ነው::

ስብሰባ በተጠሩ ጊዜ ወጥተው ቢሳተፉ ‹ተመልሰን መምጣታችን አይቀርምና ጠበቅን› የሚል ማስፈራሪያ ይደርሳቸዋል:: ከዚህ ውጭ ደግሞ ‹በዚህ ቀን እንገባለን› በሚል የሐሰት ፕሮፓጋንዳም ስለሚሰሩ ሕዝቡ ይፈራል:: ቡድኑ ደግሞ በፕሮፓጋንዳ ጥርሱን የነቀለ በመሆኑ በሚነዛው ሐሰት ሕዝቡን ስጋት ውስጥ ይከትታል:: ‹ድምጸ ወያኔ› የሚባለውም ቀድሞ የሚያቀርበውን ፕሮፓጋንዳ ነው ሲያተጋባ የሚውለው:: ስለዚህም ትግራይ ውስጥ ያለው ሕዝብ የእነርሱን ተንኮል ስለሚያውቅ ፍራቻ ካልሆነ በስተቀር ችግር አይኖርም ብዬ አምናለሁ:: በእርግጥ በውስጣቸው ሰዎች አይኖርም ማለት ባይቻልም እነዚህን አካላት ሕዝቡ እየጠቆመ ለመንግስት መስጠት ይቻላል::

ውጭ አገር ያሉት ግን አብዛኞቹ የመሪዎቹ ልጆች ናቸው ማለት ይቻላል:: እነዚህ ልጆች ደግሞ የመጡት በስኮላርሽፕ ሰበብ ሲሆን፣ የአንድ ሚሊዮን ዶላር ቤት ውስጥ የሚኖሩ እና የመቶ ሺ ዶላር መኪና የሚያሽከረክሩ ናቸው:: ይህ የቡድኑ መሽነፍ ከጥቅማቸው ጋር ክፉኛ የተሳሰረ ስለሆነ በየአደባባዩ በመንከባለሉም ሆነ በሌላ ሌላውም በጣም ንቁ ሆነው የሚሳተፉ ናቸው:: በገንዘባቸው ኢትዮጵያ ላይ ተጽዕኖ ሊፈጥር የሚችል ሎቢስት እየቀጠሩበት ነው:: በስልጣን ላይ በነበሩበት ጊዜ ከኢትዮጵያ በማውጣት ያከማቹት ገንዘብ ለዚህ ተግባራቸውና ኢትዮጵያን መልሶ ለመውጋት በማዋል የተጠመዱ ናቸው::

አብዛኛው የትግራይ ሰው ግን በብሔርተኝነት ስሜት ውስጥ ነው፤ ብሔረተኝነት የሚባለው በራሱ በሽታ ነው:: እኔ አማራ ነኝ፤ እኔ ደግሞ ትግሬ ነኝ በማለት ከማንነት አለመውጣት ሳያንስ ጀግናው እኔ ነኝ፤ ካለእኔ የሚዋጋ የለም በሚል በርካታ ትምክህቶችን ያመጣሉና ሰው ግን እንደሰው መከበር አለበት ባይ ነኝ:: የትኛውም ሰው ደግሞ እኩል መሆን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርም ሲፈጥረን በራሱ አምሳያ ነው:: ይህ እስከሆነ ድረስ ያንን አለመቀበል እና ትግራዋይ የተለየ እንደሆነ አድርገው መናገር በሽታ ነው:: እንደዚያ እያሉ ግን ስለሚነግሯቸው እናሸንፋለንን ይዘው ነው የሚንከራተቱት:: እንዲህ ማሰብ በሽታ እንጂ ፈውስ የሌለበት አመለካከት መሆኑን መረዳቱ ግን መልካም ነው::

በእርግጥ ከዚህ ሌላ ለትግራዋይ የተወሰነ መጠቀሚያ የሚሆን ነገር ስለሚሰጧቸው ያንን የሰጧቸውን ነገር መልሰው እንደሚወስዱባቸውም ስለሚያስፈራሯቸው ነው እነርሱ በፈለጉት መንገድ እንዲጓዙላቸው የሚያደርጓቸው:: ለምሳሌ ተወላጁ መቀሌ ላይ የሰራው ቤት ይኖራል፤ አሊያም ደግሞ ሌላ ቦታ ያፈራው ንብረት ይኖራልና እርሱን እንወስድብሃለን በሚል ያስፈራሯቸዋል:: የእነርሱን ሐሳብ ከተቃወመ ያቺን ንብረት ስለሚወስዱበት ከዛ ፍራቻ የተነሳ ባሉት መንገድ ሁሉ ይሳተፋል:: ሁለተኛው ደግሞ ስሜታዊ ወይም በብሔርተኝነት ተይዞ የሚሳተፍ መሆኑ ነው::

በእርግጥ ከመንግስት ጎን የቆሙ ዲያስፖራዎች በቁጥር በርከት የሚሉ ናቸው:: ለምሳሌ ቲ.ኤም.ኤች (ትግራይ ሚዲያ ሃውስ) ለሚባለው በ‹ጎፈንድሚ› የሚዋጣለት ገንዘብ አለ:: ይህ ገንዘብ መዋጣት የጀመረው ሚያዝያ ወር ላይ ሲሆን፣ የተጠየቀው ገንዘብ ደግሞ 50ሺ ዶላር ነበር:: ይህን የገንዘብ መጠን ሳየው አንድ ሺ 147 ዶላር ላይ ነው እስካሁን ቆሞ ያለው:: ቀደም ሲል ግን እንኳን 50 ሺ ተጠይቆ ይቅርና እስከ ግማሽ ሚሊዮንም ሆነ አንድ ሚሊዮን ድረስ ቢጠየቅ ምላሹ አፋጣኝ ነበር:: ይህ የሚያሳየን ምልክት አለ ማለት ይቻላል::

ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ እኔ አልፎ አልፎ ምን እንደሚሉ ገብቼ የማየው የትግራይ ሚዲያ ሃውስ የሚያወጣቸው ቪዲዮዎች ቀደም ሲል የነበረው ተመልካች እስከ 100 ሺ ድረስ የሚጠጋ ነበር:: ዛሬ ላይ ግን በእጅጉ ቁጥሩ አሽቆልቁሎ ወደ ስድስትና አምስት ሺ ድረስ ወርዷል:: ከዚህም በላይ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ጉዳይ እያበረደውና እያቀዘቀዘ እንደሚሄድ ደግሞ እርግጠኛ ነኝ:: ኢትዮጵያቹን ደግሞ እንደ ቀደመ ዘመኗ በአንድነት እንደምትቀጥል እርግጠኛ ነኝ:: እኔ ብሔር፣ ክልል ይሉት ነገርን አልደግፈውም:: በዚህ ጉዳይ ላይ መንግስትም ያስብበታል ብዬ አስባለሁ:: እኔ ፍላጎቴ እንኳን ኢትዮጵያ ቀርቶ አፍሪካንም አንድነቷ ሰምሮ ማየት ነው::

**አዲስ ዘመን፡- በአሁኑ ወቅት የትህነግን መሸነፍ ተከትሎ በምዕራባውያን አማካይነት በጣም ከባድ ተጽዕኖዎች በኢትዮጵያ ላይ እያረፉ ናቸው፤ ይህን የዓለም አቀፉን ተጽዕኖ ዲያስፖራው መታገል ያለበት በምን አግባብ ነው ይላሉ?**

**አቶ ነጋሲ፡-** በቂ ነው፤ በቂ አይደለም የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ ዲያስፖራው በዚህ ላይ የተቻለውን ሁሉ እያደረገ ነው:: ባለፈው ከዓመታት በፊት እነስብሃት ነጋ ከመፈታታቸው አስቀድሞ እና ወለጋ አካባቢ በሽኔ በደረሰው በደል የተነሳ በዲያስፖራው መካከል ትንሽ መከፋፈል ተፈጥሮ ነበር:: ይሁንና አሁን ያ መከፋፈል እንዲጠፋ ባገኘነው ሚዲያም ሆነ ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም ዲያስፖራውን እያስረዳነው ነው:: በአገርና በመንግስት ላይ ቅሬታ ቢኖርባችሁ ምዕራባውያኑ መንግስትን ያልፈለጉበት ምክንያት ግልጽ ሊሆንላችሁ ይገባል ብለናቸዋል:: መንግስትን ያልፈለጉበት ምክንያት ለኢትዮጵያ ተሸሎ የተገኘ በመሆኑና የምዕራባውያኑን ትዕዛዝ አልቀበልም በማለቱ ነው:: ዓለም አቀፉ ጫና ኢትዮጵያ ላይ መበርታቱ መንግስት እጇን አላስጠመዝዝም በማለቱ ነው::

አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት እንደትህነግ የፈለጋችሁትን እዘዙኝ እኔ ከቃላችሁ አልወጣም ቢል ምዕራባውያኑ ሕወሓት የት እንዳለ ሁሉ ላያስታውሱት ይችሉ ነበር:: ከትህነግ ጋር የሰሩ እስከማይመስላቸው ድረስ ይዘነጉትና ከዚህኛው መንግስት ጋር ይወዳጁ ነበር::

አሁን ያለው ችግር ጉዳዩን የእጅ አዙር ቅኝ ግዛት ለማድረግ በመሞከራቸው ነው ኢትዮጵያውያን ያልተገባ መስዋትነት እየከፈልን የምንገኘው:: ትህነግ ደግሞ ከምዕራባውያኑ ጋር ከበረሃ ጀምሮ ለበርካታ ዓመታት ሰርቷል:: ከእነሱዛን ራይስ ጋር ግንኙነታቸው ከድሮ ጀምሮ ነው:: በትግራይ በአመራር ደረጃ ያሉ አካላት ከእነ ሱዛን ራይዝ ጋር በልደት ቀን ሁሉ የሚጠራሩ ሰዎች ነበሩ:: ሕወሓት ደግሞ የሚሰራው ለትግራይ ጥቅም ወይ ለኢትዮጵያ ጥቅም አይደለም:: ለራሱ እንደማፊያ ለተሰባሰበው ለተወሰኑ ቡድን ብቻ ነው::

ከዚህ የተነሳ በውጭ አገር ያለው አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ምዕራባውያንን ያገኛቸው ከጠበቀው ውጭ ወርዶ ነው:: ለምን ቢባል መሬት ላይ ያለውና እነርሱ የሚያሰራጩት መረጃ ትክክል ባለመሆኑም ጭምር ነው:: እኔ ራሴ ለምሳሌ ሲ.ኤን.ኤን ጥቂት ሊያጋንን ይችል ይሆናል እንጂ እውነታውን ነው የሚያቀርበው ብዬ አስብ ነበር:: ነገር ግን ምንም ያልሆነና የሌለ ነገር ሰርቶ እንደሚናገር ተረድቻለሁ:: በጥቅሉ ሚዲያዎችና እኔ ያለሁበት አገር ያለው የስለላ ድርጅት ብሎም መንግስታቸው የተያያዙ በመሆናቸው የሚናገሩት እነርሱ ያዋጣኛል የሚሉትንና የፈለጉትን ነው::

ኢትዮጵያውያን አንድ ያልገባን ነገር አለ ብዬ ነው የማስበው:: ምክንያቱም መንግስትን ራሱ መቃወም የሚቻለው አገር ሲኖረን ነውና አገር ከሌለው ማንንስ መቃወምና መደገፍ እንችላለን ብዬ እላለሁ:: አገር ከሌለ መንግስት የለም:: መንግስት ከሌለ ደግሞ ልንቃወም የምንችለው ነገር የለም ማለት ነው:: ስለዚህ ምዕራባውያን የሚፈልጉት እኛ መንግስት አልባ ሆነን በደም በጨቀየ ምድር እንድንቀጥል ነው:: እኛ ደግሞ ማድረግ ያለብን ተቃራኒውን ነው እንጂ ከእነርሱ ጋር በመሆን ኢትዮጵያ ላይ ድንጋይ መወርወር አይገባንም::

ስለዚህ ውጭ ያለነው ዲያስፖራዎች ዋሽንግተን ዲሲ ላይ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረጋችን ለዚህ ነው:: ሰላማዊ ሰልፉ ሁለት ሰዓት ላይ በነጩ ቤተ መንግስት ፊት ለፊት ነው የተደረገው:: ሰላማዊ ሰልፍ በዚህ ብቻ የሚያበቃ ሳይሆን ቀጣይነት ያለው ይሆናል:: ሌላ የሚደረገው ደግሞ የሴነተሮችና የኮንግረስ አባላትን እንዴት አድርገን ቀርበናቸው ለኢትዮጵያ ጥቅም እንዲቆሙ እናድርግ የሚል ደግሞ እየተሰራበት ነው:: ይህ ቢያንስ በአሜሪካ ካሉት 50 ያህል እስቴቶች ኢትዮጵያውያን በብዛት አሉበት በሚባሉት በ21 ስቴቶች ላይ ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ከኢትዮጵያና ከኤርትራ ጎን የማትቆሙ ከሆነ በምርጫ ጊዜ እንደማንመርጣችሁ እውቁ በሚል መልዕክት እናስተላልፋለን ተብሎም ይጠበቃል:: ይበልጥ ሊሰራ የሚችለው ደግሞ ይህ አይነቱ አካሄድ ላይ ነው::

በአሜሪካ የምርጫ ጊዜ ሲሆን አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ድምጹን ለመስጠት አይወጣም፤ ከወጣም በኋላ ብዙዎቹ ማንን መምረጥ እንዳለባቸው አያውቁም:: በመሆኑም ይህን አይነቱን አካሄድ አስጥለን ከወዲሁ እንዴት ማድረግ እንዳለባቸው ኢትዮጵያውኑን እያነቃቃናቸው እንገኛለን:: እንዲህ የምናደርግ ከሆነ ደግሞ የተወሰነ ለውጥ ማምጣት እንደምንችል ተስፋ አደርጋለሁ:: ምክንያቱም ለውጥ ለማምጣት የእኛ የኢትዮጵያውያኑ ድምጽ ያስፈልጋል:: ለምሳሌ ባለፈው ጊዜ የቨርጂኒያ ገዥ እንዲቀየር ተደርጓል:: በሜሪላንድም በዛ አግባብ እየሰራን ነው:: ስለዚህ አያቶቻችን ከእነዚህ ከምዕራባውያኑ ጋር ተጋፍጠው ያሸነፉት ደማቸውን ከፍለው ነው:: እኛ ደግሞ ጊዜያችንንና ገንዘባችንን መስዋዕት አድርገን ኢትዮጵያን ብንታደግ ለኢትዮጵያ ያንስባታል እንጂ አይበዛባትም::

**አዲስ ዘመን፡- የምዕራባውያኑ ሚዲያዎች ከአሸባሪው በመወገን ቢቆሙም የተሸነፈው ትህነግ ብቻ ሳይሆን ራሳቸው የምዕራቡ ሚዲያዎችም ጭምር ናቸው የሚሉ አሉና እዚህ ላይ ያለዎት አስተያየት ምንድን ነው?**

**አቶ ነጋሲ፡-** እነዚህ የምዕራባውያን ሚዲያዎች እያደረጉ ያለውን ተንኮል እኛ ኢትዮጵያውያን ላይ እስኪደርስ ድረስ አላወቅናቸውም እንጂ እየሰሩ ያሉት ነገር በጣም ከባድ ነው:: ሌላው ቀርቶ የሊቢያን ጉዳይ ራሱ አሁን ካለፈ በኋላ እውነቱን አወጥተዋል:: ያልተካሄደ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ እያሉም እንደተናገሩ እውነቱን ገልጸዋል:: አሁን ላይ ሊቢያ አገር ከመባል ክብር የወረደች እንድትሆን አድርገዋት ትተዋታል::

ስለዚህ የእነርሱ ጣልቃ ገብነት ለእኛ በማሰብ የሚያደርጉት አለመሆኑ በግልጽ የሚታወቅ ጉዳይ ነው:: ለምሳሌ ትህነግን ሲደግፉ ለትግራይ ሕዝብ ስለሚያስቡለት አይደለም:: የቅርብ ጊዜ ትውስታችን የሆነችውን አፍጋኒስታንን ብናይ ለሃያ ዓመት ቆይተውባት ዶግ አመድ አድርገዋት ነው የውጡት:: ስለዚህም እንቅስቃሴያቸው ሁሉ ከራሳቸው ጥቅም ጋር የተሳሰረ እንጂ ሌላውን ለማገዝ የሚደረግ አይደለም:: በእርግጥ ኃይለኞች ስለሆኑ በኃይል ለማንበርከክ ይሞክራሉ:: እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ከአያቶቻችን የተማርነው ማንበርከክን እንጂ ለማንም መንበርከክን አይደለም:: ስለሆነም በአገር ላይ መቼም ቢሆን አይኮረፍም እላለሁ:: ሁሉም ዲያስፖራ ተነስቶ ለኢትዮጵያ ጠበቃ መቆም አለበት ብዬ አስባለሁ:: ምክንያቱም ልጆቻችን ለውትድርና ሕይወታቸውን እየሰጡ ነው:: እኛ በውጭ አገር ያለነው ዲያስፖራዎች ጊዜያችንንና ገንዘባችንን ለመስጠት ማቅማማት አይጠበቅብንም:: አንዱ ሕይወቱን እየሰጠ ነው፤ አንዱ ደግሞ ጊዜውን ሌላው ደግሞ ግፋ ሲል ገንዘቡን ነውና ይህን ማድረግ ለአገር በመሆኑ እናስብበት ስል እጠይቃለሁ::

ሁላችንም ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያ እንቁም:: እኔ ለምሳሌ በጣም ደስ ያለኝ ነገር ቢኖር በስንዴ ራሳችንን ችለን ለውጭ ገበያ እናቀርባለን የተባለው ጉዳይ ነው:: በዚህ ጉዳይ ላይ እየተሰራ ያለው ስራ ይበል የሚያሰኝ ነው:: ይህ ስራ የኢትዮጵያ እጅ እንዳይጠመዘዝ የሚያደርግ ስራ ስለሆነ ለዚህ መንግስት ድጋፍ ያስፈልጋል:: የጎደለ ነገር ካለ ደግሞ እንዲታረም ማድረግ ነው እንጂ አገርን አሳልፎ መስጠት አግባብ አይደለም እላለሁ::

**አዲስ ዘመን፡- ጊዜዎን ሰውተው ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ እመሰግናለሁ::**

**አቶ ነጋሲ፡-** እኔም በጣም አመሰግናለሁ::

# ዓለም አቀፍ

## የቻይናው ፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ ለሶስተኛ ጊዜ ስልጣናቸው ተራዘመ

የቻይናው ፕሬዚዳንት ዢ ጂንፒንግ ለሶስተኛ ጊዜ አገሪቷን ሊመሩ ነው። ገዢ ዢንፒንግ የቻይናው ገዥ የቻይና ኮሚኒስት ፓርቲ ባደረገው ጉባኤ ዋና ጸሃፊ አድርጎ መምረጡን ተከትሎም ነው ለሶስተኛ ጊዜ ሥልጣናቸው የተራዘመው።

የፓርቲው ዋና ጸሃፊ በሀገሪቱ የመሪነት ቦታ የሚያስገኝ ሲሆን መጋቢት በሚደረገውም የብሄራዊ ሕዝቦች ጉባኤ በይፋ ሥልጣናቸው ይጸድቃል።

ፓርቲው በተጨማሪም 25 አባላት ያሉትን የፖሊት ቢሮ እንዲሁም ሰባት አባላት ያሉትን ቋሚ የፖሊት ቢሮን መርጧል። ፕሬዚዳንቱ ከፍተኛ ባለሥልጣኖቻቸውንም ያስተዋወቁ ሲሆን ከነዚህም መካከል የቀድሞው የሻንጋይ ፓርቲ መሪ ይገኙበታል። ሊ ኪያንግ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትርም ይሆናሉ።

ዢ ጂንፒንግ ትናንት አዲሱን የፖሊት ቢሮ ቋሚ ኮሚቴንም እየመሩ ወደ መድረክ ወጥተዋል። ፕሬዚዳንቱ ለመገናኛ ብዙኃንም ፓርቲያቸው ያደረገውን ጉባኤ በተሳካ ሁኔታ እንዳጠናቀቀ ገልጸው "ጥንካሬያችንን በማሰባሰብ በአንድነት ወደፊት እንቀጥላለን" ብለዋል።

ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ጉባኤውን በከፍተኛ ፍላጎት ሲከታተል መቆየቱን ጠቅሰው የሀገር መሪዎች የእንኳን ደስ አላችሁ መልእክትና ደብዳቤ መላካቸውን በመግለጽ ለሁሉም ምስጋናቸውን አቅርበዋል።

ከዚያም አዲሱን የፖሊት ቢሮ ቋሚ ኮሚቴ አባላት በማስተዋወቅ "ሁሉንም በደንብ ታውቋቸዋላችሁ" በማለት ተናግረዋል። ዢ ሶስተኛ የስልጣን ዘመናቸውን አውጀው አዲሱ የአመራር ቡድናቸውን ካስተዋወቁ በኋላም ንግግር አድርገዋል።

በዚህ ንግግራቸው ቻይናን የምትመራበት አቅጣጫ



በተመለከተ ፍንጭ ሰጥተዋል። ሀገሪቱ ለዓለም ኢኮኖሚ በሯን እየዘጋጀች ነው የሚል ስጋት በጨመረበት ወቅት ፕሬዚዳንቱ "ቻይና ያለተቀረው ዓለም ማደግ አትችልም እናም ዓለምም ቻይናን ይፈልጋል" ብለዋል።

አክለውም "ከአርባ ዓመታት በላይ ባደረግነው የለውጥ እንቅስቃሴ ሁለት ተአምራትን መፍጠር ችለናል። ፈጣን የኢኮኖሚ ልማት እና ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ማሕበራዊ መረጋጋት ነው" ብለዋል



## ቀጣዩ የዩኬ ጠቅላይ ሚኒስትር ማን ይሆን?

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በተሾሙ በ45 ቀናት ሥልጣን በቃኝ ያሉትን የዩኬ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊዝ ትረስን ለመተካት የሚደረገው ውድድር ቀነ ገደብ ተቃርቧል። በዚህ ውድድር ላይ የድጋፍ ድምፅ በማግኘት ሪሺ ሱናክ ቢመሩም የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን ደጋፊዎች ተስፋቸው ከፍ እንዳለ ነው።

የውድድሩ ቀነ ገደብ በተቃረበበት በዚህ ወቅት ከፍተኛ ስፍራ የተሰጣቸው ሁለቱ ተወዳዳሪዎች ቦሪስ ጆንሰን እና ሪሺ ሱናክ ተወያይተዋል። ውይይቱ መካሄዱን ሁለት የተለያዩ ምንጮች ለቢቢሲ ቢናገሩም ሁለቱም ፖለቲከኞች ስለተወያዩባቸው ጉዳዮች ከመግለጽ ተቆጥበዋል።

ሪሺ ሱናክ የቀድሞ የጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን አጋሮችን ጨምሮ ከፓርቲያቸው 128 የፓርላማ አባላትን ድጋፍ በመሰብሰብ ውድድሩን እየመሩ ይገኛሉ። የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን በ53 የድምጽ ድጋፍ ሁለተኛ ሆነው እየተከተሉ ስለመሆናቸው ቢቢሲ መረጃ አግኝቷል።

ሆኖም ደጋፊዎቻቸው ወደ ውድድሩ ለመግባት የሚያስፈልገው የድምፅ ድጋፍ እንዳላቸው በመጥቀስ 100 የፓርላማ አባላት የድጋፍ ድምጽ እንዳገኙ ይከራከራሉ። የሪሺ ሱናክ ደጋፊዎች በዚህ ላይ ጥርጣሬ ያላቸው ሲሆን የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ማስረጃ እንዲያሳዩም ጠይቀዋል።

ፔኒ ሞርዳውንት ውድድሩ መቀላቀላቸውን በይፋ ያሳወቁ ብቸኛ እጩ ናቸው ነገር ግን በ23 የፓርላማ አባላት ድጋፍ ወደ ኋላ ቀርተዋል። የቢቢሲዋ ላውራ ኩንስበርግ ቦሪስ ጆንሰን እና ሪሺ ሱናክ ቅዳሜ አመሻሹ ላይ ተገናኝተው እንደነበር ገልጻ ነገር ግን በውይይታቸው ላይ መግለጫ ይወጣ እንደሆነ እርግጠኛ አልነበረችም።

ቢቢሲ ድጋፍ የሰጡ የፓርላማ አባላትን መረጃ ሲሰበስብ ቆይቷል።

ከ357 ወግ አጥባቂ የፓርላማ አባላት መካከል የ204ቱ የመምረጥ ፍላጎታቸው የሚታወቅ እና በቢቢሲ የተረጋገጠ ሲሆን በርካቶች አሁንም ገና ፍላጎታቸውን አልገለጹም።

ለውድድሩ በቂ ድጋፍ ለማግኘት እስከ ፊታችን ሰኞ 8 ሰዓት ድረስ ጊዜ አላቸው። በዚህም ለሚቀጥለው የውድድር ደረጃ ብቁ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ። የፓርቲው የፓርላማ አባላት አንድ እጩን ብቻ የሚደግፉ ከሆነ ሰኞ ከሰዓት በኋላ ዩናይትድ ኪንግደም አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሊኖራት ይችላል።

ካልሆነ ግን የወግ አጥባቂ ፓርቲ አባላት ምርጫ በኦንላይን የሚያካሂዱ ሲሆን ውጤቱም በመጪው ሳምንት አርብ ይፋ ይሆናል። የምርጫ አስተያየቶች እንደሚያሳዩት በዚህ ኦንላይን ምርጫ ጠቅላይ ሚኒስትር ቦሪስ ጆንሰን የአባላቱን ድምጽ ሊያሸንፉ እንደሚችሉ ነው የተገለጸው።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

## በቡራዩ የተገነባው የልዩ ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት

ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውን ተማሪዎችም ይሁኑ የፈጠራ ሰዎች ተሰጥኦቸውን አበልጽገው ወደ ምርትና አገልግሎት ለመቀየር ሲያስቡ የትምህርት ቆይታቸውን ማጠናቀቅ ግድ ይላቸዋል፣ አሊያም ምቹ ሁኔታ ሳይፈጠርላቸው ባክነው ይቀራሉ። ለእነዚህ ልጆች የሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ባለመስፋፋታቸው ምክንያት ኢትዮጵያ ከነዚህ ባለተሰጥኦዎች ማግኘት ያለባትን አዳዲስ ነገሮች እንዳታገኝ ያደርጋታል፡፡ በተጨማሪም በባለተሰጥኦዎች በቀላሉ የሚሠሩት የፈጠራ ሥራዎችን ከሌላ አገር በብዙ ዶላር ወጪ እንድታስገባ ምክንያት ይሆናል፡፡ አሁን ግን በቡራዩ ከተማ የተገነባው የልዩ ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት በመገንባቱ ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች ይቀርፋል ተብሎ ታምኖበታል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በሰባት መቶ ስምንት ሚሊዮን ስድስት መቶ 93 ሺ ብር ወጪ በቡራዩ ከተማ የተገነባውን የልዩ ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት ባሳለፍነው ሳምንት ዓርብ ጥቅምት 10 ቀን 2014 ዓ.ም መርቀው ከፍተዋል፡፡ ትምህርት ቤቱ አንድ ሺ ባለ ልዩ ተሰጥኦ ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር እንደሚችል ተጠቅሷል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በቡራዩ ከተማ የተገነባውን የልዩ ተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት መርቀው በከፈቱበት ዕለት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የብሩህ አቅሞችና ተሰጥኦዎች ባለቤት ምድር ናት፡፡ ባለ ተሰጥኦ ታዳጊዎችና ወጣቶች ክህሎታቸውን እያዳበሩ፣ አገራቸውን በቴክኖሎጂ ከበለጸጉ አገራት ተርታ እንዲያሰልፉ፣ እንደ ቡራዩ የተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት ያሉ የተሰጥኦ ማዕከላትን ማብዛት ይገባል።

ኢትዮጵያ የምትቀየረው፤ ልዩ ተሰጥኦ ያላቸው ሰዎችን የሚያበረታቱና የሚደግፉ ማዕከላት ሲስፋፉ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በቡራዩ የተገነባው ልዩ የተሰጥኦ ትምህርት ቤት የተለየ የፈጠራ ሃሳብና ክህሎት ያላቸው ወጣቶችና ታዳጊዎች ለአገር ጥቅም ከፍተኛ ሚና



እንዲያበረክቱ ያስችላል በማለት አስገንዝበዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንዳሉት፤ አገር የሚቀየረው በወሬ ሳይሆን በፈጠራ ነው፤ እነዚህ የልዩ ተሰጥኦ ባለቤቶችን የፈጠራ ሃሳባቸውን ወደ ተግባር የሚቀይሩበትና የሚያበለጽጉበት ዐውድ መፍጠር አስፈላጊ ነው፤ ይህን ማድረግ ሲቻልም እነሱም ይጠቀማሉ፤ እኛም እንደ አገር እናተርፋለን፡፡

ዓለማችን በቴክኖሎጂ መጥቃለች። አገራችን ኢትዮጵያም ቴክኖሎጂ ከሚያስገኛቸው እንደ ኢኮኖሚ ያሉ ትሩፋቶች ተጠቃሚ ለመሆን፣ በዘርፉ የላቀ ዕውቀት ያላቸው ባለሙያዎችን ማፍራቷ ግድ መሆኑን በማመልከትም፤ ከየትኛውም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚመጡ ወጣቶች ተሰጥኦአቸውን የሚያጎለብቱበት ትምህርት ቤት እንደሚሆንም ይገልጻሉ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንደገለጹት፤ የምንተባበር፤ የምንደማመጥ፤ በዘር በሃይማኖት የማንገፋፋ ስንሆን አገራችንን በቀላሉ ማሳደግ እንችላለን፤ የሃሳብ ልዩነት ሳይገድበን አገራችንን በትብብር ማሳደግና ማበልጸግ ያስፈልጋል፡፡ ፕሮጀክቱ ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ በ10 ሄክታር መሬት ላይ የሚያርፍ ሲሆን፤ የተመረቀው በአምስት ነጥብ አራት ሄክታር ላይ ያረፈው ፕሮጀክት ነው።

የልዩ የተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤቱ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል አስፈላጊ ቁሳቁሶች የተሟላለት ሲሆን መጽሐፍ፣ ኮምፒውተሮች፣ የቤተ ሙከራ ዕቃዎችንና ሌሎች አስፈላጊ ዕቃዎች የተሟሉለት መሆኑ ተጠቅሷል። የተመረቀው የተሰጥኦ ማበልጸጊያ ትምህርት ቤት ባለተሰጥኦዎችን በመለየት ከመደበኛ መማር ማስተማር ሳይለዩ ልዩ ተሰጥኦዋቸውን የሚያበለጽጉበት ይሆናል፡፡

ህንጻው ማደሪያ፣ የመመገቢያ አዳራሽ፣ የአስተዳደር ህንጻ፣ የህክምና ማዕከል፣ መማሪያ ክፍሎች፣ ቤተ ሙከራ፣ ቤተ መጽሐፍ እና ወርክ ሾፖች ያሉት መሆኑም ተጠቁሟል፡፡ የፈጠራ ሐሳብ ያላቸውን ዜጎች በማገዝ ኢትዮጵያን ተጠቃሚ የሚያደርግ ትምህርት ቤት እንደሚሆንም ይጠበቃል። የትምህርት ቤቱ ግንባታ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ በልዩ ልዩ መንገድ አስተዋጽኦ ላበረከቱ የአካባቢው ነዋሪዎች ጠቅላይ ሚንስትሩ ምስጋና አቅርበዋል፡፡

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾቻችንንና ፌስቡክ ገጾቻችንን ይጎብኙ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

# አዲስ ዘመን ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የብሔራዊ ስቴድየም ግንባታ ተቀዛቀዘ እንጂ አልተቋረጠም

**ቦጋስ አበበ**

በ2008 ዓ.ም. ግንባታውን አንድ ብሎ የጀመረው ብሔራዊ ስቴድየም፣ የመጀመሪያውን የግንባታ ምዕራፍ በ2012 ዓ.ም. ቢያጠናቅቅም፣ በኮቪድ-19 ወረርሽኝና በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት የምዕራፍ ሁለት ግንባታው በዕቅዱ መሠረት ለማከናወን እንዳልተቻለ ሲነገር መቆየቱ ይታወቃል። የስቴድየሙ ግንባታ በውጪ ምንዛሬ እጥረት ምክንያት መቆሙን የሚገልጹ የተለያዩ ዘገባዎች ሰሞኑን በማህበራዊ የትስስር ገጾች ሲዘዋወሩ ታይተዋል። ይሁን እንጂ ይህ ከእውነት የራቀ መሆኑን አዲስ ዘመን ለጉዳዩ ቅርብ ከሆኑ ምንጮች አረጋግጧል።

የብሔራዊ ስታዲየም ግንባታው ተቀዛቀዘ እንጂ እንዳልቆመ የገለጹት የአዲስ ዘመን ምንጮች፣ ግንባታው በነበረበት ፍጥነት እንዳልቀጠለ ጠቁመዋል። ለዚህ ምክንያት ደግሞ ተቋራጩ የዋጋ ማስተካከያ እንዲያደርግ በመንግስት ደረጃ ንግግር እየተደረገበት በመሆኑ ነው:: ግንባታው ቆሟል የሚባለውም ከተቋራጩ ጋር ውል ሲቋረጥ ብቻ እንደሆነ ታውቋል።

ከአዲስ አበባ ስቴድየም እድሳት ጋር ተያይዞም በተለያዩ ደረጃዎች እድሳቱ እየተከናወነ እንደሚገኝ ለማረጋገጥ ተችሏል። የመጫወቻ ሜዳ እና የተጫዋቾች ማረፊያ፣ የክብር እንግዶችና የተመልካች ንጽህና ቤቶችን የሚመለከተው የመጀመሪያው ደረጃ እድሳት መጠናቀቁ የተጠቆመ ሲሆን፣ ቀጣዩን ስራ ለማስጀመርም ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በሂደት ላይ እንደሚገኝ ታውቋል። ቀሪው የግንባታ ስራ በውል የሚከናወን እንዲሁም በካፍ ስታንዳርድ መሰረት ቁሳቁሶችን ማሟላት ደግሞ በግዢ እንደሚከናወንም ተገልጿል።



**የብሔራዊ ስቴድየም ሁለተኛ ዙር ግንባታ ቢቀዛቀዝም እንዳልቆመ ታውቋል**

ግንባታዎቹን በሚመለከት ከዚህ ቀደም በተለያዩ ጊዜያት የት ደርሷል የሚለውን የመገናኛ ብዙሃንን በመጋበዝ ማብራሪያ ይሰጥ ነበር:: ይሁንና በተያዘላቸው ጊዜ አለመጠናቀቃቸውን ተከትሎ ከእውቀት ውጭ እንዲሁም ያለውን ነገር ካለመረዳት አግባብ ያልሆኑ ትችቶች ሲቀርቡ ይስተዋላል:: በመሆኑም ውጤት ለማሳየት በማቀድ መግለጫና ማብራሪያ ሳይሰጥ ለረጅም ጊዜ ቆይቷል::

በአዲስ አበባ ቦሌ አካባቢ በቻይናው ስቴት ኮንስትራክሽን ኢንጂነሪንግ ኩባንያ እየተገነባ ያለው ስቴድየም 62 ሺህ ሰዎችን የመያዝ አቅም አለው።

ከስቴድየሙ እግር ኳስ ሜዳ ሳር ማልበስና የመሮጫ ትራክ በስተቀር በአሁኑ ወቅት የመጀመሪያው ምእራፍ ሥራ የተጠናቀቀ ሲሆን ይህም አጠቃላይ የህንፃውን መዋቅር ጨምሮ የስፖርተኞች ማረፊያ፣ ቢሮዎች፣ የጋዜጠኞች ማስተናገጃ ወዘተ ያካትታል።

የመጀመሪያው ምእራፍ የፕሮጀክቱ ሥራ በተወሰነ ጊዜ የዘገየ ሲሆን ለዚህም ምክንያቶቹ ከውጭ የሚገቡ እቃዎች በጊዜው አለመድረስና የውጭ ምንዛሬ እጥረት ተጠቅሰዋል።

ሁለተኛው ምእራፍ የስቴድየሙ ፕሮጀክት ከሚካተቱት ሥራዎች መካከል የመጫወቻ ሜዳውን ሳር ማልበስ፣ የመሮጫ ትራክ ማንጠፍ፣ የስታዲየሙን ጣሪያ ማልበስና ወንበር መግጠም ይገኙበታል።

ከዚህም ሌላ ሰው ሰራሽ ሀይቅ፣ የሄሊኮፍተር ማረፊያ፣ ዘመናዊ የደህንነት ካሜራ ሌሎች በርካታ ስራዎች ይከናወናሉ ተብሏል።

ለመጀመሪያው ምዕራፍ ግንባታ ከ2.47 ቢሊዮን ብር በላይ ወጪ እንደተደረገ ከዚህ ቀደም የተገለጸ ሲሆን፣ ሁለተኛው ምእራፍ የግንባታ ሥራ ከዚህ የበለጠ ወጪ ይጠይቃል ተብሎ ይጠበቃል።

ስቴድየሙ ተጠናቆ ለአገልግሎት ሲበቃ ዓለም አቀፍ የእግር ኳስ ውድድሮችን ከማስተናገድ በተጨማሪ ሌሎች እንደ አትሌቲክስ አይነት ውድድሮችን ለማስተናገድ ምቹ አጋጣሚን የሚፈጥር ነው። የሁለተኛውን ምዕራፍ ግንባታ በዘጠኝ መቶ ቀናት ለማጠናቀቅ የታሰበ ቢሆንም ከተያዘው ቀን በላይ እንደሚያስፈልግ ተረጋግጧል። ሁለተኛውን ዙር ግንባታ ለማጠናቀቅ ከ 5.5 ቢሊዮን ብር በላይ እንደሚያስወጣ ይጠበቃል።

የአደይ አበባ ስታዲየም ሙሉ ለሙሉ ሲጠናቀቅ ከ 62,000 በላይ ተመልካቾችን የመያዝ አቅም እንዳለው ይጠበቃል። ይህ ውብ ስታዲየም ተገንብቶ ሲጠናቀቅ የጋዜጣዊ መግለጫ ክፍሎች (ሳውንድ ፕሩፍ የሆነ)፣ 8 ቪ አይ ፒ ክፍሎች፣ 2 ቪ ቪ አይ ፒ ክፍሎች ፣ ከ 1,000 በላይ መፀዳጃ ቤቶች (የወንድ እና የሴት )፣ 10 የሚዲያ ክፍሎች፣ ከ15 በላይ ሬስቶራንቶች (በአንድ ጊዜ ከ2,500 ሰው በላይ ማስተናገድ የሚችሉ) እና 7 ሊፍቶች እንደሚኖሩት ይጠበቃል።

## ከኢ.ፌ.ዲ.ሪ የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር
## ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# የሳይበር ታሪክ በወፍ በረር

**ደበል ካሳ**

### ሳይበርና የሳይበር ዘመን

በዘመናት ሒደት ውስጥ የሰው ልጅ ከፈጠራቸው ትልልቅ የቴክኖሎጂ ግኝቶች መካከል አንዱና ዋነኛው የበይነ መረብ (Internet) ቴክኖሎጂ ነው:: አንዳንዶች ከሦስተኛውም ባሻገር አራተኛው ነው የኢንዱስትሪ አብዮት እንደሆነ የሚናገሩለት በተለይም ከአውሮፓውያኑ 1970ዎቹ ጀምሮ በዓለማችን ላይ የነበረውና በኮምፒውተር፣ በሰዎችና በልዩ ልዩ በመሰረተ ልማቶች መስተጋብር ላይ የተመሰረተው ሳይበር በመባል የሚታወቀው ይህ ዘመን እጅጉን የተለየ ባህርይ ያለው አዲስ ዓይነት ምህዳር እንዲፈጠር አድርጓል:: ኑሯችንንም በእጅጉ እያቃለለልን ይገኛል::

ይሁን እንጂ በራሱ መጥፎ ወይንም ጥሩ፣ ጎጂ ወይንም ጠቃሚ የሚባል ነገር ባይኖርም ከሰው ልጆች የአጠቃቀም ሁኔታ ጋር ተያይዞ ማንኛውም አዲስ የስልጣኔ ውጤት ወይንም ግኝት እንደየሰው ዝንባሌ ለጥቅም ወይንም ለጉዳት፣ ለልማት አለያም ለጥፋት የሚውልበት መኖሩ ግልጽ ነው:: የዓለምን የስልጣኔ ደረጃ ወደሌላ አዲስ ምዕራፍ ያሸጋገረውና በዋነኝነት በኮምፒውርና በኢንተርኔት ግኝት ላይ የተመሠረተውና እስካሁንም ድረስ በሂደት ላይ በሚገኘው ሦስተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን የሆነውም ከዚህ የተለየ አይደለም::

ብዙሃኑ የሰው ልጅ ኮምፒውተርንና በይነ መረብን በመጠቀም መልካም ነገርን ለመሥራትና ዓለምን የተሻለች መኖሪያ ለማድረግ ሲታትር ጥቂቶች ደግሞ ታላላቆችን የሰው ልጆች ፈጠራዎችን ለጥፋት በማዋል እኩይ ምርጫ ላይ በመሰማራታቸው ዘመኑ የአልሚዎችና የአጥፊዎች፣ የጠባቂዎችና የአጥቂዎች፣ የልማትና የጥፋት መፎካከሪያ መድረክ ሆኖ ለመቀጠል ተገድዷል:: ከመጀመሪያው እስካሁን ያለው የየሳይበር ዘመን ታሪክም የሚከተለውን ይመስላል::

### የመጀመሪያዎቹ ዓመታት የሳይበር ዘመን ታሪክ

እስከ አውሮፓያኑ አቆጣጠር 1970 አካባቢ ሳይበር ደህንነት ጉዳይ ብዙም አሳሳቢ አልነበረም:: በ1980ዎቹ የግል መገልገያ ኮምፒውተሮች(Personal Computers) በሰፊው ለሕዝብ ተደራሽ መሆናቸውን ተከትሎ ግን የመጀመሪያዎቹን የኮምፒውተር ቫይረሶች በመጠቀም ጥቃቶችን ማድረስ ተጀመረ:: እናም ዋነኛ ዓላማውን ጥቃቶቹን በመከላከልና በማክሸፍ ላይ ያደረገው የሳይበር ደህንነት ሥራ ትኩረት እያገኘ መጣ:: ስለሆነም በኮምፒውተር ቫይረሶች አማካኝነት የሚፈጸመውን የዘመኑን የሳይበር ጥቃት ለመከላከልና ለማክሸፍ ፀረ-ቫይረሶችን በመፍትሔነት ጥቅም ላይ ማዋል ተጀመረ::

### የሁለተኛው ትውልድ የሳይበር ደህንነት ታሪክ

ከዚያም የበይነ መረብ ቴክኖሎጂ ይበልጥ እየተሻሻለ መጥቶ እንደ አውሮፓውያኑ አቆጣጠር ጃኑዋሪ 1 ቀን 1983 ያለምንም ቁሳዊ ገመድ ኮምፒውተሮችን በያሉበት እርስ በእርስ የሚያስተሳስረው በመጀመሪያ "ትራንስፈር ኮንትሮል ፕሮቶኮል" በኋላ "ኢንተርኔት ፕሮቶኮል" የተባለው የመገናኛ ዘዴ ወይንም በአሁኑ አጠራር "ኢንተርኔት" በይፋ ሥራ ላይ ዋለ:: በዚህም በዓለም ዙሪያ ያሉ ኮምፒውተሮች በስፋት እርስ በእርስ መተሳሰር በመጀመራቸው የሳይበር ጥቃቶችም በዚያው ልክ እየጨመሩ መጡ:: የሳይበር አጥቂዎች አንድ ወይንም ሁለት ኮምፒውተሮችን በተናጠል ከማጥቃት ኢንተርኔትን በመጠቀም በአንድ ጊዜ ብዙ ኮምፒውተሮችን በብዛትና በፍጥነት ማጥቃትና መረጃዎችን መመንተፍ ቻሉ:: የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችም የጥቃቱን አዲስ ዕድገት ተከታትለው መፍትሔ ለመስጠት ሞከሩ:: ለዚህም "ፋየር ወል" የሚባል የኦንላይን የሳይበር ጥቃት መከላከያ ቴክኖሎጂ ፈጥረው ጥቅም ላይ አዋሉ::

### የሦስተኛው ትውልድ የሳይበር ደህንነት ታሪክ

የሳይበር ጥቃት ፈጻሚዎች ጥቃታቸውንና የጥቃት መንገዳቸውን በየጊዜው በማሻሻል በ2000ቹ መጀመሪያ አዲስ የጥቃት መፈጸሚያ ዘዴዎችን ጥቅም ላይ ማዋል ጀመሩ:: ይኸውም የጥቃት መፈጸሚያ ዘዴያቸውን ከፍሎፒ ዲስክና ከቀጥታ የኦንላይን የኢንተርኔት ጥቃት ወደሶፍትዌሮችና የበይነ መረብ የአሠራር ሥርዓቶች አሸጋገሩት:: በዚህም መረጃን መመንተፍ ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ የኮምፒውተር ሥርዓቶችን ማጥቃትና ትስስሩን በመረበሽ የበለጠ ጫና መፍጠር የሚችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ:: ይሁን እንጂ የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችም በመጀመሪያ "ኢንስትራክሽን ዲቴክሽን ሲስተምስ" ቀጥሎ ደግሞ "ኢንስትራክሽን ፕሪቬንሽን ሲስተም" የሚባሉ የደህንነት ሲስተሞችን በመጠቀም ጥቃቶችን ለመከላከልና መፍትሔ ለመስጠት በብርቱው ጣሩ::

### የአራተኛው ትውልድ የሳይበር ደህንነት ታሪክ

ከ2010 ጀምሮ ደግሞ የሶፍትዌር ቴክኖሎጂ በከፍተኛ ደረጃ እያደጉ መምጣታቸውን ተከትሎ በሦስተኛው ትውልድ የተጀመረው በአጥፊ ሶፍትዌሮች አማካኝነት የሚፈጸመው የሳይበር ጥቃት በዓይነትና በብዛት እጅጉን እየተወሳሰበ መጣ:: ለመለየትና ምላሽ ለመስጠት እስኪያስቸግር ድረስ የጥቃቱ ዘዴ እጅጉን የተራቀቀ ደረጃ ላይ ደረሰ:: የሳይበር ደህንነት ባለሙያዎችም "ሳንድቦክሲንግ" የተባለ ዘዴን በመጠቀም ለጥቃቱ መፍትሔ ለመስጠት ሞከሩ:: ሆኖም ብዙም አልተሳካም:: በተፎካካሪዎቻቸው የሳይበር አጥቂዎች ብዙ ርቀት መቀደማቸውን ለማመን ተገደዱ::

### አሁንና የመጭው ዘመን የሳይበር ደህንነት ፈተና

የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂው በከፍተኛ ደረጃ እያደገ መምጣቱን ተከትሎ በተለይም ከእአአ 2017 ወዲህ ደግሞ አጥቂዎች አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ራሳቸውን የበለጠ እያበቁ፣ በጥቃት ዘዴያቸውም ይበልጥ እየተራቀቁ መጥተዋል:: በመሆኑም አጥቂዎቹ ኮምፒውተሮችንና የተያያዥ መሣሪያዎችን፣ የመረጃ ክምችትና ስርጭት ሁኔታዎችን፣ የሃርድዌርና የሶፍትዌር፣ የሲስተምና አፕሊኬሽኖችን፣ የአውታረ መረብ መገልገያ የግላዊነት መለያዎችን ሁሉንም የበይነ መረብና የኮምፒውተር ነገራቶችን በመጠቀም በከፍተኛ ፍጥነትና ዓለምን ባካለለ ስፋት ግዙፍ የሳይበር ጥቃቶችን ማድረስ የሚችሉበት የዕድገት ደረጃ ላይ ደርሰዋል::

እናም በሰው ልጆችና በዓለማችን ደህንነት ላይ ከባድና አሳሳቢ ስጋት ተደቅኗል:: ለዚህ ደግሞ ዋነኛው ምክንያት ይላል እውቁ ቴክኖሎጂስት ጂል ሸውድ፤ "ዓለም የሳይበር ዘመን አወንታዊ ጎን የፈጠረውን ጥቅሙን ለማጋበስ መሯሯጥ እንጂ አሉታዊ ጎኑ የሚያስከትለውን ጉዳት ለመከላከል ትኩረት ባለመስጠቱ ነው"::

### የመፍትሔ አማራጮች

ስለሆነም የሰው ልጅ በየጊዜው በከፍተኛ ደረጃ በማደግ ላይ የሚገኘውን የሳይበር ጥቃት ለመከላከልና ራሱን ከጥፋት ለማዳን ቆም ብሎ ሊያስብ ይገባዋል:: ለዚህም የዘርፉ ምሁራን ሦስት መሠረታዊ መፍትሔዎችን ይመክራሉ:: እነዚህም አንደኛ እንደከዚህ በፊቱ ለጥቃት ምላሽ በመስጠት ላይ የተመሠረተ ሳይሆን አስቀድሞ በመከላከል ላይ የተመሠረተ ንቁና ወዲያውኑ ምላሽ መስጠት የሚያስችል(Real time prevention) የሳይበር ደህንነት ሥርዓትን መዘርጋት:: ሁለተኛ በግለሰብ፣ በተቋም በአገር፣ በቀጠናና በአህጉር ደረጃ ከሚደረግ የተናጠል የሳይበር ደህንነት ሥርዓት ይልቅ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተቀናጀና ሁሉንም ያካተተ(Wholistic) የሳይበር ደህንነት ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ:: ሦስተኛ የሳይበር አጥቂዎቹ የደረሱበትን ደረጃ የሚመጥን፣ ዘመኑን የሚዋጁ ስልጡን የሳይበር ደህንነት ቴክኖሎጂን መጠቀም ለዚህም ቴክኖሎጂው የሚፈልገውን ሁሉ ለማሟላት በቂ በጀት፣ የሰው ኃይልና የአሠራር ማዕቀፍ ለመቅረጽና ለመተግበር ቁርጠኛ መሆን ናቸው::

በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ